




የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅከላውያን መዘምራን በመስቀል አደባባይ


ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ

ዋጋ ብር 3.00

© Safeguarding Religio... Ethiopia Orthodox Church

# ፈለገ ጥበብ

፬ ዓመት ቁጥር ፲ መስከረም - ኅዳር ... ዓ/ም







- ከንግግር ወሰን ባሻገር፤ ሃይማኖትና ሥልጣኔ በአዲሱ ክፍለ ዘመን . . . . . . . . .
- ባሕረ ሐሳባችን፡ ሐሳበ ቢዘን ፣ ሐሳበ ጐንዳጐንዲ
- ኤች አይቪ ኤድስን መከላከል ይቻላል?
- በብሉይና በሐዲስ ኪዳን የክህነት አገልግሎት ዘመን ጽጌ . . . . . . . . . . . .
- ከወጣቱ የሚጠበቅ ክርስቲያናዊ ግዴታ
- የአንድነታችን መግለጫ

www.ethiopianorthodox.org

# እኛና እናንተ

## በቅርብ እንደማውቃቸው

ይድረስ ለፈለገ ጥበብ መጽሔት ዝግጅት ክፍል

መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ

ወደፈለገ ጥበብ መጽሔት አዘጋጆች ይህን መልእክት ለመጻፍ ያነሣሣኝ፣ ፈለገ ጥበብ ፫ኛ ዓመት ቁጥር ፰ ላይ የብፁዕ አባታችን አቡነ መቃርዮስ «እኔም ወጣት ነበርኩ» በሚለው አርእስት ያዘጋጃችሁትን በማየት በጣም ተደስቼአለሁ። በወጣትነት እናላ ጉልበታቸው ለ8 ዓመት በጅማ ዞን ቆይታቸው ከፈጸሙት ተግባራት ሁሉ አንድን እንኳን ሳይገልጹ ማለፋቸው ቅሬታ ስለተሰማኝ ከጅምሩ እስከ መጨረሻው ስምንት ዓመት አብሬአቸው ስለ ነበርኩ ከብዙ የልማት ሥራዎቻቸው ጥቂቱን ለመግለጽ አእምሮዬን ስላስገደደኝ ነው። ወትሮውንም በቅርብ እንደማውቃቸው የፈጸሙት ሥራቸው በዓይን የሚታይ በእጅ የሚዳሰስ ይናገርላቸዋል እንጂ ይህን ሠርቼአለሁ ይህን ፈጽሜአለሁ ይታወቅልኝ የማለት ክንቱ ውዳሴ የመሻት ባሕርይ በተፈጥሮአቸው የማያውቁ ትሑህ፣ ደከመኝ፣ ሰለቸኝ የማያሰኛቸው በትጉህ ምሳሌነት የሚጠቀሱ ቅዱስ ንጹሕ አባት ስለሆኑ መልካም ሥራቸውን ሁሉ ለመግለጽ አእምሮዬ እስበ ለእናንተ ለመግለጽ አስብኩ።

ይኸን ያህል ውይይት ለማድረግ ተጠያቂው ፈቃደኛ ሆነው ለንባብ ማብቃታችሁ ቀላል ስላልሆነ ለዝግጅት ክፍሉ ምሥጋና ይድረሰው። ዝግጅት ክፍላችሁ አስተማሪ እንደ መሆኑ እኔ እስካሁን አንባቢ እንጂ ካሁን ቀደም የጽሑፍ ተሳታፊ ስላልሆንኩ የረዘመውን በማሳጠርና የጐደለውን ሞልታችሁ ለአባታችን እንደሚገባ አድርጋችሁ ለጅማ ዞን ልማት እጅግ በጣም ደክመው ከፈጸሙት ሥራዎች እንኳን «በዓይን በዑልፉ» እንዲሉ ያቀረብኩትን በተባይ መጽሔታችሁ ለንባብ ብታበቁልኝ ምሥጋናዬ የላቀ ነው።

ብፁዕነታቸው የከፋ ጠቅላይ ግዛት ቆሞስ ሆነው በመጡ ጊዜ ቅድሚያ የሰጡት ሰብከተ ወንጌልና ሰንበት ትምህርትን በስድስቱ አውራጃዎች ማስፋፋት ነበር። ከዚያም ቀጥሎ ከአምስት መቶ በላይ የሚደገፍ የሰብከተ ወንጌል አዳራሽ አሠርተዋል።

የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት አሠርተው ቢሮው ራሱ እንዲችል አድርገዋል። ከዚህም ባሻገር የስድስቱ አውራጃዎች ቢሮዎች አሠርተዋል።

ከአሠሯቸው አብያተ ክርስቲያናት ለአብነት የሚጠቀሱ፤

፩. በጅማ ከተማ ደብረመዊዕ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ሙሉ አድሳት እና ውስጡን አፍርሰው በዘመናዊ መልክ ያሠሩት፤

፪. በጅማ ከተማ የደብረ ኤፍራታ ቅድስት ማርያም ሙሉ እድሳት

፫. በሊሙ አውራጃ የአጋሮ ከተማ ቅድስት ማርያም እድሳት፤

፬. አዲሱ የቤተ ክርስቲያን ሥራ፤ የጅማ ከተማ ደብረ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በአባታችን ብርቱ ጥረት የተሠራ ነው። በየአውራጃውና ወረዳው በጋማ ከብት እየሄዱ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አሠርቷል

፭. በጅማ ወኅኒ ቤት ለሕግ ታራሚዎች ቅድስት ኪዳነ ምሕረትን አሠርተዋል

፮. በከፋ አውራጃ መንበረ ጵጵስና አሠርቷል።

በተለያዩ ጊዜያት በሕይወታቸው ላይ የተቃጣ ገጠመኝ

፩ኛ. የደብረ ሰላም ቅዱስ ገብርኤልን (ጅማ) ቤተ ክርስቲያን ጅማ ከተማ ውስጥ ሲያሰሩ የቀድሞ መሬት ከበርቴዎች እሳቸውን ለመግደል በቅጥር ነፍሰ ገዳይ ሕይወታቸውን ለማጥፋት ከፈተኛ ጥበቃና ክትትል አድርገው በእግዚአብሔር ኃይል ተርፈዋል።

፪ኛ. እጅግ ዘግናኝ የሀገረ ስብከቱን ያቦታ የጠቅላይ ግዛቱ ፖሊስ መ/ቤት በተለበት አልፈው የአጥር ሥራ ጀምረው አባታችን እሰ በሕይወት ቆሜ የቤተ ክርስቲያን መብት አይደፈርም፤ በማለት ስለተከላከሉ ሠራተኞቹ ለጥና ጠ/ግዛቱ ፖሊስ አዛዥ ነግረዋቸው አዛዡም እሳት ለብሰው እሳት ጉርሰው መጥተው ብዙ ቃላት ከተለዋወጡ በኋላ ኮረኦሉ ሽጉጣቸውን መዘው ሊተኩሱባቸው ሲሉ በአካባቢው ባለው ሰው ብርታት ሕይወታቸው ተርፎ በኋላ ስለሰው ተጸጽተው በሽማግሌ ይቅርታ ጠይቀዋቸው የታረቁ ሲሆን ቦታውንም አስከብረዋል።

፫ኛ. የደብረ ኤፍራታ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን የከበብ ቦታ ከርስቱ እያቸገሩ ውስብስብ ስለ ነበረ አባታችን ጉዳዩን በፍጥነት ስለያዙ ተመሣጥረው የመግደል መከሩ በማድረግ ያልፈንቀሉት ድንጋይ አልነበረም። ግን በጸሎታቸው ሁሉም ተሸንፈው ሕይወታቸው ተርፎ እስከ አሁን ቆይተዋል።

አባታችን ለጅማ የፈጸሙት ሥራ የጉልበት ብቻ ሳይሆን እስከ ሕይወት መሥዋዕትነት የደከሙ አባት በመሆናቸው ምን ጊዜም መልካም ሥራቸውን የጅማ ሕዝብና ቤተክርስቲያን ስያስታውሰው የሚኖረው ነው። ከዚህ ላይ ይብቃ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ከመምህር አባተ ኃይሉ ባህሩ – ጅማ ከተማ

## በድጋሚ አንድ በሉን

በትምህርቱ መንፈሳዊ ሰላምታዬን በቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር ስም ይድረሳችሁና ከሰላምታዬ በመቀጠል የምገልጽላችሁ ነገር ቢኖር እንደሚከተለው ይሆናል።

በፈለገ ጥበብ ፫ኛ ዓመት ቁጥር ፯ ጥር – መጋቢት ፲፱፻፺ ዓ.ም እትማችሁ ላይ አንድ በሉን በሚል ርእስ አንድ ወንድማችን ከደቡብ ጎንደር ደብረ ታቦር ከተማ አንድ በጣም አሳሳቢና ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፀር የሆነ ተግባር በማጋለጥ አስተያየቱን ፍጹም ትክክለኛ ጥቆማውን አድርሶ ነበር። እናንተም የመናፍቃን መድኃኒት የለሽ በሽታ እንደ መሆናችሁ መጠን የሚገባውንና የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል የሚናገረውን ትክክለኛ መልሽ ሰጥታችኋል።

ነገር ግን ሀገረ ስብከቱ ምንም የወሰደው ርምጃ ባይኖርም ይሆች ባህታዊት ነኝ ባይ መናፈት ቦታውን በመልቀት በአሁኑ ሰዓት በኢሉባቦር ዞን በሁሩ ወረዳ ደብረ ብርሃን ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ያንኑ ከአባቶች ፈለግ ውጭ የሆነውን የመናፍቅነት ሥርዓቷን ይዛ ሌላ ተጨማሪ እስኪታሪ ነገሮችን እያስጠች ትገኛለች።

ማለትም በመጽሔቱ ከጠባው በተጨማሪ ዲያቆናትን ከቤተ ልሔም ውጡ ታቦትን የሚቸረችረው ዲያቆንና ቄስ ነው በማለት ምንም በማያውቀው ምእመን ፊት እየተናገረች ክህናትንና ሕዝቡን እያጋጨች ትገኛለች። ይህን ጉዳይ ሀገረ ስብከቱ በትክክል አጤና የማያዳ ድብዳቤ ቢጽፍባትም ኃይለ ቃል እየተናገረች ግብረ አበሮቿን በማነሳሳት ምንም የተወሰደ እርምጃ የለምና እባካችሁን በእግዚአብሔር ስም በድጋሚ አንድ በሉን።

ወልደሐዋርያ ባልደ ትንሣኤ

## ከኢሉባቦር ዞን – ሶፖራ ከተማ

[illegible]

[illegible] – አዲስ አበባ

አዘጋጅ፦ አስተያየትህንና ጥቆማህን ተቀብለነዋል ለጠየከው ጥያቄ ማብራሪያ ግን በሚቀጥለው እትም በሰፊው ይቀርባልና በትዕግሥት ተከታተል። ✣

የፊት ለፊት ሽፋን ዕንቈባሕርይ ተከሥተና በገነ መርሰና ግርማ ኢልያስ

---


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃና ማስተባበርያ መምርያ በየ፫ወሩ የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት


# ፈለገ ጥበብ


፬ኛ ዓመት ቁጥር ፲

መስከረም – ኅዳር ፲፱፻፺፩ ዓ.ም


## ከአዘጋጁ ብዕር

ዘመናትን አሳልፎ ዘመናትን የሚተካ ጌታ እግዚአብሔር እንኳን ከዘመነ ማቴዎስ ወደ ዘመነ ማርቆስ አደረሳችሁ።

እነሆ ፈለገ ጥበብ መጽሔት ማዘጋጀት ከጀመርንበት እንስቶ አንድ ሁለት ብለን አራት ዓመታት ሆኖአል። ከዚህም ለመድረስ የቻልነውና ሥራችንም የተቃና እንዲሆን ያደረገው የእናንተ ጸሎትና ቀና አመለካከት መሆኑን በጽኑዕ እናምናለን።

ሰው ሳያስበው ተሰባሪ ነውና አገልግሎታችን ለሁሉ እንዲዳረስ በብረቱ ጸልዩልን። እኛን ለማበረታታት በቅርብ በሩቅም ያሉ ክርስቶሳውያን ወገኖች ሁሉ በደብዳቤ፣ በስልክም፣ በአካልም ቀርበው ሐሳብ በመስጠት፣ ደካማ ጐናችንም እንድናስተካክል፣ በጠንካራ ጐናችንም ሥራችን እንድንቀጥልበት ከጐናችን በመሆን ላበረታቱን ምስጋና እናቀርባለን። ለወደፊቱም የተለመደ ሐሳባቸው እንዲለግሱን አደራችን የጸና ነው።

ፈለገ ጥበብ በአሁን እትምዋ ጣዕመ ስብከታቸው ተሰምቶ የማይጠገበው የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ቃለ በረከትን፣ ብዕራቸው የማይነጥፈው የብፁዕ አቡነ ጎሪግዮስ ጽሑፍ፣ ምሥጢራቸው ተቀድቶ የማያልቀው የመልአከ ገነት ገብረሥላሴን ትምህርት የሌሎች ሊቃውንት ቤተክርስቲያን ጥናታዊ ጽሑፎችን ይዛልን ቀርባለች። በተረፈ የጐደለውን ለመሙላት፣ የጠበበውን ለማስፋት፣ የእናንተ ተሳትፎ አንጠይቃለን። ዘመኑ ዘመነ ምሕረት፣ ዘመነ ሰላም፣ ዘመነ በረከት ያድርግልን ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁን።

## ማውጫ


ከንግግር ወሰን ባሻገር፣ ሃይማኖትና ሥልጣኔ

በአዲሱ ክፍለ ዘመን . . . . . . . . ፪

እስመ ነገረ መስቀሉ ዕበድ ውእቱ በኀበ ኅጉላን

ወበኀቤነሰ ኃይለ እግዚአብሔር ውእቱ . ፭

ትምህርተ ሃይማኖት

በብሉይና በሐዲስ ኪዳን የክህነት አገልግሎት

ዘመነ ጽጌ . . . . . . . . . . ፲

ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን

ምሥጢረ ቍርባን . . . . . . . . ፲፩

ባሕረ ሐሳባችን፣ . . . . . . . . ፲፫

ኤች አይቪ ኤድስን መከላከል ይቻላል? . ፲፯

መጣረፀር

መንጋችንን ከተኩላ እንጠብቅ . . . ፲፰

አገልግሎታችን እንዴት ይሁን? . . . ፳

ከወጣት ለወጣት

የአንድነታችን መግለጫ . . . . . . ፳፪

በሰ/ት/ቤት በመኖሬ በጣም ደስተኛ ነኝ ..... ፳፫

ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

ከወጣቱ የሚጠበቅ ክርስቲያናዊ ግዴታ . ፳፭

እኔም ወጣት ነበርኩ

ድፍን አምሳ ዓመታት በቤተ ጉባኤ . ፳፰

ዜና መጽሔት . . . . . . . . . . ፴፩

እስትጉቡእ . . . . . . . . . . ፴፪

እኛ እና እናንተ . . የፊት ለፊት ሽፋኑ ውስጥ



ኦርታዕያን (ኤዲተሮች)

ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ

መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

ቀሲስ በላይ ተገኝ



አዘጋጆች:-

ዋና አዘጋጅ መምህር ዕንቈባሕርይ ተከሥተ

ም/ዋና አዘጋጅ መምህር ሰሎሞን ገብሩ

☎ 562652፤ 550098፤ 550099 Ex.46

✉ 81286 – አዲስ አበባ



www.ethiopianorthodox.org

# ከንግግር ወሰን ባሻገር፤

## ሃይማኖትና ሥልጣኔ በአዲሱ ክፍለ ዘመን

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፤ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በዕለተ ሰንበት ነሐሴ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በባርሴሎና ከተማ (በእስጳንያ) በተደረገው ዓለም አቀፍ የሰላም ስብሰባ በታላቁ ሊቾኡ አዳራሽ ያደረጉት ክፍል አንድና ክፍል ሁለት ንግግር ሙሉ ቃል።

### ክፍል አንድ

«ከቅዱስ ፋሲካ በኋላ በኅብረት፤ ዓለም አቀፍ ክርስ ቲያናዊ አንድነት»

ክቡር ሊቀ መንበር
ብፁዓን ፓትርያርኮች
ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት
የተወደዳችሁ ወንድምና እህቶች

የታወቁ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና የተከበሩ የሥነ – መለኮት ምሁራን በሚገኙበት በዚህ ታላቅ ጉባኤ ትንሽ ንግግር ለማቅረብ በመቻሌ ደስታ ይሰማኛል። ዛሬ ጥዋት የምን መለከተው ርእስ «ከቅዱስ ፋሲካ በኋላ በኅብረት፤ ዓለም አቀፍ ክርስ ቲያናዊ አንድነት» የሚል ነው።

ሁላችንም እንደምናውቀው በዐለ ፋሲካ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት የተነሣበትን ዕለት የምናከብርበት ነው። በእውነቱ ይህ ርእስ በመጀመሪያ ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ «መጣ በመካከላቸውም ቆሞ አላቸው ሰላም ለእናንተ ይሁን። አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ... ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ» (ዮሐ. ፳፥፲፱–፳፪) በማለት ሀብተ መንፈስ ቅዱስን እስካሳደረባቸው ጊዜ ድረስ በአንድነት ተቀምጠው የነበሩ ሐዋርያትን ያመለክታል። ሰላምን ያስገኘላቸው፣ ጽማዌ፣ ጥብዓት፣ ትጋትና ዓለም አቀፋዊ ጥሪያቸውን ለማከናወን ክህነታዊ ሥልጣንን ያሰጣቸው ይህ ኅብረትና እርሱን ለመጠበቅ በአንድ ነት መሰባሰባቸው ነው። ይህ ኅብረትና የተጣመረ አንድነት ነው በጰራቅሊ ጦስ ዕለት የመንፈስ ቅዱስን ጸጋና ኃይል ለመቀበል ያስቻላቸው። እንደ እውነቱ ከሆነ እስከ አሁን ድረስ ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት የሆናትና በውስጧም የሚሠራ ይህ መንፈሳዊ ጸጋ እና የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነው።

የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ለክርስቲያኖች ተስፋ ትንሣኤ ማረጋገጫ ነው (፩ጴጥ.፩፥፫)። በእርግጥ ትንሣኤ ሙሉ ለሙሉ መዳናችንን የሚያረጋግጥልን የክርስትና እምነት መሠረት ነው። በተጨማሪም ትንሣኤ የሞት ኃይል እንደ ተወገደና ሰውነታችንም በእውነት እንደሚነሣ ፍጹም ያረጋግጥልናል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ጌታችን ካልተነሣ ስብከታችን ከንቱ ነው እምነታችንም ከንቱ ነው። ጌታችን ለደቀመዛሙርቱና ለሌሎችም ብዙ ጊዜ ስለተገለጠላቸው ትንሣኤው እውነትና ትክክል ነው። (፩ቆሮ.፲፭፥፬–፰)።

ሐዋርያትም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመነሣቱ «በኢየሱስ የሙታን ትንሣኤ» (የሐዋ.፬፥፪) በማለት ለመስበክ ችለዋል። ስለዚህ ትንሣኤ የአዲስ ዘመን ጅማሬ ነው። ትንሣኤ አምላካዊ ምሥጢር እንደ መሆኑ ሐዋርያትን በአንድነት አጽንቷቸዋል፤ እንዲሁም ሁሉም ክርስቲያኖች በአንድነት ለመሆን ሁል ጊዜ መታገል እንዳለባቸው ያመለክታል።

አሁን ዓለም አቀፋዊ ክርስቲያናዊ አንድነት (Ecumenism) ወደሚለው ወደ ሌላኛው የርእሳችን ክፍል እንሻገራለን። በመጀመሪያ ዓለም አቀፋዊ ክርስቲያናዊ አንድነት ማለት «አንድ ይሆኑ ዘንድ» (ዮሐ.፲፯፥፲፩) እንዳለው በክርስቲያኖች ዘንድ የሚታይ ወይም ተጨባጭ አንድነት ለማምጣት መፈለግ ማለት ነው። ይህም ልዩነቶችን ሁሉ ኋላ በመተው ሁሉም አማኞች ወደ አንድነት እንዲመለሱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው።

እስከ ኤፌሶን ጉባኤ (፬፻፴፩) ድረስ የዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ አንድነት ዓላማ የጌታችን ትምህርት መሠረቱን ሳይለቅ እንዲቆይና የቤተ ክርስቲያንን አንድነት መጠበቅ ነበር። ስለሆነም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረውና ሐዋርያት የሰበኩት ንጹሀ እምነትና እውነተኛው ወንጌል የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የሁላችን ቅዱሳን አባቶች በሆኑት ተጋድሎ ተጠብቋል። ከላይ እንደ ገለጽነው የቀደሙት ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ የአንድነት ጉባኤዎች ዋነኛ ተቀዳሚ ተግባር እውነተኛው ሐዋርያዊ እምነት ኦርቶዶክሳዊ ጠባዩን ሳይለቅ ማቈየት ነበር።



በየዘመናቱ በክርስቲያኖች መካከል አንድነትን ለማምጣት ሙከራዎች ተደርገዋል። ይሁን እንጂ ከ፳ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በተለያዩ የሃይማኖት ክፍሎች መካከል መሠረታዊውን የሃይማኖት ትምህርት ወይም ዶክትሪንን አስመልክቶ አንድ ዓይነት አመለካከት ወይም ስምምነት ባለመኖሩ አንድነት ሊገኝ አልቻለም። እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ ግን በመቻቻል አብሮ ለመሥራት ተችሏል። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አንድነትን አጥብቃ በመያዟና ለዚህም አበክራ ከመታገሏ የተነሳ ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ነበራት አሁንም አላት። በአሁኑ ጊዜ ያለው ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ አንድነት እንቅስቃሴ ግን በአብያተ ክርስቲያናት ወይም የሃይማኖት ክፍሎች መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ብቻ ያተኮረ ይመስላል። በዚህም ምክንያት አንዳንዶች የዛሬው ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ አንድነት እንቅስቃሴ ወይም ኢኩመኒዝም ለቤተ ክርስቲያን መለያየት ዋና ምክንያት የሆነውን ዶግማ ጉዳይ ቸል በማለት ይልቁንም አባልነትን ለማበራከት ይበልጥ የሚተጋ በተለይም ከማኅበራዊና ከፖለቲካዊ ጉዳዮች ጋር የበለጠ የተያያዘ ይመስላል ብለው የሚያስቡ አሉ። በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ መተባበርና ስለሰዎች ደህንነት መሥራት ድርቅ ባጠቃቸውና ጦርነት ባየለባቸው በርካታ አገሮች የሚሊዮኖችን ሕይወት ያዳነ እንዳ መሆኑ በራሱ ታላቅ ነገር ነው። በእውነቱ «እምነት ያለሥራ የሞተ» ስለሆነ (የዕ.፪፥፳) እምነትን መጠበቅ አስፈላጊ እንደ ሆነ ሁሉ ማኅበራዊ ሥራም ምግባረ ትሩፋት የክርስቲያን አንዱ ተቀዳሚ ሥራ ነው። ይሁን እንጂ መልካም ከመሥራት ጋር ነገሮችን በጥልቅ በማሰላሰል፤ በነገረ ክርስቶስና በምሥጢራት ረገድ ባለው ልዩነት እንዲሁም በሌሎች እንደ ቅሰጣ፤ የፖፑ የበላይነትና የአንዱን ሃይማኖታዊ ትውፊት በመውሰድ ተመሳስሎ እንደ መታየት ያሉትን (Uniatism) ሁኔታዎችን በማስወገድ መሠረታዊ የሃይማኖት ልዩነቶችን እስካልፈታን ድረስ ወደ ውህደት የሚያመራ እውነተኛ ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ አንድነት የሩቅ ሕልም እንደ ሆነ ይቀራል። በተለይ ለክርስትና የሥነ – መለኮት ትምህርት የማዕዘን ድንጋይ በሆኑት በነገረ ክርስቶስና በምሥጢራት ትምህርት ጥያቄ ላይ አንድ ዓይነት የሆነ አመለካከት እስካልኖረን ድረስ አንድነት ላይ መድረስ አይቻልም። ለእኛ ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማንያን ከመሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርት አንድነት ውጭ የክርስትና አንድነት ሊታሰብ አይችልም።

የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያኑ አገልጋዮች እንደ መሆናችን እውን የሆነው የቤተ ክርስቲያን አንድነት የምንመኘው ብቻ ሳይሆን በተግባር ሊገለጥ የሚችል እንደ ሆነ እናምናለን። እንደ መሆናችንም ሌላ ፈቃድ ሊኖረን አይችልም፤ አይገባምም። የርሱን ፈቃድ የመፈጸም ግዴታ አለብን። ተጨባጭ የቤተ ክርስቲያን አንድነትን ማምጣት የሚቻለው ክርስቶስ ባስተማረውና ሐዋርያት በሰበኩት መሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርት ወይም ዶክትሪን ላይ በሙሉ በማተኮር ለዚህም ካለመታከት ከልብ ለመሥራት ስንነሣሣ ብቻ ነው። ስለዚህም በመንፈስ ቅዱስ በመመራት የጥንቷ ቤተክርስቲያንና የቅዱሳን አባቶቻችን የቅድስና፣ የታላቅ ጽናትና የአንድነት ምልክት የሆነውን አንድነት በብርቱ ልንፈልግ ይገባል።

እግዚአብሔር ዓለማችንን ይባርክ
ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ

### ክፍል ሁለት

ውይይት አብሮ የመኖር ሥልጣኔን ይገነባል

ክቡር ሊቀ መንበር
የተከበራችሁ የጉባኤው ተሳታፊዎች
የተወደዳችሁ የባርሴሎና ከተማ ኗሪዎች

ከሁሉ አስቀድሜ በዚህ ዓለም አቀፍ የሰላም ስብሰባ እንድንሳተፍ ለቅዱስ ኤጂዲዮ ማኅበረሰብ ለጋበዙን ፕሬዚዳንት ለፕሮፌሰር አንድሪአ ሪካርድ እና ለአባላቱ ጥልቅ ምስጋናዩን አቀርባለሁ። ጥንታዊትና ታሪ



www.ethiopianorthodox.org

ካዊት የሆነችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንንና የ፸፰ ሚሊዮን የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰላምታ ለናንተ ሳቀርብ ታላቅ ደስታ ይሰማኛል። ይልቁንም ስለሰላም ለመወያየት በባርሴሎና በመገኘታችን በጣም ደስ ይለናል። በዚህች በከበረች ሰንበት ከቀትር በኋላ «ውይይት አብሮ የመኖር ሥልጣኔን ይገነባል» በሚል ርእስ በምናደርገው ውይይት ባጭሩ ሐሳቤን በመጠኑ አቀርባለሁ።

ውይይት የሰዎች ግንዛቤ መሠረታዊ መመሪያ ነው። ውይይት ከሌሎች ሰዎች ጋር ግንኙነትንና ስለ ነገሮች የተሻለ አመለካከትን ይፈጥራል። ሰፋ አድርገን ስንመለከተው የሰው ልጅ የአእምሮ ልቀት ፍሬ የሆኑት ዛሬ ሥልጣኔ የደረሰባቸው ሁሉ በአንድ መንገድም ሆነ በሌላ የውይይት ውጤት ናቸው።

እንደ እውነቱ ከሆነ ንግግር ወይም ውይይት ከማይለካው የእግዚአብሔር ጥበብ የፈለቀ አምላካዊ ግኝት ነው። እግዚአብሔር ሙሴን በሲና ተራራና በሕይወቱ ሁሉ በሞት እስከ ተለየበት ጊዜ ድረስ አናግሮታል። ይህም ንግግር መለኮታዊ ግኝት ለመሆኑ ዓይነተኛ ግልፅ ማስረጃ ነው። በደማስቆ መንገድ ወይም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ቅድስት ድንግል ማርያምን በሚያበሥራትና አስቀድሞም ለዘካርያስ በተገለጠለት ጊዜ ከፍተኛ ደረጃ ሰማያዊ ንግግር ሲደረግ እናያለን። በመሆኑም አምላካችንን የምናመሰግንበት፥ ይቅርታውን የምንለምንበትና በእያንዳንዱ አፍታ በረከቱን የምንጠይቅበት የዘወትር ጸሎታችንም ከእግዚአብሔር ጋር የምንነጋገርበት ነው። በእርግጥ ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቈጠረ ጀምሮ በዘመናቱ ሁሉ እግዚአብሔር በነቢያት፥ በሐዋርያትና በቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶች አማካኝነት ለሕዝቡ ተናግሯል። አሁንም ድረስ እንደ ፈቃዱ በመረጣቸው ላይ አድሮ ይናገራል። ይህ ሁሉ ንግግር በእርግጥ አምላካዊ ግኝት መሆኑንና ሁል ጊዜ በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ መብቀል የሚያስፈልገው መሆኑን ያሳያል። ኃያሉ አምላክ ከእኛ ከፍጥረቶቹ ጋር ከተነጋገረ ለሰው ልጅ በጎ ሕይወትና መልካም አኗኗር ሲባል እርስ በርስ መነጋገር መወያየት ምን ያህል ተገቢና ጠቃሚ ይሆን።

ስለዚህ በአጠቃላይ መንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ አብሮ የመኖር ይዘት የተመሠረተው በውይይት ላይ ነው። ኃጢአተኞች ንስሐ ሲገቡና ከአምላካቸው ጋር በምሕረቱ ሲታረቁ ንግግር ያደርጋሉ። ውይይት ወረትን የሚቀንስና መተማመንን፥ ወዳጅነትን፥ እርቅንና ዘላለማዊ ሰላምን እንደሚገነባ በአንጻሩ ደግሞ ጦርነት የሰው ልጅ ጥፋትና የንብረት መውደምን እንደሚያስከትል በፍጥጫና በመቆራቆስ ላይ ያሉ ክፍሎችና ቡድኖች ሁሉ ሊገነዘቡ ይግባል። አዋቂ አእምሮ ያለው የሰው ልጅ አስተዋይነት የጎደለው ባሕርይ ማሳየቱና እርስ በርስ መጠፋፋቱ የሚያሳዝን ነው። የሠለጠነው የሰው ልጅ አመለካከትና ዓለም አቀፋዊ የመንግሥታት ግንኙነት ሕግጋት የጠባይ ሕግ ግጭቶች በውይይትና በሰላም እንዲፈቱ ግድ ይላል።

ሰላም በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ዋጋ ያለው እንደመሆኑ በውይይት ልንሻው ይገባል። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና» (ማቴ.፭፥፱) በማለት ሰላምን መፈለግ በራሱ የተባረከ ቅዱስ ተግባር መሆኑን አረጋግጦልናል።

የሃይማኖት መሪዎችና ርእሳነ መንግሥታት እንደ መሆናችን በዓለማችን ያለ እያንዳንዱ ሰው ሰላምን የመከላከልና የመጠበቅ አስፈላጊነትን እንዲገነዘብ የማድረግ ከባድ ኃላፊነት አለብን። ሰላም ከጦር ሜዳ አይመረትም። በማናቸውም መልክ ቢሆን ከጦርነት አደባባይ የሚገኝ ነገር ቢኖር የእናቶች ዋይታ፥ ዕንባ፥ የሕፃናት ልቅሶ፥ እጅ እግራቸውን ያጡ ወገኖችና የአስከሬን ክምር ነው። በሁሉም አቅጣጫ ብንመዝነው ወደ ሰላም የሚያመራው ብቸኛው አስተማማኝ ጎዳና ውይይት ነው።

በተለይ አብርሃማዊ የአንድ አምላክ እምነት ተከታዮች የሚባሉ የዓለም ዓበይት ሃይማኖቶች ስለ ሰላም መወያየታቸው በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ዛሬ ዓለም በጦርነት እየጠፋች ነው። በመካከለኛው ምሥራቅ፥ በሌሎች የእስያ ክፍሎች በአፍሪካ፥ በአውሮፓና በመላው ዓለም በመስፋፋት ላይ ያለውን ጦርነት ስናስተውል ልባችን በኀዘን ይሸማቀቃል። እጅግ አደገኛ የሆነው ይህ ሁኔታ ይገታ ዘንድ የሃይማኖት ሰላማዊ ድምፅ ያሻል። በተለይ እኛ የሰላምን አምላክ ለመስበክና በሕዝቡ ልብና አእምሮ ውስጥ የሰላምን ፍቅር እንድናሳድር በራሱ በሰላም አምላክ በእግዚአብሔር ኃላፊነት የተሰጠን ነን። (ዕብ.፲፫፥፳) የሰላም አለቃ በሆነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተው ክርስትናም ሰላምን ተቀዳሚ አምላካዊ ጥሪ አድርጎ አበክሮ ያሳውቃል።


ሃይማኖት የሰላምን ጥያቄ ከማንሣት ጋር የዓለም ማኅበረሰብ መንፈሳዊ ሕይወት ይታደስ ዘንድ የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረግ አለበት። ዛሬ የቴክኖሎጂ ምጥቀትና የምድራዊ ምቾት ጉጉት መንፈሳዊ ባዶነትን በፈጠረበት በቁሳዊ ዓለም ታጠረናል። እንዲሁም ስስት፥ ጥላቻና ትርፍን ወይም ወረትን የማካበት የማያባራ ፍላጎት ማኅበራዊ ምድረ በዳ የገነነበት ቁሳዊ ኅብረተሰብ እየወለደ መጥቷል። ስለዚህ ጊዜ የማይገድባቸው የክርስቲያናዊ በጎ ምግባር መገለጫ የሆኑት ፍቅር፥ ልግስና፥ እምነት፥ ተካፍሎ የመኖርና የባልንጀራነት ስሜት በሰው ልቡና እንዲያንሰራራና እንዲታደስ ዘወትር መትጋት አለብን።

ይህ በሥራ እንዲገለጥ በተናጠል በሰዎች ግንኙነት፥ በአጠቃላይ ደግሞ በዓለም አቀፋዊ ግንኙነት ውስጥ ውይይት በእጅጉ የዕለት ተዕለት መሣሪያ መሆኑ መታወቅ አለበት። ምን ጊዜም ቢሆን አብሮ የመኖር ሥልጣኔ የሚገነባው በውይይት ነው። የሰው ልጆች ከልብ በውይይት እስካልተሳተፉ ድረስ እውነተኛ ሰላም በምድራችን ከቶውንም ሊሰፍን አይችልም።

እግዚአብሔር ዓለማችንን ይባርክ!

# እስመ ነገረ መስቀሉሰ ዕበድ ውእቱ በኀበ ኅጉላን ወበኀቤነሰ ለእለ ድኅነ ኃይለ እግዚአብሔር ውእቱ

ከአባ ገሪማ
የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽ/ቤት
የውጭ ግንኙነት የበላይ ኃላፊና የድሬዳዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ



«የመስቀሉ ቃል ወይንም የመስቀሉ ነገር ለሚጠፉት ሞኝነት፤ ለእኛ ለምንድነው ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና» ይላል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ (፩ኛ ቆሮ.፩፥፲፰)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የመስቀሉ ነገር የእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ እንደሆነ ያስተምረናል።

የመስቀሉ ነገር ሞኝነትና ኃይል በሆነላቸው ሰዎች መካከል እንደ መለኪያና መለያ ያለ ነገር ይሆናል ማለት ነው።

ለአይሁድ የመርገም፥ ለአሕዛብ አምላኪዎች የሞኝነት፥ ለክርስቶስ ወገኖች የእግዚአብሔር ኃይል የሆነውን የመስቀሉን ትርጉም ለማስተማር ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እስከ ቆሮንቶስ ድረስ ረጅም ሐዋርያዊ ጉዞ ያደረገው።

ኃይለ እግዚአብሔር የሆነው የመስቀሉ ታሪክ የተመሠረተው መጋቢት ፳፯ ቀን ፴፬ ዓመተ ምሕረት በማዕከለ ምድር ቀራንዮ ነው።

«እግዚአብሔርሰ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም፤ ወገብረ መድኀኒተ በማዕከለ ምድር...»

«እግዚአብሔር ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው፤ በምድር መካከልም መድኃኒትን አደረገ» ይላል ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት (መዝ. ፸፫፥፲፪)

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ማዕከለ ምድር ያለው ቀራንዮ ጎልጎታን ነው።

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የስቅለቱና የመቃብሩ ቦታ ቀራንዮ ጎልጎታ መባሉ ነው።

ይህም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጋቢት ፳፯ ቀን ፴፬ ዓመተ ምሕረት በዕለተ ዓርብ በዕፀ መስቀል የተሰቀለበት፥ በሥጋ የሞተበትና የተቀበረበት በይቀጥላልም ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር ውሎና አድሮ መጋቢት ፳፱ ቀን ፴፬ ዓመተ ምሕረት በዕለተ እሑድ የተነሣበት ነው።

ቀራንዮ ጎልጎታና የቀሩትም ቅዱሳት መካናት የተባሉት ሁሉ እስከ ታላቁ ቈስጠንጢኖስ መንግሥት ድረስ ማለት እስከ አራተኛው መቶ ዓመት ድረስ እንዴት እንደ ነበሩ መናገሩ ይከብዳል።

የክርስቶስ ቅዱስ መስቀል መጋቢት ፳፯ ቀን ፴፬ ዓ.ም በዕለተ ዓርብ ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ ድል የተነሣበት ሆነ። እንኳን አማናዊው የክርስቶስ መስቀል ይቅርና የእርሱ ምሳሌ የሆነው፤ ሙሴ ከእግዚአብሔር መመሪያ ተቀብሎ በምድረ በዳ የሰቀለው እርዌ ብርት እንኳ ሳይቀር ብዙ ተአምራትን ሠርቷል። እባብ የነደፈው እስራኤላዊ ሁሉ በእላግ ላይ የተሰቀለውን የናሱን እባብ በእምነት በተመለከተ ጊዜ ሕይወቱን አግኝቷል፤ ከደዌው ተፈውሷል፤ ከኀዘኑ ተጽናንቷል። (ዘኁ.፳፩፥፮-፱) ይህ የመስቀለ ክርስቶስ ምሳሌ የነበረው ነው፤ ይህን ያህል ተአምር የሠራው። ይሁንና ከላይ ከተጠቀሰው ዕለትና ዓመተ ምሕረት ወዲህ መስቀል የተፈተነ መድኃኒት በመሆኑ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በመስቀል ይመካል፤ መስቀልን ይሸከማል፤ በአንገቱም ያደርገዋል። ካህን የሆነው ሁሉም በእጁ ይይዘዋል። መስቀል ለመጀመሪያ ጊዜ በሰው እንገት ለመንጠልጠል የቻለው ታዳጊነቱ ከታወቀ ወዲህ ነው። እየቆየ ከመድኃኒትነቱ ኃይል ባይሻር ጌጥነትም ስለአለው ትንሹም ትልቁም፥ ወንዱም ሴቱም ያጌጥበት ጀመር። ሁሉም የመስቀልን ክብር፥ ኃይል ሲናገር መስቀል ኃይላችን ነው፤ መስቀል ገርማችን ነው፤ መስቀል ጽናችን ነው፤ መስቀል ታዳጊያችን ነው። እኛ በመስቀሉ ኃይል አምነናል፤ ያመነውም ሁሉ እንድናለን እያሉ ተአምራቱን ይናገራሉ፤ ክብሩንም ይገልጣሉ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ» ይላል (ገላትያ ፮፥፲፬)።







www.ethiopianorthodox.org

ይህ ከዚህ በላይ የሰማነው ትምህርት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በስህተት ትምህርት ሊተወናበዱት የገላትያ ሰዎች ትክክለኛውን የክርስትና እምነትና ሕይወት ለማሳወቅ መሆኑ ግልፅ ነው።

እኛም ስለነገረ መስቀሉ መናገር ያለብን በሐዋርያው በቅዱስ ጳውሎስ ዘይቤ መሆን አለበት።

ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቅሎበት የነበረው ዕፀ መስቀል አስደናቂዎች የሆኑ ተአምራትን ማድረግ ማለት ሙታንን ማስነሣት፤ ድውያንን መፈወስ፤ ዕውራንን ማብራትና እነዚህን የመሳሰሉ ተአምራት ሲፈጽም በመታየቱ ድኅነትን የሚፈልጉ ሕሙማን ሁሉ ቅዱስ መስቀሉን ለማግኘት መካነ መቃብሩን ሌሊትና ቀን ከበውት ይውሉና ያድሩ ነበር። ከዚህ የተነሣ አይሁድ ድርጊቱ አስቆጥቷቸው ጥልቅ ጉድጓድ አስቆፍረው እንዲዳፈን አደረጉ። ከዚህም ጋር ከከተማው ግዛት ጋር በመተባበር የከተማው ቆሻሻና ጥራጊ መስቀለ ክርስቶስ በተቀበረበት እንዲጣል አስወሰኑ። በዚህ የኢየሩሳሌም ከተማ ቆሻሻ በሚከማችበት ቦታ የመስቀሉን መቀበር አውቀው የመጡ ሕሙማን ሁሉ ከደዌአቸው ይፈወሱ እንደ ነበር ይተረካል። ከጊዜ በኋላም ወደዚያ ቦታ ማንም እንዳይደርስ በወታደር ይጠበቅ ጀመር። ትውልድ እያለፈ ትውልድ ሲተካ ከጊዜ ብዛት ያ ቦታ ለሁሉም ስውር ሆነ።

እንግዲህ ይህን በመሰለ ሁኔታ ከአንደኛው መቶ ዓመት እስከ አራተኛው መቶ ዓመት ድረስ የኢየሩሳሌም ከተማ ጥራጊ በአንድ ቦታ መጠራቀሙ ቦታውን የተለየ ኮረፍታ አድርጎት ይታይ ነበር።

የክርስትናው ታሪክ ከተመሠረተበት ከአንደኛው መቶ ዓመት ጀምሮ እስከ አራተኛው መቶ ዓመት ድረስ የነበረው ዘመን የተለያየ የታሪክ ክፍፍል ያለው ቢሆንም በአጠቃላይ ያ ክፍለ ጊዜ ለክርስቶስ ቤተሰብእ የሰማዕትነት ወይንም የቤተ ክርስቲያን የስደት ዘመን ነበር። ቤተ ክርስቲያን ሀብቷን፣ ንብረቷን፣ ቅርሷን፣ የተወደዱ ልጆቿን ያጣችው በዚያ ዘመን ነበርና ነው።

ቤተ ክርስቲያን ከቅዱሳን ሐዋርያት ጀምሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ የምታከብራቸው ቅዱሳን ሰማዕታት በነዚያ የከፉ ዘመናት ስለ ወንጌል መንግሥት ሰማያት ብለው በሰማዕትነት ያረፉና ያለፉ ናቸው።

ያ በክርስትናው ዓለም ክፉ አድራጊዎች አስከፊ ታሪክ የፈጸሙበት ማለት ከአንደኛው እስከ አራተኛው መቶ ዓመት የነበረው ጊዜ፤

- የሮማ ቄሣሮች ከመሳፍንቱ፣ ከመኳንንቱ ጋር በኮሎሲያ ስንነት ሁነው ክርስቲያኖችን ከሴመዱ አራዊት ጋር በሳቅ በስላቅ ያታገሉበት፤ ያስፈጁበት፤
- በክርስቲያኖች ሕይወት ላይ ዓፈና፣ ስቃይ፣ ግርፋት፣ ስቅላት፣ ግድያ የፈጸሙበት ነበር። የክርስቶስ ቤተ ሰቦች የሆኑት ሁሉ ሕይወታቸውን ለማትረፍ ሲሉ በገበበ ምድር ማለት በከርሠ ምድር ተዳፍነው ከሕያዋኑ በታች ከሙታኑ በላይ የሙታን ጎረቤቶች ሁነው የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት ያን የገበበ ምድር ሕይወት ይገፉት ነበር። በዚህ ሁኔታ ትውልድ እያለፈ ትውልድ እየተተካ በሞትና በሕይወት መካከል በመሆን ነው ከአራተኛው መቶ ዓመት ከታላቁ ቈስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት የደረሱት።

ይህ ክፍለ ዘመን ማለት አራተኛው መቶ ዓመት ለክርስትናው ታሪክ የነጻነት ጎሕ የቀደደበት ጊዜ ነበር።

ኢየሩሳሌም በሰባ ዓ.ም በጥጦስ ከጠፋች በኋላ ለአያሌ ዘመናት ያህል ጠፍ ሁና ስትኖር እንደ ምዕራባውያን ዘመን አቈጣጠር ታላቁ ቈስጠንጢኖስ በ፫፻፳ ዓ.ም ቅዱሳት መካናት በተባሉት ቦታዎች ሁሉ አብያተ ክርስቲያናትን ለማሠራት እንደ ተነሣና እናቱ እሌኒ ንግሥትም ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዛ የተቀደሱትን ቦታዎች ሁሉ ስትጠይቅ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የመቃብር ቦታ ጎልጎታንና መካነ ስቅለቱን ቀራንዮን ተግታ ትፈልግ ወይንም ታስፈልግ ነበር፤ ይህ ጥረቷም የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ መስቀል ለማግኘት ነበር። የንግሥት ዕሌኒ ረዳቶችም ታሪክ የሚያውቁ የአይሁድን ሥርዓትና ሕግ የተማሩ ሰዎችን ማግኘት አስፈላጊ መሆኑን ለንግሥቲቱ ሀሳብ ያቀርባሉ፤ በዚሁ መሠረት ሁለት ሰዎች ይገኛሉ።

እነዚህም ሰዎች ቅዱስ መስቀሉን በጎልጎታ ቀራንዮ ዙሪያ እንደሚያገኙት ተረድተው ማስቈፈር ይጀምራሉ። እነዚህ ሁለት ሰዎች የአይሁድን ሥርዓትና ሕግ ጠንቅቀው ያወቁ ናቸውና ለቁፋሮው ሥራ መነሻ ያደረጉት አሪት ዘዳግም ምዕራፍ ፳፩ ቁጥር ፳፪ንና ፳፫ትን ነበር። ይህም «አንድ ሰው በሠራው ወንጀል ምክንያት በስቅላት ቢቀጣ በተሰቀለበት ዕንጨት ላይ ሌሊቱን ሁሉ አይደር፤ በዚያኑ ዕለት ይቀበር፤ ምክንያቱም በዕንጨት ላይ ተሰቅሎ ያደረ በድን በምድሪቱ ላይ እግዚአብሔር አምላካችሁ የሰጣችሁን ምድር እንዳ ታረክሱ፤ አስከሬኑን ቅበሩ» የሚል ነው።

በዕንጨት ተሰቅሎ የሞተ ሰው ሬሳው አይደር ዕለቱን ይቀበር ተብሏልና በዚሁ ልማድ መሠረት አይሁድ ይህኑ ሥርዓት ይጠብቁ ነበርና በዕለተ ዓርብ የጌታ ሥጋና የሁለቱ ወንበዴዎች ሬሳ ተሰቅሎ እንዳያድር ወዲያውኑ ሳይመሽ ዕለቱን እንዲሞቱ ያልሞቱ ካሉ በቶሎ ጭናቸውን ተሰብሮ ከሞቱ በኋላ ከመስቀል አውርደው ሥርዓቱን ፈጽመው እንዲቀብሯቸው ጲላጦስ ያለመናል (ዮሐ.፲፱፥፴፩)።

እንደዚህ የተደረገው በዕንጨት ተሰቅሎ የሞተ ሁሉ የተረገመ ነው ተብሏልና ዕንጨቱም ጭምር እንደርኩስ ተቈጥሮ ሰው እንደ ይነካው ይቀብሩት ነበርና ነው።

በዚህም ምክንያት ዕሌኒ ንግሥት ያሠማራቻቸው ሁለት ሰዎች ልማዱን ተከትለው ተግተው በማስቆፈራቸው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ቅዱስ መስቀልና ሁለቱ ወንበዴዎች የተሰቀሉበት ዕንጨት ከቀራንዮ ጎልጎታ ወደ ምሥራቁ ሲል ፳ ክንድ በሚያህል ርቀት የውሀ ማጠራቀሚያ በሚመስል ጉድጓድ ተቀብረው ይገኛሉ። ከነዚህም ከሦስቱ አንዱ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል መሆኑ በተአምራት አድራጊነቱ ታውቋል።

፩. በጠና የታመመች ሴት መስቀሉን ብትነካው በመዳኗ፤

፪. ሙት በማስነሣቱ

በነዚህ ሁለት ተአምራት አድራጊነት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል መሆኑን ሁሉም አምነው ከዚህ የተነሣ እሌኒ ንግሥት በወርቅና በዕንቍ አስጊጣ ልጇ ቈስጠንጢኖስ በጎልጎታ ባሠራው ቤተ ክርስቲያን እንዲቀመጥ አድርጋለች።

በታላቁ ቈስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት ቅዱሳት መካናት በተባሉት ቦታዎች ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት ተሠርተውባቸው ነበር።

በዚህ ጊዜ ነው የታላቁ ንጉሠ ነገሥት የቈስጠንጢኖስ እናት ዕሌኒ ንግሥት ታላቅ ደስታ የተሰማት። ይኸውም፦

፩ኛ. የቢዛንታይን መንግሥት ንጉሠ ነገሥት የሆነው ልጇ ታላቁ ቈስጠንጢኖስ በቅድስት እናቱ እሌኒ ንግሥት ጥረትና ብርታት ከጊዜ በኋላ ክርስቶስን አምኖ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቆ የክርስቶስ ቤተ ሰብእ በመሆኑ፤

፪ኛ. ልጇ ታላቁ ቈስጠንጢኖስ መክሰምያኖስን ለመውጋት በተነሣ ጊዜ «በዝ ትእምርተ መስቀል ትመውዕ ፀረከ» «በዚህ የመስቀል ምልክት ጠላትህን ድል ትነሣለህ» የሚል ጽሑፍ በጸፍጸፈ ሰማይ ስላየ የጋሻውን የፈረስ የበቅሎውን መግሪያ ሁሉ የመስቀል ምልክት እንዲቀረፅበት አድርጎ ዘምቶ ጠላቱን ድል አድርጎ ተመልሷል።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አምልኮተ ጣዖት እየተዳከመ አምልኮተ እግዚአብሔር እየሰፋ እየዳበረ መጣ። ከታላቁ ቈስጠንጢኖስ ጀምሮ የነገሡት ሁሉ የመስቀልን ባንዲራ የሚያውለበልቡ ለክርስትናው ሃይማኖት የሚጋደሉና የሚያስቡ ሆኑ።

፫ኛ. ታላቁ ቈስጠንጢኖስ «ሃይማኖት የግል ነው ሀገር የጋራ ነው» በሚለው መርሕ መሠረት ለክርስቲያኖቹም ለሁሉም የአምልኮት ነፃነት ያወጀ ነው።

በዚያን ጊዜ ነው ያ ለሦስት መቶ ዘመን ያህል በክርስቲያኖች ላይ ይፈጸም የነበረው ሰቆቃ ዋይታ ያከተመው፤ ነፃነት የታወጀው፤ ሁሉም እኩልነትን ያገኘው።

ስለ ቅዱስ መስቀሉ መገኘት ቀደም ሲል ከተናገርነው የተለየ በሌላ አቅጣጫ የሚተረክ አለ።

በዚያን ጊዜ ነው ዕሌኒ ንግሥት ስዕለቷ ወደ ፍጻሜ መቃረቡን ተረድታ በፈቃደ እግዚአብሔር ብዙ ገንዘብ በመያዝ ሠራዊት አስከትላ ከቍስጥንጥንያ ወደ ኢየሩሳሌም የተጓዘችው። ዕሌኒ ንግሥት ኢየሩሳሌም እንደ ደረሰችም መስቀሉን ለማግኘት ከፍተኛ ችግር እንዳጋጠማትና ለችግሩ መፍትሔውን የሚሰጡ በዚያ አካባቢ ብዙ ዘመናትን ያሳለፉ ሽማግሌዎችን ማጠያየት መጀመሯን ታሪክ ያስተምረናል።

ዕሌኒ ንግሥት መስቀሉ የተዳፈነበትን ቦታ ለማግኘት በተለያየ ዘዴ ብዙ ጥረት ከአደረገች በኋላ ዕጣን አጢሳ እግዚአብሔርን በጸሎት ጠይቃ የዕጣኑ ጢስ ወደ ላይ ወጥቶ ተመልሶ መስቀሉ የተቀበረበትን ኮረፍታ በማመልከቱ ዕሌኒ ከዚህ አለ ማለቱ ነው ብላ አስቆፍራ መስቀሉን ማግኘቷ ይነገራል። ይህን ይዞ ነው ቅዱስ ያሬድ «ዘዕጣን አንፀረ፣ ሰገደ ጢስ በጎልጎታ ዘደፈኑ አይሁድ ዮም ተረክበ ዕፀ መስቀል» በማለት የጻፈው። (ድጓ)

ይህ ዘመን የአምልኮት ነፃነት የታወጀበት ነበርና ከሦስት መቶ ዘመን ጥፋት በኋላ መስቀለ ክርስቶስ በመገኘቱ መላዋ ኢየሩሳሌም ታላቅ ደስታን አደረገች ዕሌኒ ንግሥትም ያን ላደረገ እግዚአብሔር ምስጋናዋን አቀረበች። በታላቅ ክብርና ሥልፍም መስቀሉን ወደ ጎልጎታ እንዳስወሰደችው ይተረካል።

እናቱ ዕሌኒ ንግሥት የመስቀሉን መገኘት ተቀዳሚ ዜና አድርጋ በጊዜው በነበረው የመገናኛ ዘዴ ማለት በጊዜው በየተራራው ቃጤ ሮች በማስቀመጥ አንዱ ያንዱን የችቦ መብራት በማየት በዚህ ዓይነት ዕይታ የመስቀለ ክርስቶስ የመገኘቱ ዜና በቍስጥንጥንያ ለልጇ ደርሶ ነበርና ልጇ ታላቁ ቈስጠንጢኖስም ስለመስቀለ ክርስቶስ መገኘት ክብር በቍስጥንጥንያው ቤተ መንግሥት ታላቅ በዐልና ደስታ ማድረጉ ይተረካል።

እንግዲህ ዕሌኒ ንግሥት ያደረገችውን በመከተል እኛም ደመራ በመደመር፤ በደመራው ዙሪያ ካህናቱ ጸሎተ እኩቴት፤ ጸሎተ ምህላ በማድረስ፤ በመባረክ በይቀጥላልም ደመራውን በመለኮስ በየዓመቱ በዚህ ጊዜ በታላቅ ሥነ ሥርዓት በዐለ መስቀሉን እናከብረዋለን። በኢትዮጵያ የመስቀሉን በዐል የምናከብረው በዝናሙ ወራት መውጫ በመጸው መግቢያ አበቦች በሚፈነዱበት ለበዐል እከባበር አመች በሆነበት ጊዜ ነው።

መስቀሉ በተገኘ ጊዜ እሌኒ ንግሥት ተደስታ ወዲያውኑ የቤተ ክርስቲያኑን መሠረት በኢየሩሳሌም ማስጣሏና ታላቁ ቈስጠንጢኖስም የእናቱን ደስታ ለመካፈል ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዞ በዚያው እንዳለ በ፫፻፳፯ ዓ.ም እናቱ ዕሌኒ ንግሥት በ፹ ዓመቷ በዐረፈች ጊዜ ከፍ ባለ ክብር ዕንባውን እፍስሶ ዐሳርፏታል፤ በእምነቷ የጸናች የተቀደሰች እናት ነበረችና ነው። ከጊዜ በኋላም ዓፅሟን ከኢየሩሳሌም ወደ ቁስጥንጥንያ አስወስዶታል ይባላል። ይህም የቦታ ማበላለጥ ሳይሆን የቅድስት እናቱን ዓፅም በአጠገቡ ለማስቀመጥ መሆኑ ግልጥ ነው።

ይሁንና ከጊዜ በኋላ እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ፮፻፲፬ ዓ.ም ፋርሶች በኢየሩሳሌም ዘምተው በኢየሩሳሌም ከተማ የተገኘውን ሁሉ ፈጅተው ከሞት የተረፉትንም ማርከው ወደ ፋርስ ወስደዋል። አብያተ ክርስቲያናትንም በሙሉ አቃጥለዋል፤ የኢየሩሳሌም ከተማ ሀብት ንብረት ተወስዷል።

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ መስቀል በወርቅና በዕንቁ አጊጦ ሲያገኙት ከቀሩት ንዋያተ ቅድሳት ጋር ይዘው ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል።

በዚሁ በ፯ኛው መቶ ዓመት የቢዛንታይን ንጉሠ ነገሥት የነበረው ህርቃል ወደ ፋርስ ዘምቶ ጠላቶቹን አሸንፎ ቅዱስ መስቀሉን በማግኘት ቅዱስ መስቀሉን እስይዞ በመጀመሪያ ወደ ቍስጥንጥንያ ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም ሲደርስ የሁለቱም ከተሞች ሕዝብ ከደስታው ብዛት የተነሣ በነቂስ ከከተማዎቹ ወጥቶ በዕልልታ በሆታ በዝማሬ ችቦና ጧፍ በማብራት ለንጉሠ ነገሥቱና ለቅዱስ መስቀሉ የደመቀ አቀባበል ማድረጉን ታሪክ ይነግረናል።

የዚሁ የደመራ በዓላችን የታሪክ መታሰቢያ ከዕሌኒ ንግሥት ያገኘነው ትውፊት እንዳለ ሆኖ በሀገራችን በኢትዮጵያ በመስከረም ፲፮ ቀን ማታና ፲፯ ቀን ማለዳ ሕዝበ ክርስቲያኑ በየሀገሩ በየመንደሩ ችቦ እያቀጣጠለ የሚያበራውም ለንጉሠ ነገሥት ህርቃል አቀባበል ከታየው ድርጊት የተገኘ ውርስ ይመስላል። በሁለተኛ ደረጃም ንጉሠ ነገሥት ህርቃል ለመዝመት ወደ ፋርስ ሲነሣ ለሀገሩ፣ ለየአብያተ ክርስቲያናቱ አዋጅ ነገር ነበር፤ የአዋጁም ዓላማ በዘመቻው ድልን እንዲጎናጸፍና በደኅና እንዲመለስ ሁሉም ጾምና ጸሎት እንዲያደርግ ነበር።

እንግዲህ የጾመ ህርቃል አዋጅ መነሻ ሁኖ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጾመ ህርቃልን ዘወረደ የሚል ስያሜ በመስጠት የዓቢይ ጾም መነሻ ሕግ አድርጋ ስለጾመችው እስከዛሬ ድረስ ሳይረሳ ጾመ ህርቃል በማለት ትጾማለች፤ ይሁንና ይህን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቀር የሚጾመው የለም።

ሃይማኖት ነክ የሆነውን ሁሉ ሳናጠፋ አክብረን ይዘን በመገኘታችን በበለጠ የሚያኮራን ትውፊት ይሆናል።

በነገራችን ላይ ከጊዜ በኋላ የመስቀል ጦርነት መነሻዎች ከሆኑት አንዱ «ስለ መስቀለ ክርስቶስ ብላችሁ ወደ ኢየሩሳሌም ዝመቱና ቅድስት ሀገርን ነፃ አውጡ» የሚል ነበር። በዚህም መነሻ በመነኮሳት ስብከት አውሮፓውያን አንድ ሁነው ወደ ኢየሩሳሌም በብዙ ድካም በመጓዝ ቅድስት ሀገርን ነፃ አውጥተዋል። የመስቀል ጦርነት የተደጋገመ ታሪክ ያለው በመሆኑ ታሪኩን በዝግታ ማገበብ ያስፈልጋል።

ስለ መስቀሉ መገኘት ታሪክ ይህን ያህል ካልን በኋላ መስቀሉ ስለተገኘበት ጊዜና ቦታ ብዙ የሚባል አለና ስለሁኔታው እንደሚከተለው ለማለት እንሞክራለን።

ይህም መስከረም ፲፯ ቀንንና መጋቢት ፲ ቀንን በማቀናጀት የሚተረክ ነው። ያም ሆነ ይህ መስቀሉ የተገኘበት ዕለት ተብሎ ዓለም በየዓመቱ የሚያከብረው በመስከረም ወር ነው።

ስለዚህ እኛም እንደ ዓለሙ አሠራር ይኸውና በየዓመቱ መስከረም ፲፯ ቀን ከዋዜማው ከመስከረም ፲፮ ቀን ጀምረን በታላቅ ሥነ ሥርዓት ማለት ካህናቱ በዝማሬ ሕዝበ ክርስቲያኑ ትልቁም ትንሹም፤ ወንዱም ሴቱም በሆታ፤ በዕልልታ፤ ፀዐዳ በመልበስ አደይ አበባና መንሳነስ በመያዝ፤ ችቦ በማብራት፤ ደመራ በመለኮስ በታላቅ ሥነ ሥርዓት እናከብረዋለን።

ስለ ነገረ መስቀሉ ብዙ ተነግሯል፤ ብዙም ሰምተናል። ሰነፎች የመስቀሉን ነገር አይተውና ተመልክተው ታዳጊነቱ ስለ አስቈጣቸው ባንድ አልባሌ ቦታ ተጥሎ የጥራጊ መጣያ እንዲሆን አደረጉ። ክፉ አድራጊዎች ይህን ያደረጉት የመስቀሉን ታዳጊነት ያጠፉ መስሏቸው ነበር፤ ግን ሊያጠፉት አልቻሉም። እንዲያውም ነገረ መስቀሉ፤ ዜና መስቀሉ፤ ኃይለ መስቀሉ እየጎላ፤ እየሰፋ፤ እየዳበረ፤ እያደገ መጣ። የመስቀሉ ነገር በክርስቶስ ወገኖች ለውነት የተያዘ በመሆኑ ሰነፎች እንዳሰቡት ተዳፍኖ አልቀረም፤ ነገረ መስቀሉ ዘመን የማይሽረው፤ ጊዜ የማይለውጠው ነውና። ✣



www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ሃይማኖት

፩. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን በጻፈው ክታቡ (መልእክቱ) ክርስቶስ ታላቅ ሊቀ ካህናት ሆኖ ከካህናት ሁሉ እንደሚበልጥ በምዕራፍ ፩ እና ምዕራፍ ፲ ላይ በሰፊው ገልጾታል። በዚህ መነሻነት የኢየሱስ ክርስቶስ የሊቀ ካህናትነት ሥራ ምንድነው?

ከሌሎች ይበልጣል ያስባለውስ ምሥጢሩ እንዴት ነው? የኢየሱስ ክርስቶስ የሊቀ ካህናትነቱ አገልግሎት እንዴት ይፈጸማልን የሚል ጥያቄ መነሳቱ አስፈላጊ ይሆናል። ስለ ሆነም ይህን ሐተታ ዘርዘር አድርገን እንመልከት።

## የአሪት ሊቀ ካህናት

የኦሪቱ ሊቀ ካህናት አፍአዊ ኃጢአትን እንጂ ውስጣዊ ኃጢአትን አያስተሰርይም። መሥዋዕቱ የላም፣ የበግ፣ መሥዋዕት ነበረ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አማናዊ ሥጋውንና ደሙን ሰጠ እንጂ የላም፣ የበግ፣ የፍየል መሥዋዕት አድርጉ አላለም። መሥዋዕቱ ተለወጠ፤ ሊቀ ካህናቱ ተለወጠ፤ የኦሪት ሥርዓት ሁሉ በሐዲስ ሥርዓት ተለውጧል። በብሉይ ዘመን የነበሩ ሰዎች በጎ ቢሠሩም ወደ ሲኦል ይወርዱ ነበረ እንጂ ድኅነት አያገኙም ነበረ። ዛሬ ግን አምኖ ተጠምቆ በጎ ቢሠራ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባል እንጂ ወደ ሲኦል መውረድ የለም።

«እንክሰ ኢንወርድ ታሕተ አላፈድፋደ ንተልዎ ለዘፈጠረነ፣ ኅበ ቦአ ሐዋርያነ ህየ ንበውእ ኵልነ» እንግዲህስ ወደታች አንወርድም የፈጠረን መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ገባበት በፍጹም ተከትለነው ኹላችን እዚያ እንገባለን እንጂ» እንዳለ (ዮሐንስ አፈወርቅ)።

የብሉዩን ሊቀ ካህናት ለውጦ እሱ

## በብሉይና በሐዲስ ኪዳን የክህነት አገልግሎት

ከፈለገ ጥበብ መጽሔት ቁጥር ፱ የቀጠለ ነው።

ከየኔታ ገ/ሥላሴ አወቀ

ሊቀካህናት ሆኖ አስተማረ፣ ከእሱም በኋላ ደግሞ ወደ ሐዋርያት፣ ወደ ጳጳሳት፣ ወደ ሠለስቱ ምዕት፣ ከዚያም ወደ ሊቃውንት አስተላልፏል።

ከሌሎች ይበልጣል ያስባለውም ያ የብሉይ ሊቀ ካህናት ኃጢአት እንዲያስተሰርይ፣ በድንጋይ እንዳይ ወገር በዚህ ዓለም በእሳት እንዳይነድ ተብሎ ይከላከላል እንጂ ወደ ገሐነመ እሳት ከመውረድ አያድንም።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናትነት ግን ወደ መንግሥተ ሰማይ እንጂ ወደ ገሐነም አያወርድም። አማናዊ ሥጋውን፣ አማናዊ ደሙን፣ ሰጥቶ ወደ ሲኦል እንዳይሄድ ወደ ገነት እንዲገባ አድርጎታል።

በዚህ ክህነቱ በለጠ ታድያ መንግሥተ ሰማይ ሲያገባ በለጠ አይባልም? ያ ቁልቁል ወደ ሲኦል ነው የሚሄደው። የብሉይ ክህነት ልጅነትን አያሰጥም፣ ዛሬ ግን የአብ የወልድ፣ የመንፈስ ቅዱስ ልጅ ሆኖ ክፉ ካልሠራ በጎ ከሠራ መንግሥተ ሰማያት ይገባል።

## የኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናትነት አገልግሎት ምንድነው ቢባል?

ለሰው አብነት መሆን ነው «ወልደ እጓለ እመሕያውሰ ኢመጽአ ከመ ይትለአክዎ ዘእንበለ ዳዕሙ ከመ ይትለአክ» «የሰው ልጅ ሊያገለግል እንጂ ሊያገለግሉት አልመጣም» ይላል። የሐዋርያት እግር እያጠበ፣ ዓይን ለሌለው ዓይን እየሰጠ፣ እጅና እግር ለሌለው እጅ እግር እየሰጠ፣ ለተራቡት በአምስት እንጀራ እና በሁለት ዓሣ አምስት ሺህ ሰዎች መመገብ፣ በተረፈው ትርፍራፊ ደግሞ ድውያንን መፈወስ ነው።

ዓይን ላጣ ዓይንን መስጠት፣ እጅ እግር ላጣ እጅ እግርን መስጠት፣ ድውይን መፈወስ፣ሙትን ማሥነሣት ይኸ ሁሉ አገልግሎት ነው። ላገለግል ነው የመጣሁ አለ እንጂ፣ አገልግሉኝ አላለም። ልብስ አልብሱኝ፣ ምግብ አብሉኝ አላለም።



የብሉይ ሊቀ ካህናት አገልግሎትስ ምን ነበረ?

የብሉይ ሊቀ ካህናት ዝም ብሎ አሥራት፣ በኩራት፣ ቀዳሚያት ሲመጣለት ያንኑ እየተቀበለ ለቤተ ሰዎቹም ለሁሉም መተዳደሪያ ያደርግ ነበር። እርሻ፣ ቁፋሮ የለም፣ ወደ ሲኦል ከመውረድ አያድንም፤ ለራሱ ያጌጣል፣ ይጠቀማል እንጂ ወደ ሲኦል ከመውረድ አላዳነም። ምነው ቢሉ ካሣ አልተፈጸመም፣ አዳም ያስወሰደው ልጅነት አልተመለሰምና።

ጌታ ግን በዚህ ዓለም አብሉኝ፣ አጠጡኝ ሳይል አንድ ጊዜ ሰብአ ሰገል ያመጡለት ቀሚስ ለብሶ አደገ እንጂ አልብሱኝ አላለም።

የብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት አስራቱን በኩራቱን ቀዳሚያቱን እየተቀበለ ለራሱና ለቤተሰቡ መተዳደሪያ ያደርግ ነበር።

«አነ ክፍልከ ወአነ ርስትከ» «አሥራ አንዱ ነገድ ርስት ሲካፈሉ ነገደ ሌዊ ርስት አልተካፈሉም።» ለቤተ እግዚአብሔር የሚገባው ነበር ምግባቸውና ቀለባቸው፣ ጌታ ግን አብሉኝ፣ አጠጡኝ አላለም ሌላውን ኅብስት እያበረከተ ይመግባል እንጂ።

## የብሉይ ሊቀ ካህናት በቅድስትና በቅድስተ ቅዱሳን ሆኖ ይሠራው የነበረ

ሊቀ ካህናቱ በቅድስተ ቅዱሳን ገብቶ፣ «ተዘከር አብርሃምሃ፣ ይስሐቅሃ፣ ወያዕቆብሃ ዘመሐልከ ሎሙ በርእስከ» «አብርሃምን፣ ይስሐቅን፣ ያዕቆብን አስበህ ይቅር በለን» ድርቁን አርቅልን እያለ ይጸልያል።

ለሕዝቡ ደግሞ ሕዝበ እስራኤልን አሕዛብ እንዳያጠፏቸው ጠብቅልን፣ በዚህ ጊዜ ከኪሩብ ቃል ይመጣል «ኃጢአት አትስሩ፣ ጣዖት አታምልኩ፣ እኔ እጠብቃችኋለሁ ብሏል» ይላቸዋል። ያም እያስተላለፈ ወደ ሲኦል ከመውረድ አላዳነም። በቅድስተ ቅዱሳን ገብቶ ይሄን ይናገራል። በቅድስተ ቅዱሳን አሠርቱ ቃላት የተጻፈበት ጽላት አለ፤ ሥዕለ ኪሩብ አለ፤ ከዚያ ድምፅ ይሰማል ከዚያ ሰምቶ ድምፅ ያስተላልፋል። ይኸ ምሳሌ ነው እንጂ አማናዊ አይደለም። ጽላቱና ቅድስተ ቅዱሳን የእመቤታችን ምሳሌዎች ናቸው። ከኪሩብ የሚመጣው ቃል ደግሞ የሚካኤል እና የገብርኤል ነው። ገብርኤል ትወልጃለሽ ብሎ የተናገረው፣ ሚካኤል ደግሞ ጠባቂ ሆኖ የጠበቃት፣ በዚያ ምሳሌ ነው። የአዳም ልጆች ሲሞቱ ነቢያት ሲሞቱ እነ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ ሲሞቱ በሲኦል ነው የነበሩ። ዛሬ ግን አምኖ ተጠምቆ ምግባር፣ ትሩፋት ከሠራ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባል እንጂ ወደ ገሐነም አይወርድም። አማናዊው ሊቀ ካህናት ጌታ ተወልዶ፣ ተሰቅሎ አድኖታልና።

## በሐዲስ ኪዳን የሊቀ ካህናት አገልግሎት

በሐዲስ ኪዳን የሊቀ ካህናት አገልግሎትም ሕዝቡን ማስተማር፣ ማጥመቅ፣ መምከር፣ ንስሐን መስጠት፣ ሥጋውንና ደሙን ማቀበል፤ መናፍቃን ሲነሱ ጉባኤ አድርጎ መለየት ነው። ሊቀ ካህናት ሊሆን የሚገባው ምን ያሟላ ነው ቢባልም ሊቀ ካህናቱን የተካ ሊቀ ጳጳሱ ነው። ሃይማኖት እንዳይዛባ፣ የንስሐ ልጅ ሌላ ሃይማኖት እንዳይዝ መምከር፣ ማስተማር ነው። ለምሳሌ ባንዳንድ አካባቢ አምልኮ ባዕድ ያለው ሰው ዛፉን አምላክ ነው ብሎ ቅቤ ይቀባል፤ ግምጃ ይጠመጥማል። ያንን ማስተው። ያን ቢቀር ደግሞ የእመቤታችን በወር ዝክር ጎምቦ በጨርቅ ሸፍነው ተሸክመው ጃንጥላ ይዘው እንደታቦት አጅበው እልል እያሉ የሚሔዱትን ማስተው። ለድኃ ስጡ፣ አጠጡ አለ እንጂ ጎምበውን እንደ ታቦት አክብራችሁ እልል እያላችሁ ውሰዱ አላለም። የሊቀ ካህናት አገልግሎት መምከር፣ ማስተማር መገሰጽ ነው። ከመናፍቃን እገሌ ይወደኛል፣ እገሌ ይጠላኛል ብሎ ነገር የለም። እምቢ ሲል እያወገዘ መለየት ነው። ሐዋርያትኮ ሐራጻራግሞንን ከእነ ጭፍራው ነው በአውታረ ነፋስ የሰቀሉት። ✣



www.ethiopianorthodox.org

# ዘመነ ጽጌ

አባ ዘካርያስ የምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ



«በምድር ዘመን ሁሉ መዝራትና ማጨድ፣ ብርድና ሙቀት፣ በጋና ክረምት፣ ቀንና ሌሊት አያቋርጡም» (ዘፍ.፰፥፳፪)

በዚህ የኪዳን ቃል መሠረት እግዚአብሔር አምላክ የተለያዩ ክፍላተ ዘመናትን በከሃሊነቱ እያፈራረቀ ፍጥረቱን ሁሉ ይመግባል። ክፍላተ ዘመናቱም አራት ሲሆኑ መፀው፣ በጋ፣ ፀደይና ክረምት በመባል የሚታወቁት ናቸው።

በእነዚህም ወቅቶች እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተለያዩ አዳዲስ በረከቶችን ይሰጣል። የሰው ልጆችም ወቅቶችንና በረከቶችን በተመለከተ በየወቅቱ ልዩ ልዩ አዲስ ምስጋናን ለፈጣሪያቸው ለእግዚአብሔር ያቀርባሉ።

በእነዚህ በአራቱ ክፍላተ ዘመናት መካከል እንደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮት ሕግ ዐበይትና ንዑሳን የአገልግሎት ክፍላተ ዘመናት አሉ። ከዐበይት ክፍላተ ዘመንም አንድ ዐቢይ ክፍል «ዘመነ ጽጌ» ነው። ይህም ከመስከረም ሃያ ስድስት እስከ ኅዳር ስድስት ቀን ድረስ ያለው ስድስት ሱባዔ ነው። «ዘመነ ጽጌ» ማለትም የአበባ ወቅት ማለት እንደ ሆነ ግልፕ ነው። የዘመነ መፀው የመጀመሪያው ክፈል ነውና።

በዚህ በዘመነ ጽጌ እግዚአብሔር ሰማይን በከዋክብት፣ ምድርንም በልምላሜና በአበባ ማስጌጡ፣ ክርምቱ አልፎ አልፎ መፀው በመተካቱ፣ የተዘሩት አዝርዕትና የተተከሉት አትክልት በእግዚአብሔር መግቦት ለአበባና ለፍሬ መድረሳቸው እየታሰበ ምስጋና ለእግዚአብሔር ይቀርብበታል።

ዘመነ ጽጌ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመርዓዊ በጽጌና በመዓዛ ገነት እየተመሰለና የቅዱሳን መዓዛ እየተባለ የሚመሰገንበት ክፍለ ዘመን ነው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ደግሞ መርዓት ገነት፣ የገነት ተክልና ዐፀደ ወይን እንደሆነች የተነገረላት ምሳሌ እየተነበበ እየተተረጐመና እየተዘመረ ትምህርት የሚሰጥበትና ምስጋና የሚቀርብበት ነው።

በመሆኑም «መኀልየ መኀልይ» የተሰኘው መጽሐፈ ሰሎሞን በዚህ ወቅት በየሳምንቱ ቅዳሜ ከጸሎተ ቅዳሴ በፊት የቅዱስ ያሬድን ዜማ የመዘመር ችሎታ ባላቸው መዘምራን ይዘመራል። ከውስጡም እንደ ቅኔ ተቀምረው በቅዱስ ያሬድ የተዘጋጁት አሥራ ዘጠኝ ምቅናይ እጅግ ደስ በሚያሰኝ ጣዕመ ዜማ ይዘመራሉ፤ በኢትዮጵያዊ ንዋየ ማኅሌት ይዘመማሉ፤ ይጸነጸላሉ፤ ተጸፍተውም ይሸበሸባሉ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በዘመነ ጽጌ መኀልየ መኀልይ እንዲዘመር ማድረጓ በውስጡ የሚነጋገሩት እንደ ቅዱሳን ሐዋርያትና አበው ሊቃውንት አተረጓጐም ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን መሆናቸውን አምና ስለምታስተምር ነው። እንደ ገናም የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ትንቢትና ምሳሌ የተነገረበት መሆኑን አረጋግጣ ስለ ተቀበለች ነው።

ከዚህም ሁሉ ጋር ዘመነ ጽጌ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሕፃኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ይዛ ወደ ግብጽ መሰደድዋ በዚያም በእንግድነት በረኀብና በጥም መኖርዋ የሚታሰብበት ክፍለ ዘመን ነው። እመቤታችን በምድረ ግብጽ በስደት የኖረችው ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ሲሆን ከመስከረም ፳፮ እስከ ኅዳር ፮ ያሉት አርባው ቀናት የስደትዋ መታሰቢያ እንዲሆኑ ቅድስት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወስናለች።

በዚህም መሠረት በየሳምንቱ እሑድ ስደትዋንና ከስደት መመለስዋን የሚያስታውሰው ስለ እርስዋም፤

- የመፀው አበባ፤ በገነት አበባ፤
- የዳዊትና የሰሎሞን መንግሥት አበባ፤
- የአሮን የክህነቱ አበባ
- ገነተ ጽጌ ዘመነ ጽጌ
- አክሊለ ጽጌ፤ ዘመነ ፍሬ፤
- የትንቢት መኽሮ የቀናንሞስ አበባ
- የሽቶ ዕንጨት፤ የሽቶ መዓዛ፤
- የሮማን ሽቶ ጽጌ ረዳ ወዘተ...

እያለ ምሳሌዋን ከዘመነ ጽጌ ጋር የሚያስተባብረው «ማኅሌተ ጽጌ» የተሰኘው መዝሙር እየተዘመረ ለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ውዳሴና ምስጋና ይቀርባል።

በዘመነ ጽጌ ባሉት አምስት አንዳንዴም ስድስት እሑዶች የሚደርሰው ሥነ ማኅሌት ከምን ጊዜውም የበለጠ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ልጆች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን እጅግ ስለሚያፈቅሩ የዘመነ ጽጌ እሑድን በጣም ይናፍቃሉ።

በዘመነ ጽጌ እሑድ የማኅሌተ ጽጌን መዝሙር እያዳመጡ በቤተ ክርስቲያን የሚያድሩ ምእመናን ጥቂቶች አይደሉም። አንዳንዶችም እመቤታችን በስደትዋ ጊዜ የደረሰባትን ረኀብና ጥም፣ ችግርና ኀዘን ለማስታወስ እርባውን ቀናት በቤተ ክርስቲያን ትውፊታዊ ትእዛዝ ወይም ቀኖና ሳይሆን በራሳቸው ፈቃድ ይጾማሉ። ይህም ታላቅ በረከትን የሚያስገኝ ነው።

በያመቱ በዘመነ ጽጌ የሚታሰበው የጌታችንና የእመቤታችን ስደት ለምድረ አፍሪቃ ፍጹም በረከት ነው። ኢየሩሳሌም ባሳደደቻቸው ጊዜ አፍሪቃ ተቀብላቸዋለችና የቤተልሔምና የኢየሩሳሌም ሕዝብ ሊያስተናግዱአቸው ባልቻሉበት ጊዜ የአፍሪቃ ሕዝቦች አስተናግደዋቸዋልና።

ስለዚህም ምድረ አፍሪቃ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር በጌታችንና በእመቤታችን ኪደተ እግር ተባርካለች፤ ተቀድሳለችም። ባሁኑ ጊዜ ሌሎች ሀገሮች ይህ በረከት የተገኘበትን ታሪክ በአንዳንድ ተፅና ምክንያት በልዩ ሥነ በዓል ሊያስታውሱት ባይችሉም ኢትዮጵያና ግብጽ ግን ምንጊዜም አይረሱትም ይልቁንም በኢትዮጵያውያን ዘንድ በአጽንዖት ተጠብቆ ይኖራል። ✣

# ሥርዓተ ቤተክርስቲያን

## መግለጫ:- ይህ ጽሑፍ የቁርባን ነገር የሚነገርበት የትምህርት ዝግጅት ነው

ክብሩዕ አቡነ መርሐ ክርስቶስ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘመቀሌ

- ቁርባን የምንለው የክርስቶስ ሥጋውና ደሙ ነው።
- የክርስቶስ ሥጋውና ደሙ የዘላለም ሕይወት ሊኾን የተሰጠ ነው።
- ሥጋውን ደሙን የተቀበለ የዘላለም ሕይወት አለው። (ዮሐ.፮፥፶፫–፶፮ አንብቡ)

## ክፍል አንድ

## ዝርዝር ትምህርት

የክርስቶስ ሥጋውና ደሙ በምን ምክንያት ይገኛል?

የሚገኝበትስ በምን ቦታ ነው? ቢባል መልሱ በትምህርት ይሰጣል።

የክርስቶስ ሥጋውና ደሙ የሚገኝበት ቦታ በቤተ መቅደስ ነው። የሚገኝበትም ምክንያት በኅብስትና በወይን ነው።

በኅብስትና በወይን መገኘቱም እንዲህ ነው።

በቤተ መቅደስ ውስጥ መንበረ ታቦት አለ፤ ታቦቱ በመንበሩ ላይ ይኖራል። ጸሎተ ቅዳሴ በሚደረግበት ጊዜ፤ ወይም ቁርባን በሚደረግበት ጊዜ ቄሱ (ቀዳሹ ቄስ) ኅብስቱን በጻሕል፤ ወይኑን በጽዋዕ አድርጎ በታቦቱ ላይ ለእግዚአብሔር ያቀርበዋል። (እግዚአብሔር እንዲባርከው፣ እንዲቀድሰው) ነው።

በታቦቱ ላይ ያቀርብና «አሐዱ አብ ቅዱስ፣ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፣ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ» ብሎ ሃይማኖትን ይመሰክርበታል፤

ሕዝቡም (ምእመናኑ) የቀሲሱን ቃል ተከትለው

«በአማን አብ ቅዱስ፣ በአማን ወልድ ቅዱስ፣ በአማን ውእቱ መንፈስ ቅዱስ» ብለው ሃይማኖት ይመሰክሩበታል፤

## ምሥጢረ ቁርባን

ከዚህ አያይዞ ሙሉ ጸሎተ ቅዳሴ ይደረስበታል (ይጸለይበታል)።

በጸሎተ ቅዳሴው ውስጥ ቡራኬ የሚደረግበት ጸሎት አለ፣ ቄሱ እንደ ሥርዓቱ እየጸለየ በኅብስቱና በወይኑ ላይ ቡራኬ ያደርጋል፤ ጸሎተ ቅዳሴውንም ሲጸልይ፣

«አቤቱ ወደዚህ ኅብስትና ወደ ዚህ ወይን መንፈስ ቅዱስንና ኃይልን እንድትልክ እንለምንሃለን፣ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውንና ደሙን ያደርገው ዘንድ» የሚለውን ጸሎት እየጸለየ ቀዳሹ ኅብስቱንና ወይኑን ይባርካል፤ ይህን ጊዜ (ይህን በሚጸልይበት ጊዜ) በመንፈስ ቅዱስ ኃይል (በመንፈስ ቅዱስ ሥራ) ኅብስቱ የክርስቶስ ሥጋ፣ ወይኑ የክርስቶስ ደም ይኾናል፤

ይህም ጸሎት ይረስዮ ይባላል (ኅብስቱንና ወይኑን የክርስቶስ ሥጋውንና ደሙን ያድርገው፣ ማለት ነው) ይህም በቅዳሴ ሐዋርያትና በቅዳሴ እግዚእ ነው ያለው፤ በሌሎቹ ቅዳሴዎችም ይህን የመሰለ ጸሎት አለ፤

ከዚህ ቀጥሎ አያይዞ ቄሱ እየመራ፣ ሕዝቡ እየተከተለ «ሀበነ ንኅበር በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ ወፈውሰነ በዝንቱ ጽርስፎራ...» እያሉ ይጸልዩበታል፤

ቀጥሎ ጸሎተ ፈትቶ (እየቈረሱ የሚጸለይ) አለ፣ ቄሱ ያን እየጸለየ እንደ ሥርዓቱ ሥጋውን ይቈርሰዋል (ክፍል ክፍሉን ይከፋፍለዋል)።

ፍታቴውን ሲፈጽም ቄሱ እየመራ ሕዝቡ እየተቀበሉ አርባ አንድ ጊዜ እግዚኦታ (እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ) ያደርሱበታል።

ቀጥሎ ቄሱ «አአምን፣ አአምን፣ አአምን፣ ወእትአመን...እያለ ሥጋውን በደሙ» «ቡሩክ እግዚአብሔር አብ...ወብሩክ ወልድ ዋሕድ...ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ...» እያለ ደሙን በሥጋው ሦስት፣ ሦስት፣ ጊዜ ይባርከዋል። ከዚህ በኋላ በቅድሚያ ቀዳሾች ካህናት፣ ቀጥሎ ሕዝቡ በቄሱ እጅ እንቈርበዋለን (እንቀበለዋለን)።

ደሙን በጣት ለማቀበል ስለማይቻል በዕርፈ መስቀል እንቀበለዋለን። ማቀበያው በዕርፈ መስቀል ስለኾነ ደሙ በዲያቆኑ እጅ እንዲሰጥ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ያዝዛል።

የምንቀበለውም ሥጋውና ደሙ በዕለተ ዓርብ (የስቅለት ዕለት) ነፍስ የተለየው መለኮት ያልተለየው ነው። ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደው ነው ብትልም ይኾናል።



www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ሁለት

### ቁርባንን ማን እንደ ጀመረ ይቀርባል።

ቁርባንን በኅብስትና በወይን ማቅረብ የጀመረ ማን ነው?

ወይም ቁርባን በኅብስትና በወይን እንዲቀርብ ያዘዘ ማን ነው? ብንል መልሱ ለመጀመሪያ ቁርባንን በኅብስትና በወይን ምክንያት የሰጠ፣ ቁርባን በኅብስትና በወይን እንዲቀርብ ያዘዘ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ትምህርቱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርቱ ዘመናት ሲያስትምር «ከሰማይ የወረደ ሕያው ኅብስት (እንጀራ) እኔ ነኝ ከዚህ እንጀራ የሚ በላ ለዘላለም ሕያው – ይኾናል፣ ለዘላለም ሕይወት እኔ የምሰጠውም እንጀራ ሥጋዬ ነው። ሥጋዬን የበላ፣ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፣ እኔም በመጨረሻ ዕለት አስነ ሳዋለኹ። ሥጋዬ እውነተኛ የጽድቅ መብል ነውና ደሜም እውነተኛ የሕይወት መጠጥ ነውና፣ ሥጋዬን የበላ፣ ደሜን የጠጣ በእኔ ይኖራል፣ እኔም በእርሱ እኖራለሁ ሲል አስተምሯል።

ይህን ትምህርት በወንጌለ ዮሐንስ እናገኘዋለን። (ዮሐ.፮፥፶፩ እና ቁጥር ፶፬–፶፮)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መዋዕለ ትምህርቱን አስተምሮ ሲፈጽም ለመ ድኃኒተ ዓለም ዓርብ ዕለት ሊሰቀል ሐሙስ ማታ ከመያዙ በፊት ባንድ በደገኛ ሰው ቤት ልዩ አዳራሽ ተዘጋጅ ቶለት ገብቶ ለእራት ተገኘ፣ በዚያ ተገኝቶ በኦሪቱ ሕግ ለደቀመዛሙርቱ የፋሲካን መሥዋዕት አደረገ (ሉቃ. ፳፪፥፯–፲፰)።

በዚያን ጊዜ ለፋሲካ ካቀረበው አንዱን ኅብስት አንሥቶ ያዘና ጸለየ፣ ጸለየና ባርኮ ቈርሶ «እንኩ ብሉ ይህ ስለ እናንተ የሚሰጥ ሥጋዬ ነው» ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው።

እንዲሁም ወይኑን በጽዋ ይዞ ጸሊዮ ባርኮ «እንኩ ኹላችኹ ከዚህ ጠጡ፣ ይህ ጽዋ ስለ እናንተ እና ስለብዙ ሰዎች ለኃጢአት ሥርየት (ኃጢአትን ለማጥፋት) የሚፈስ ያዲስ ኪዳን ደሜ ነው» ብሎ ሰጣቸው፣ ሰጣቸውና መታሰቢያዬን እንዲህ አድርጉ» ብሏቸዋል።

ይህን ትምህርት በወንጌል ተጽፎ እናገኘዋለን (ማቴ.፳፮፥፳፮–፳፯፤ ማር.፲፬፥፳፪–፳፬፤ ሉቃ.፳፪፥፲፱–፳)። ደቀ መዛሙርቱም (ሐዋርያትም) ጌታ ባሳያቸውና «መታሰቢያዬን እንዲህ አድርጉ» ብሎ ባዘዛቸው መሠረት ባስተማሩበት ቦታ ኹሉ ቁርባንን በኅብስትና በወይን ያቀርቡ ነበር። ለዚህም (፩ቆሮ.፲፥፲፮ና ምዕ.፲፩፥፳፫–፳፮) ተመልከቱ።

ሐዋርያት ለቤተ ክርስቲያንም ቁርባን በኅብስትና በወይን እንዲኾን በሲኖዶሳቸው አስተላልፈዋል።

ጥቅስ «ወኢያዕርጉ ላዕለ ምሥዋዕ ዘእንበለ ኅብስተ ስርናይ ንጹህ ወማየ ወይን ንጹህ» ማለት «ከንጹህ ከስንዴ ኅብስትና ከንጹህ ከወይን ውኃ በቀር ሌላ አያቅርቡ በመሥዋዕ ላይ» ፍትሕ መንፈሳዊ ጴጥ ረስጠጅ ፫ (ጴጥ ማለት ጴጥሮስ አለ፣ ለማለት ነው፣ «ረስጠጅ» ሦስተኛ ሲኖዶስ ለማለት ነው)

ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን ቁርባን በኅብስትና በወይን መቅረቡ ትምህርቱን ከዚህ በላይ እንዳወሳነው ጌታ ባደረገው፣ መታሰቢያዬን እንዲህ አድርጉ፣ ባለው እና በሐዋርያት ትምህርት መሠረት ነው።

ስለ ቁርባን ከሃይማኖተ አበውም እንጠቅሳለን። የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት አትናቴዎስ ስለ ቁርባን እምነት የተናገረው እንዲህ ይላል።

«ደግሞ እናምናለን በቅዱስ ቁርባን፤ ሕይወት የሚኾን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም እንደኾነ፣ ይኸውም ካህኑ ሳይቀድሰው (ሳያከብረው) ኅብስትና ወይን የነበረ፣ ካህን ሲቀድሰው ግን መንፈስ ቅዱስ እላዩ ላይ ይወርዳል፣ ኅብስትም ከመኾን የእግዚአብሔር ልጅ የአካላዊ ቃል እውነተኛ ሥጋ ወደመኾን ይለወጣል፣ እንዲሁም በጽዋ ያለው ወይንም ከወይንነት የወልደ እግዚአብሔር የአምላክ ደም ወደመኾን ይለወጣል ከሥጋው ጋር ሲዋሐድ ባለበት እያለ» ብሏል። ሃይማኖተ አበው ድርሳን ዘአትናቴዎስ ክፍል ፲፮። በእትሙ መጽሐፍ ምዕ. ፳፭ ገጽ ፹፯ ተመልከቱ።

ኅብስቱና ወይኑ የክርስቶስ ሥጋና ደም ሲኾን ተመሳሳይ ሁኔታ የለውም።

ለቁርባን በመንበረ ታቦት ላይ የሚቀርበው ኅብስትና ወይን የክርስቶስ የወልደ እግዚአብሔር ሥጋና ደም ሲኾን፣ ለአኳኑ ተለውጣ ጨው እንደኾነች እንደ ብእሲተ ሎጥ እና ተለውጦ ደም እንደኾነ እንደ ማየ ግብጽ አኳኋን አይታይም፣

እንደዚሁም ተለውጦ ወይን እንደ ኾነ እንደ ማየ ቃና አኳኋን አይ ታይም፣ በእነዚያ ኹኔታ አይመ ስልም፣ ከእነዚያ ኹኔታ ጋር አይነጻ ጸርም፤ (ዘፍ.፲፥፲፯ እና ፳፮፤ ዘጸ. ፯፥፲፯–፳፩፤ ዮሐ.፪፥፯–፲)።

ለቁርባን የሚኾነው ኅብስትና ወይን የሚዘጋጅበት ቦታ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ለቁርባን የምናደርገው ኅብስትና ወይንም በቤተ ክርስ ቲያን ቅጽር ግቢ በሚገኘው ቤተ ልሔም በሚባለው ቤት ውስጥ በካህ ናት ተልእኮ ነው የሚዘጋጀው፣ በውጪ የተሠራ ግን ለቁርባን አይሆንም።

## ክፍል ሦስት ክለሳ

ከዚህ ቀጥለን እስከዚህ የተነገ ረውን ትምህርት በጥያቄ መልክ እንከልሳለን።

፩. ቁርባን የምንድር ነው?

፪. የክርስቶስ ሥጋውና ደሙ የሚገኝበት ቦታ የት ነው?

፫. የምንቀበለው ሥጋውና ደሙ እንዴት ያለ ነው? (ኹኔታውን ግለጽ)

፬. ቁርባንን በኅብስትና በወይን ምክንያት ማቅረብ የጀመረ ማን ነው? መልሱን በታሪክ መልክ አቅርብ፣

፭. ሐዋርያት ቁርባንን በኅብስትና በወይን ምክንያት ያቀርቡ እንደ ነበር ማስረጃ ጥቀስ ከሐዲስ ኪዳን።

፮. ቁርባን በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የሚዘጋጀው በየት ቦታ ነው?

፯. በመንበረ ታቦት ለቁርባን የምናቀርበው ኅብስትና ወይን የክርስቶስ ሥጋና ደም ሲኾን ተመሳሳይ የሚኾ ነው አለ? ምንድር ነው?

መደምደሚያ ስለ ቁርባን በአጭ ርና በግልጽ ቃላት የተዘጋጀው አጭር ትምህርት በዚህ አለቀ። ✣

ክብር ይሁን ለእግዚአብሔር



# ባሕረ ሐሳባችን፣ ሐሳበ ቢዘን፣ ሐሳበ ጕንዳጕንዲ

/በመምህር ያሬድ ፈንታ ወልደ ዮሐንስ)



በዘመናት ውስጥ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ባሕረሐሳብን በተመለከተ ያሁኑ ጊዜ ትውልድ በቅጡ ሊያውቀው፣ ካህኑም ሆነ ምእመኑ ሊረዳው የሚገባው፣ ጥልቀት ያላቸውን የሐሳበ ዘመን ጥናቶች አካሂደዋል። የሐሳበ ዘመንን አወጣጥ፣ በተለያየ አቀራረብና መነሻ እነዚያ አርበኛ ሊቃውንት ሲራቀቁበትና ሲመራመሩበት ኖረው ለዛሬው ትውልድ አቈይተውታል። ጠቃሚነቱም ጥራትና ብቃቱም ወሰን እንደ ሌለው ካገር ቤትም ሆነ ከውጭ በመጡት ያጠኑት ምሁራን ያሰመሩበት ነጥብ ነው።

ቀደምት የባሕረ ሐሳብ ሊቃውንት ጥናት እንዲያደርጉ፣ በጽሑፍም ለትውልድ እንዲያስተሩ በቤተክህነትም ሆነ በቤተ መንግሥት ከፍተኛ የሆነ እገዛ ይደረግላቸው ነበር።

የሰለጠነ የመጠቀ ነው የተባለለት ያሁኑ ያለንበት ፳ኛው (፳፩ኛው ሴክል) (ምዕት) ለዚህ ባይታደልም እንኳ ለአብነት ይሆነን ዘንድ የ፲፯ኛውን ሴክል የባሕረሐሳብ ሊቃውንት ትጋትን እዚህ ላይ እናነሳለን።

በወርቃማ የባሕረ ሐሳብ ዘመን ነቱ በሚታወቀው በአፄ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ ዘመን የነበሩ በባሕረ ሐሳብ ሙያ የተራቀቁ ሊቃውንት (መጋቢ አዝማናትን) ሥርዓተ ዘመንን በተመለከተ ዘርዘር ያለ ጥናት ማድረጋቸው ይነገራል። ከዚህም የተነሣ ንጉሡ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትን በጣም ያከብሩ ነበርና ለሊቅነታቸው ክብር የወርቅ ጫማ እንዲያደርጉ ፈቅደውላቸው ነበር። የሊቃውንቱም ልብስ እንዳያድፍ በከተማው ዙሪያ እንዶድ በብዛት ማስተከላቸው፣ በዚያን ጊዜ አዳፋ ልብስ የሚለብስ እንደ ነውረኛ ይቆጠር እንደ ነበረ በታሪክ ተመዝግቧል። (ከአፄ ልብነድንግል እስከ አፄ ቴዎድሮስ ገጽ ፩፻፹፱) የሐሳበ ዘመኑ ጥናት የተደረገበት ጊዜ በ፲፮፻፸፯ ዓ.ም አፄ ኢያሱ (ብርሃን ሰገድ) በነገሡ በ፫ኛው ዓመት እንደሆነ ይጠቀሳል። በዘመኑ የጎንደር ዘመን ሊቃውንት ጥናታቸውን ሲያካሂዱ ዓመተ ዓለምን በተለያየ ስልት ቢቈጥሩት፤

፩ኛ. በቀመረ ድሜጥሮስ ፯ ሺህ ፩፻፸፯ ዓ.ዓ

፪ኛ. በሐሳበ ሳቤላ ፯ ሺህ ፩፻፶፰ ዓመት፣

፫ኛ. በሐሳበ ቢዘን ፯ ሺህ ፱፻፸፱ ዓመት፣

፬ኛ. በሐሳበ ጕንዳጕንዲ ፯ ሺህ ፯፻፳፩ ዓመት፣

፭ኛ. በዓመተ ሰማዕታት (ሐሳበ ግብፅ) ፩ ሺህ ፬፻፩ ዓመት ኾኖላቸው።

በሊቃውንቱ የተደረገው ጥናት በመካከላቸው ያለውን ልዩነትና የዓመታቱን መብዛትና ማነስ ምክንያት እንዲህ ይመለከታል።

### ፩ኛ. ቀመረ ድሜጥሮስ

ቀመረ ድሜጥሮስ ዓመተ ዓለምን በዐቢይ ቀመርና በንኡስ ቀመር እየቀመረ የሚቈጥር የቀመር ሥርዓት ነው። ዐቢይ ቀመር ማለት ፭፻፴፪ ዓመት ነው።

ንዑስ ቀመር ማለትም ፲፱ ዓመት ነው። ጥንተ ቀመሩን ማከሰኞ፣ ወንጌላዊውን ማቴዎስ በማድረግ ቀመሩን ይጀምራል። ሠሉስ ማቴዎስ እንዲል (መርሐ ዕውር) ፯ ሺህ ፩፻፸፯ ዓመተ ዓለም በዐቢይ ቀመር ሲቀመር ፲፫ ዐቢይ ቀመር ኹኖ ፪፻፳፩ ዓመተ ቀመር ይተርፋል። ይህ የጥናት ውጤት የሚገኘው ከጥንተ ቀመር ከማክሰኞ ጀምሮ ሲቈጠር ነው።

### ፪ኛ. ሐሳበ ሳቤላ

ሐሳበ ሳቤላ ከ፲፬ኛው ዐቢይ ቀመር አንዱን ንኡስ ቀመር ወደ ኋላ ትቶ ከ፪ኛው ንኡስ ቀመር ከ፳ኛው ዓመተ ቀመር ቀመሩን ይጀምራል። ጥንተ ቀመሩ ዓርብ፣ ወንጌላዊው ዮሐንስ ነው። ምክንያቱም ዓርብ አዳም የተፈጠረባት ዕለት ስለሆነች፣ ዮሐንስ አስቀድሞ «ቃል ነበር» ብሎ ያስተማረ ወንጌላዊ ስለሆነ ስለዚህ ሐሳበ ሳቤላ እነዚህ ሁለቱ ምሥጢራት በሚገኙበት ርእሰ አንቀጽ የተጀመረ የቀመር ሥርዓት ነው ብለው፣ የሐሳበ ዘመን ሊቃውንት ያትታሉ። ፯ ሺህ ፩፻፶፰ ዓመት ዐቢይ ቀመር ሲቀመር ፲፫ኛ ዐቢይ ቀመር ሆኖ ፪፻፵፪ ዓመት ይተርፋል። ሐሳበ ሳቤላ ፲፱ኙን ዓመት ትቶ በ፳ኛው ዓመተ ቀመር ቀመሩን ይጀምራል የተባለው ስለዚህ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

## ፫ኛ. ሐሳበ ቢዘን

ሐሳበ ቢዘን ከ፲፩ኛው ዐቢይ ቀመር ፲፪ቱን ንዑስ ቀመር ወደኋላ ትቶ ከ፲፫ኛው ንዑስ ቀመር ከ፪፻፳፱ ዓመተ ቀመር፣ ቀመሩን ይጀምራል። ጥንተ ቀመሩ እሑድ፣ ወንጌላዊው ማቴዎስ ነው። ምክንያቱም የቢዘን ሊቃውንት እሑድ ዓለም የተፈጠረባት የሰባቱ ዕለታት ጥንት ስለ ሆነች፤ ማቴዎስም የወንጌላውያን በኩር ስለሆነ ነው። ስለዚህ ሐሳበ ቢዘን እነዚህ ሁለቱ ምሥጢራት በሚገኙበት ርእሰ አንቀጽ የተጀመረ የቀመር ሥርዓት ነው ብለው ሊቃውንቱ ያትታሉ። ፯ ሺህ ፱፻፺፱ ዓመት በዐቢይ ቀመር ሲቀመር ፲፫ ዐቢይ ቀመር ሆኖ ፴፫ ዓመት ይተርፋል። ሐሳበ ቢዘን ፲፪ቱን ንዑስ ቀመር ትቶ በ፪፻፳፱ ዓመተ ቀመር፣ ቀመሩን ይጀምራል የተባለው ስለዚህ ነው።

## ፬ኛ. ሐሳበ ጉንዳጉንዲ

ሐሳበ ጉንዳጉንዲ ከ፲፫ኛው ዐቢይ ቀመር ፳፬ቱን ንኡስ ቀመር ወደኋላ ትቶ፣ ከ፳፭ኛው ንኡስ ቀመር ከ፬፻፶፯ ዓመተ ቀመር፣ ቀመሩን ይጀምራል። ጥንተ ቀመሩ ዓርብ፣ ወንጌላዊው ማቴዎስ ነው። ምክንያቱም የጉንዳ ጉንዲ ሊቃውንት ዓርብ አዳም የተፈጠረባት፣ ከአዳም ጀምሮ የአበው ዕድሜ የሚቈጠርባት ዕለት ስለሆነች፣ ማቴዎስም የወንጌላዊያን መነሻና ጥንት ስለሆነ ነው። ስለዚህ ሐሳበ ጉንዳጉንዲ እነዚህ ሁለቱ ምሥጢራት በሚገኙበት ርእሰ አንቀጽ የተጀመረ የቀመር ሥርዓት ነው። ፯ ሺህ ፯፻፳፩ ዓመት በዐቢይ ቀመር ሲቀመር ፲፪ ቀመር ኾኖ ፫፻፷፯ ዓመት ይተርፋል። ሐሳበ ጉንዳጉንዲ ፳፬ቱን ንዑስ ቀመር ወደኋላው ትቶ በ፬፻፶፯ ዓመተ ቀመር ቀመሩን ይጀምራል የተባለው ስለዚህ ነው።

የእነዚህ አቅማራት መገኛ እንደ ሆኑ የተመረጡት ዕለታትና ወንጌላውያን የሚነሡት ከአልቦ ስለሆነ ሥርዓተ ቀመራቸው አይፋለስም። ዋናው የቀመር ሥርዓት ከአልቦ እየተነሣ በየ፲፱ኙ ዓመት የሚመላለስ ነው። ይህ ሥርዓተ ቀመር አይለ ወጥም። አይፋለስም። ከፍጥረተ ዓለም እስከ ኅልፈተ ዓለም ሲመላለስ ይኖራል።

ክብር ምስጋና ይግባቸውና ሐሳበ ቢዘን የሚባለውን ሥርዓተ ቀመር የፈለሰፉ በታላቁ ገዳም በደብረ ቢዘን ይኖሩ የነበሩ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ናቸው። ይህ ገዳም የሚገኘው በሰሜን ኢትዮጵያ ያን ጊዜ ሐማሴን ይባል በነበረው ክፍለ ሀገር ነው።

ሐሳበ ጉንዳ ጉንዲ የሚባለውን ሥርዓተ ቀመር የፈለሰፉ ሊቃውንትም ክብር ምስጋና ይግባቸውና በታላቁ ገዳም በጉንዳ ጉንዲ ይኖሩ የነበሩ ናቸው። ይህ ገዳም የሚገኘው በትግራይ ምሥራቅ ዓጋሜ በሚባለው አውራጃ ነው። በዘመናችን ግን እነዚህ ገዳማት ስም ብቻ ይዘው ቀርተዋል። ቀመራቸውም አልቦ!! ብቻ ኹኖአል።

## ፭ኛ. ዓመተ ሰማዕታት

ዓመተ ሰማዕታት ወይም ሐሳበ ግብጻውያን የሚባለው የዘመን አቈጣጠር ሥርዓትም፣ ፩ ሺህ ፬፻ ዓመት እንደኾነ ሊቃውንቱ በጥናታቸው ገልፀውታል። ይኸውም ዲዮቅል ጥያኖስ ከነገሠባት ዓመት እስከ አፄ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ ዘመነ መንግሥት ያለውን ጊዜ የሚያመለክት ነው። ዓመተ ሰማዕታት ከ፯ ሺህ ፩፻፸፯ ዓመተ ዓለም ፭ ሺህ ፯፻፸፮ ዓመትን ወደኋላ ትቶ ቀመሩን ይጀምራል። ጥንተ ቀመሩ ዓርብ፣ ወንጌላዊው ማቴዎስ ነው ምክንያቱም «አብያተ ክርስቲያናት ይትዐጸዋ አብያተ ጣዖታት ይትረኃዋ» አብያተ ክርስቲያናት ይዘጉ የጣዖቶች ቤቶች ይከፈቱ ብሎ ዲዮ ቅልጥያኖስ ያወጀባት፣ እነ ቅዱስ ጊዮርጊስም በሰማዕትነት የሞቱባት ዕለት ስለሆነች ነው። ስለዚህ ዓመተ ሰማዕታት ይህን ሁሉ ግፍ በክርስትያኖች ላይ የፈጸመ ከሐዲ ንጉሥ በነገሠባት ታሪካዊት ቀን ዓርብ የተጀመረ የቀመር ሥርዓት ነው ብለው መምህራን ያስረዳሉ። ፩ ሺህ ፬፻ ዓመት በዐቢይ ቀመር ሲቀመር ፪ ዐቢይ ቀመር ሆኖ ፫፻፸፯ ዓመት ይተርፋል። ዓመተ ሰማዕታት ፭ ሺህ ፯፻፸፮ ዓመተ ዓለምን ትቶ ቀመሩን ይጀምራል የተባለው ስለዚህ ነው። ከዚህ ቀጥሎ በ፲፱፻፺፩ ዓመተ ምሕረት አጽዋማትና በዓላት የሚውልበትን ወርና ዕለት እንመለከታለን።

## አጽዋማትና በዓላት

ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያለው ዘመን ቢቈጠር ፯ ሺህ ፬፻፺፩ ዓመት ኾነ በዘመነ ማርቆስ ወንጌላዊ።

፯ ሺህ ፬፻፺፩ ዓመተ ዓለም በ፭፻፴፪ ዐቢይ ቀመርና በ፲፱ ንዑስ ቀመር ሲቀመር ፲፬ ዐቢይ ቀመር ፪ ንዑስ ቀመር ኹኖ ፭ ዓመተ ዓበቅቴ ይተርፋል። ከ፭ቱ ዓመተ አበቅቴ ፩ ሲቀነስ ፬ ወንበር ይገኛል። ጥንተ አበቅቴ ፲፩ ነው። ፬ ወንበር በ፲፩ ጥንተ አበቅቴ ተባዝቶ በ፴ ሲቀመር (፬X፲፩ ÷ ፴=፪) ፪ ወር ኹኖ ፲፬ አበቅቴ ይገኛል። ይህ የ፲፱፻፺፩ ዓ.ም አበቅቴ ነው።

## መጥቅዕ

ጥንተ መጥቅዕ ፲፱ ነው ፬ ወንበር በ፲፱ ጥንተ መጥቅዕ ተባዝቶ በ፴ ሲቀመር ፬X፲፱÷፴= ፬ ወር ኹኖ ፲፫ መጥቅዕ ይገኛል። ይህ የ፲፱፻፺፩ ዓ.ም መጥቅዕ ነው።



## ወንጌላዊ

፯ ሺህ ፬፻፺፩ ዓመተ ዓለም ለ፬ቱ ወንጌላውያን ሲካፈል (፯ ሺህ ፬፻፺፩ ÷ ፬=፩ ሺህ ፰፻፸፪) ኾኖ ፫ ዓመት ይተርፋል። ለእያንዳንዱ ወንጌላዊ ፩ ሺህ ፰፻፸፪ ዓመት ደርሶ ፫ ዓመት ስለተረፈ የ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ወንጌላዊ ማርቆስ መሆኑ በዚህ ይታወቃል።

ወንጌላዊ በዓመት ጳጕሜን በዕለት ድርሻቸው አንድ ነውና የ፮ኛ ጳጕሜን ድርሻም እንደ አንድ ወንጌላዊ ፩ ሺህ ፰፻፸፪ ዕለት ነው፤ ስድስተኛዋ ጳጕሜን ሠግረ ዮሐንስ ትባላለች። አምስተኛ ጳጕሜንም ዕለተ ምርያ ተብላ ትጠራለች።

ዘመን ከተቈጠረ ጀምሮ የሠግረ ዮሐንስ ብዛት ፩ ሺህ ፰፻፸፪ ቀን ነው።
ዘመን ከተቈጠረ ጀምሮ የዕለተ ምርያ ብዛት ፯ ሺህ ፬፻፺፩ ቀን ነው።
የዕለት ድምር ፱ ሺህ ፫፻፷፫ ነው።

፱ ሺህ ፫፻፷፫ ቀን በሱባኤ ሲመደብ ፩ ሺህ ፫፻፴፯ ሱባኤ ዕለት ኾኖ ፬ ቀን ስለ ተረፈ፣

አሚሩ (፬) ጥንተ ቀመር (ማክሰኞ)

ሰቡዑ (፯) ጥንተ ዮን (ማክሰኞ)

ሠሉሱ (፫) ዕለተ ዮሐንስ (ማክሰኞ) ተብሎ ይታወሳል። ስለዚህ የ፲፱፻፺፩ ዓ.ም የመስከረም መባቻ ማክሰኞ መኾኑ በዚህ ይታወቃል።

በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም መስከረም ማክሰኞ፣ ጥቅምት ኀሙስ ይብታል። በዓለ መጥቅዕ ጥቅምት በባተ በ፲፫ኛው ቀን ማክሰኞ ይውላል። የማክሰኞ ተውሳክ ፭፣ በ፲፫ኛው መጥቅዕ ላይ ሲደመር (፭+፲፫) ፲፰ መባጃ ሐመር ይገኛል። ስለዚህ ጾመ ነነዌ የካቲት ፲፰ኛው ቀን ሰኞ ይገባል።

የበአተ ጾም ተውሳክ ፲፬ ነው፤ በ፲፰ ላይ ሲደመር ፴፪ ይሆናል። ፴ውን (ወር ብሎ) (ትቶ) ፪ ይይዛል ስለዚህ በአተ ጾም ሰኞ መጋቢት ፪ ቀን ይኾናል። የደብረ ዘይት ተውሳክ ፲፩ ነው። በ፲፰ ላይ ፲፩ ቢደምሩ (፲፰+፲፩)=፳፱ ይሆናል። በዓለ ደብረ ዘይት እሑድ መጋቢት ፳፱ ቀን ይውላል። የሆሣዕና ተውሳክ ፪ ነው በ፲፰ ላይ ፪ ቢያክሉ (፪+፲፰)=፳) ሃያ ይሆናል። ሆሣዕና እሑድ ሚያዝያ ፳ ቀን ይውላል። የስቅለት ተውሳክ ፯ ነው ፲፰ ላይ ፯ ቢያክሉ፤ (፯+፲፰ = ፳፭) ይሆናል። በዓለ ስቅለት ዓርብ ሚያዝያ ፳፭ ቀን ይውላል። የትንሣኤ ተውሳክ ፱ ነው በ፲፰ ላይ ፱ ቢታከል (፱+፲፰=፳፯) ይሆናል። በዓለ ትንሣኤ እሑድ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ይውላል። የርክበ ካህናት ተውሳክ ፫ ነው በ፲፰ ላይ ፫ ቢያክሉ (፫+፲፰= ፳፩) ይሆናል ርክበ ካህናት ሮብ ግንቦት ፳፩ ቀን ይውላል። የዕርገት ተውሳክ ፲፰ ነው በ፲፰ ላይ ፲፰ ቢያክሉ (፲፰+፲፰)=፴፮ ይሆናል። ፴ውን ወር ብሎ (ትቶ) ፮ ይይዛል። በዓለ ዕርገት ኀሙስ ሰኔ ፮ ቀን ይውላል። የጰራቅሊጦስ ተውሳክ ፳፰ ነው በ፲፰ ላይ ፳፰ (፳፰+፲፰)= ፵፮ ይሆናል። ፴ውን ወር ብሎ (ትቶ) ፲፮ ይይዟል። በዓለ ጰራቅሊጦስ እሑድ ሰኔ ፲፮ ቀን ይውላል። ጾመ ሐዋርያት ሰኔ ፲፯ ቀን ጾመ ድኅነት ሰኔ ፲፱ ቀን ይውላል።

የዘመነ ማርቆስ አጽዋማትና በዓላት አወጣጥ ሥርዓት ከዚህ ይፈጸማል። ሃሌ ሉያ በዘንዜከር ሐሳባተ ሕጉ ወትእዛዛቲሁ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዘ ሀሎነ በዘመነ ቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ ያብጽሐነ እስከ ዘመነ ቅዱስ ሉቃስ ዜናዊ በሰብዓ ወአርባዕቱ ምእት ተስዓ ወአርባዕቱ ዓመተ ዓለም፤ በኀምሳ ወኃምስቱ ምእት ዓመተ ኵነኔ፤ በዐሠርቱ ወተስዓቱ ምእት ተስዓ ወአርባዕቱ ዓመተ ምሕረት ዮም ሠረቀ ለነወርኃ መስከረም ቡሩክ ያብጽሐነ እስከ ወርኃ ጥቅምት። ቡሩክ ሰላመ እግዚአብሔር።

**ሃሌ ሉያ በዘንዜከር ሐሳባተ ሕጉ ወትእዛዛቲሁ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዘ ሀሎነ በዘመነ ቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ ያብጽሐነ እስከ ዘመነ ቅዱስ ሉቃስ ዜናዊ በሰብዓ ወአርባዕቱ ምእት ተስዓ ወአርባዕቱ ዓመተ ዓለም፤ በኀምሳ ወኃምስቱ ምእት ዓመተ ኵነኔ፤ በዐሠርቱ ወተስዓቱ ምእት ተስዓ ወአርባዕቱ ዓመተ ምሕረት ዮም ሠረቀ ለነወርኃ መስከረም ቡሩክ ያብጽሐነ እስከ ወርኃ ጥቅምት። ቡሩክ ሰላመ እግዚአብሔር።**

ዐሠሩ ወተስዑ (፲፱) ሠርቀሌሊት፤

እሥራ ወሠሉሱ(፳፫) ሠርቀ ወርኁ፤

አሚሩ (፩) ሠርቀ መዓልት

ሠሉሱ (፫) ጥንተ ዕለት

አሚሩ (፩) ጥንተ ቀመር

ሰቡዑ (፯) ጥንተዮን።

ኮነ በዛቲ ዕለት በሰላመ
እግዚአብሔር አሜን።

ዝ ጸሎት ይዕርግ በእንተ ስመ አብ
በእንተ ስመ ወልድ በእንተ ስመ
መንፈስ ቅዱስ አሜን።

ስብሐት ለአብ

አቡነ ዘበሰማያት

ይጸለያል እስከ መጨረሻው። ✣



www.ethiopianorthodox.org

# ኤች አይ ቪ ኤድስን እንዴት መከላከል ይቻላል?

ከመጋቢ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

ማንኛውንም አይነት በሽታ እንዴት መከላከል እንደሚቻል ትምህርትና ምክር ለመስጠት የሙያ ኃላፊነቱም መብቱና ግዴታውም ለጤና ባለሙያዎች እንደሆነ የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ ዛሬ መላውን የዓለምን ሕዝብና መንግሥታት፣ አብያተ ክርስቲያናትንና የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎችን በታላቅ ፍርሀትና ሥጋት ላይ የጣለው፣ እጅግ አስፈሪና አስደንጋጭ የሆነው፣ አብዛኛውን ጊዜ በጾታዊ ግንኙነት እንደሚተላለፍ የተረጋገጠው ኤች አይ ቪ ኤድስ ለጊዜው እንደ ሌላው በሽታ ሁሉ መከላከያም ሆነ ፈዋሽ መድኃኒት ያልተገኘለት በመሆኑ፣ ስለ በሽታው ሰፊም ሆነ መጠነኛ ግንዛቤ ያላቸው ሁሉ ከዚህ በሽታ እንዴት መከላከል እንደሚቻል ለቤተሰባቸውና ለጎረቤቶቻቸው፣ ለወዳጆቻቸውም ሁሉ መንገር ግድ እየሆነ መጥቶአል።

በዚህም መሠረት ይኸው አሰቃቂ በሽታ ከተከሠተበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ቀዳሚ ሐዋርያነት በሁሉም አህጉረ ስብከትዋ ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ በአርባ ሚሊዮን ለሚቈጠሩ ተከታዮችዋ ምእመናንና ለሌሎችም መዳን ለሚፈልጉ ሁሉ ሰፊ መግለጫና ትምህርት ሰጥታለች ባለማቋረጥም እየሰጠች ነው። ይልቁንም «ኦርቶዶክስ የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያ ማእከል» በቅዱስ አባታችን ከፍተኛ አርቆ አሳቢነት ተቋቁሞ የኤድስን ስርጭት ስለ መከላከልና ስለ ኤድስ ሕሙማን ምክረ ካህንና እንክብካቤ በሰፊው እየተሰጠ ነው።

የኤች አይ ቪ ኤድስ ከአንዱ ወደ ሌላው መተላለፊያ ምክንያቶች በርካታ እንደሆኑ የጤና ባለሙያዎች ሲናገሩ አንደኛውና ዋናው ሥነ ምግባራዊ ያልሆነ ጾታዊ ግንኙነት መሆኑን አረጋግጠዋል።

እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የሰው ዘርዕ ሥነ–ምግባር በጎደለው ጾታዊ ሕይወት ሳይሆን በቅዱስ ጋብቻ ሥርዓት እንዲበዛ ወስኖአል። ይህ የእግዚአብሔር ውሳኔ በተጣሰበት ጊዜ ሁሉ በዓለም ላይ ብዙ ጠንቅ ተከሥቷል። የሥነ ምግባር መድከም ሰውን እንደ እንስሳ ያደርገዋል። ሰው ከሥነ ምግባር ውጭ ሲሆን እግዚአብሔር የሰጠውን መልካሙን ስጦታ ሁሉ ያበላሻል። የእግዚአብሔርም ትልቁ ስጦታ ሕይወት ነው። ሰው ከእግዚአብሔር አመራር ውጭ ሲሆን ይህን ትልቅ ስጦታ ከንቱ ያደርጋል። እግዚአብሔር ግን ከእርሱ የተሰጠንን ሕይወት እንደሚገባ እንድንይዘው ይፈልጋል።

የሥነ–ምግባር ውድቀት፣ የነበረው የሕዝብ መልካም ሥርዓት መዛባትም በሀገርና በሕዝብ ላይ ከፍተኛ ችግርን እየፈጠረ ነው። ኤች አይ ቪ ኤድስም የዚሁ ውጤት እንደ ሆነ ይታመናል።

የዓለም የሥነ ፍጥረት ሊቃውንትና የጤና ባለሙያዎች በየጊዜው እየተሰበሰቡ መላውን የሰውን ዘርዕ ካስጨነቀው ፍርሀትና ሥጋት ነጻ የሚያደርግ መፍትሔ ለማግኘት እንደሚያወያዩ ሁል ጊዜ ይነገራል፤ ለጊዜው ባያገኙም አንድ ቀን በእግዚአብሔር ፈቃድ የተባለውን መፍትሔ እንደሚያገኙ የሁሉም ተስፋ ነው።

ይሁን እንጂ እያንዳንዱ ሰውስ በግሉ ምን አይነት እርምጃ መውሰድ አለበት?

የኤች አይ ቪ ኤድስን ስርጭት ስለመከላከል በየጊዜው የሚሰጡ ትእዛዛት በቁጥርም በዓይነትም የታወቁና የተለመዱ ቢሆኑም ያለመናቅና ማቃለል መስማቱና መጠበቁ ተገቢ ነው። ከእነዚህም ጥቂቶቹ:-

፩. ቅድመ ጋብቻ ከጾታዊ ግንኙነት መታቀብ፣ ይህ ትእዛዝ ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከል ብቻ የተሰጠ አይደለም፤ የብሉይና የሐዲስ ኪዳናት ትእዛዝ ነው፤ የነበረና ያለ ምንጊዜም መኖር የሚገባው ትእዛዝ ነው። ነገር ግን ሰዎች ይህን ትእዛዝ መፈጸም ባለመቻላችን ራሳችን በራሳችን ከባድ ችግርን እየፈጠርን ነው።

፪. ወንዱ ሌላዋን ሳያውቅ፣ ሴትዋም ሌላውን ሳታውቅ ቆይተው ከተጋቡ በኋላ መተማመን፣ እርሱ ለእርስዋ እርስዋም ለእርሱ ታማኝ በመሆን መኖር ያስፈልጋል።

፫. ሁለት ወይም ከዚህ በላይ ሚስቶችን የማኖር ልማድን ማቆም

ይህ ልማድ ያላቸው ሌሎች ቢሆኑም በአንዳንድ ብሔረ ሰብእ በክርስቲያኖች መካከልም ይታያል። ልዩ ስያሜም አለው «አንዲት የገጠር፣ ሁለተኛዋ የከተማ፣ ወይም አንዲት የውስጥ ሌላዋም የውጭ» በመባል ይታወቃል። እንደ ብልጽግና እንደ ታላቅ ሰውነትም እየተቈጠረ ነው ባለቅኔውም:-



«ለብእሲ ዋሕድ ሀለዋሁ፣
አንስትያ ዓለም ክልኤቲ፣
እስመ አሐቲ ዘውስጥ ወእንተ አፍአ አሐቲ»
«ለአንድ ሰው፣
ሁለት የዓለም ሴቶች አሉት፤

አንዲት የውስጥ አንዲቱም የውጭ ናትና» በማለት ያለውን ልማድ አንጸባርቋል።

ይህ ልማድ የክርስትና እምነት ሥርዓትን ፈጽሞ የሚፃረር ከመሆኑም ጋር ለበሽታው ስርጭት ከፈተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ስለሚችል ሊወገድ የሚገባው ባህል ነው።

፬. ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ ግንባዜን ማዳበር፣

ስለ ኤድስ ፈዋሽ መድኃኒት ገና ባለ መገኘቱ ጠቢባኑም መድኃኒቱን መቼ እንደሚያገኙ ባለመታወቁ «ዕድሜ ቀጥል ወይም የዕድሜ ማራዘሚያ የተባለውም የሥቃይ ማራዘሚያ በመሆኑ ለጊዜው ጤናማ እንደ ሆነ የሚመስለው ሁሉ የሌሎች መጥፎ ዕድል እንዳይገጥመው ይጠንቀቅ» ስለ በሽታው ያለውን ግንዛቤ ያሳድግ።

፭. «ትዳር ከሌላችሁ በትዳር እስከ ምትወሰኑ ወይም ትዳር ለመመሥረት ምን ጊዜም የማትፈልጉ ሴትኛ አዳሪዎችና የሴትኛ አዳሪዎች አጋሮች በሽታውን ሊከላከል ብቻ ባለው መሣሪያ ተጠቀሙ» የሚለው ምክር በቤተ ክርስቲያናችን ተቀባይነት የሌለውና የማይፈቀድ ነው። ምክንያቱም:-

- በጤና ባለሙያዎች እንደሚገለጠው መሣሪያው ፍጹም አስተማማኝ አይደለም፤
- ዝሙትን ያስፋፋል፤
- ኤድስን ለመከላከል የሚደረገውን ሩጫ ያሰናክላል
- እግዚአብሔር አክብሮ የፈጠረውን አካል ያዋርዳል።
- በንጽሕና በሕገ ተፈጥሮ ሊፈጸም የሚገባውን በቁሳዊ ነገር መጠቀም እግዚአብሔርን መቃወምና ማቃለል ነው።
- በእግዚአብሔር አርአያ የተፈጠሩ እኅቶችንና እናቶችን እንደ ግዑዝ ፍጥረት ማድረግ ነው።
- የሥነ–ተፋቅሮ ጉድለትም ያለበት ተግባር ነው።
- ስለዚህ ከሁሉም በላይ የኤድስ ፍቱን መድኃኒት ወንዶችና ሴቶች ወጣቶች ያገቡና ያላገቡም ሁሉ:-
- ሕገ እግዚአብሔርን መጠበቅ፤
- አንዱ በአንዲቱ፣ አንዲት በአንዱ መጽናት፤
- ወደ ብዙ ሴቶች የመሄድ ጠባይ ያላቸው ወንዶችና ወደ ብዙ ወንዶች የመሄድ ጠባይ ያላቸው ሴቶች በጠባያቸው ላይ ጽኑዕ ለውጥ ማድረግ፤
- በድንግልናዊ ሕይወት በንጽሕና በመቆየት ደማቸው ከኤች አይ ቪ ኤድስ ነጻ መሆኑን በማረጋገጥ ጋብቻን መመሥረት ነው።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በጥቅምት ወር ፲፱፻፺፪ ዓ.ም በአዲስ አበባ ስታዲዮም ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ መፍትሔ ምዕዳን ሲሰጡ:-

«በምእመናን ዘንድ ኤድስን ለመከላከል ፍቱን የሆነው ብቸኛው መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል መጠበቅ በቅድስና ሕይወት መመራት ነው። እግዚአብሔር አምላክ በደነገገው ሕግ መሠረት አንድ ወንድ በአንዲት ሴት፣ አንዲት ሴት በአንድ ወንድ ተወስነው በመተማመን መጽናት ነው፤ ሕይወትን በሥርዓት መምራት ኑሮን መልክ ማስያዝና ራስን ለሕገ እግዚአብሔር ማስገዛት ነው። በእግዚአብሔር አርአያ የተፈጠረ አስተዋይ ልቡና ያለው ሰው በደመ ነፍስ እንደሚመሩ እንስሳ ሊሆን አይገባውም» በማለት ያስተላለፉት መልእክት ሁል ጊዜ ልናስተውለውና ልንመራበት የሚገባ ነው የዛሬውም መልእክት ይኸው ነው።

በሥነ ምግባር ጉድለት በዓለም ላይ በየጊዜው ከሚከሠተው ችግር ሰዎች ማምለጥ እንዲችሉ እግዚአብሔር አምላክ በቅዱሳን መላእክት፣ ነቢያትና ሐዋርያት የሰጠው ታላቅ መመሪያና ትእዛዝ አለ፤ ዛሬም ትእዛዙ ሊደመጥና ተግባራዊ ሊሆን የሚገባው ነው።

በሰዶምና በገሞራ ላይ መቅሠፍት በወረደ ጊዜ ጻድቁ ሎጥ በቅዱሳን መላእክት «አድኅን ነፍሰከ» ራስህን አድን ተብሎ በተሰጠው ትእዛዝ በመጠቀም እርሱና ልጆቹ ከመቅሠፍቱ ሊድኑ ችለዋል። (ዘፍ.፲፱፥፲፯)

«ሞአብ ጠፋች፣ ልጆችዋ ጩኸትን አሰሙ። ልቅሶን እያለቀሱ ወጡ የጥፋትና የመባባት ጩኸትን ሰሙ ስለዚህ እናንተ ራሳችሁን አድኑ (አድኅኑ ነፍሰክሙ) (ኤር.፵፰፥፬–፮)

«ፃኡ እምባቢሎን ወአድኅኑ ነፍሰክሙ» «ከባቢሎን ውጡ ራሳችሁንም አድኑ» (ኤር.፶፩፥፮–፮) ባቢሎን የዝሙት የመከፋፈል ከሥነ ምግባር ውጭ ለሆነ ሕይወት ምሳሌ ናት ይህን የነቢዩን ትእዛዝ የሰሙ ሁሉ ድነዋል፤ ያልሰሙ ጠፍተዋል።

ቅዱስ ጴጥሮስም በበዓለ ኀምሳ ቀን በመንፈስ ቅዱስ ተመልቶ «አድኅኑ ነፍሰክሙ እም ዓለም እኩይ» «ከዚህ ክፉ ዓለም ራሳችሁን አድኑ» ሲል ተናግሯል።

ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው ራሱን ለማዳን ለእግዚአብሔር ትእዛዝ ተገዢ መሆን አለበት። ማዳን የእግዚአብሔር ነው ግን እያንዳንዱ ሰው ለመዳን ፈቃደኛ ዝግጁና ምቹ ሆኖ መገኘት አለበት።

አኰቴት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሜን! ✣



www.ethiopianorthodox.org

# መግረሬ ፀር

ይህ ዓምድ መናፍቃንንና አጽራረ ቤተክርስቲያንን የሚያጋልጡ ጽሑፎች የሚቀርቡበት፣ የእመቤታችን፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት፣ አማላጅነትና ተራዳኢነት የሚተነተንበት ስለሆነ መግረሬ ፀር ተባለ፡፡

## መንጋችንን ከተኵላ እንጠብቅ


ከሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ

የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ዋና ኃላፊ


መጻሕፍት ተኩላ ወይም ተኩላት እያሉ የሚገልጹአቸው፣ ዲያብሎስ በልባቸው አድሮ በፍኖተ ሰይጣን የሚጓዙ፣ እማኙን ከእምነት ወደ ክሕደት የሚነጥቁ መናፍቃንን ነው።

መናፍቅ ማለትም የሚከፍል፣ የሚሰነጥቅ፣ የሚለይ፣ ከአንድነት ይልቅ መለያየትን የሚመርጥ፣ የሚጠራጠር፣ የሚያጠራጥር፣ የሚክድ፣ የሚያስክድ፣ ሃይማኖቱ ሕፁፅ (ጐደሎ) ምሉእ ወይም ፍጹም ያልሆነ፣ ትክክል ያይደለ፣ በተሳሳተ አመለካከት የተሳሳተን መንገድ የሚከተል ማለት ነው።

የመናፍቅ መሠረታዊ ባሕርዩ ይኸው በመሆኑም፣ ምሥጢረ ተዋሕዶን ይከፍላል፣ ነገረ ሥጋዌን ይክዳል፤ (ክርስቶስን ይክዳል) ከእምነት ይልቅ ፍልስፍናን መከተል ይቀናዋል፤ በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ይጠራጠራል። ብሎም ይክዳል ያስክዳል። ጀፋን ይሆናል። በእምነት በመመራት ፈንታ በተጣበበ ነገር መጓዝን ይመርጣል። የመጻሕፍትን ገጸ ንባብ እያጣመመ ቃለ መጻሕፍትን እየቈነፀለ የመጻሕፍትን ትርጉም፣ በግል ፍላጐቱ ለግል ፍላጐቱ ይተረጉማል። መናፍቅ፣ ወይም ተጠራጣሪ፣ ኑፋቄን ጸንሶ፣ ክህደትን ይወልዳል። ክሕደት ከጥንተ ተፈጥሮ ታሪክ እንደምንርዳው፣ «እንፈጠርነኩሙ» ብሎ ክሕደትን ካመነጨ፣ የሐሰት አባት ከሆነ ከዲያብሎስ፣ በዘመነ ብሉይ፣ «እልቦ መጋቢ ወሠራዒ» ብሎ ከካደው ከቀዳማዊ ማኒ፣ በዘመነ ሐዲስ ፈጣሪውን አሳልፎ ከሸጠ ከይሁዳ፣ «ቃል ሥጋ ኮነ» ምትሐት ጽላሎት ብሎ ከካደው ዳግማዊ ማኒ፣ «ወልድ ፍጡር በባሕርየ መለኮቱ» ብሎ ከካደው አርዮስ እና ከመሳሰሉ የእግዚአብሔር ጠላቶች የዲያብሎስ የግብር ልጆችና ሠራዊት የመነጨ ሆኖ ሌሎቹ ከሐድያንም ከእነዚህ በግብር የሚወለዱ ናቸው።

ኑፋቄ፣ የኑፋቄ ምንጩ አላፊ ጠፊ ለሆነ መብል ብኩርናውን ከሸጠ ከዔሳው፣

በዘመነ ሐዋርያት ከነበሩ፣ ቢጽ ሐሳውያን፣ ከሰማሪያዊው ሲሞን መሠሪይ፣ ሥልጣን ሳይኖራቸው አጋንንትን ሊያስወጡ የሞከሩና አጋንንት ከተበረታቱባቸው ደቂቀ አስቄዋ፣ ግብ (ሐዋ.፰፣፲፰፣ ፲፭፣፩–፲፱፣ ፲፬–፲፯)። በአራተኛው ክፍለ ዘመን ቤተክርስቲያንን ሲያውኩ ከነበሩ እያሌ ንፉቃን፣ በዘመናችንም በዓለም ላይ እየተልከሰከሱ መንግሥተ ሰማያትን የሚያዘጉ፣ እነሱ ላይገቡ፣ የሚገቡትን ከመግባት የሚከለክሉ ግብዞች፣ የጽላት፣ የታሪክና የእምነት ቀሳጢዎች የሚፈጥሩት የጥፋት ጐዳና ነው።

ዲያብሎስ አዳምንና ሔዋንን እንዳሳተ ሁሉ፣ መናፍቃንም የሰውን ልብ እያወኩ ጠማማ ትምህርት በማምጣት ሰውን ከእውነተኛው ሃይማኖት የሚለዩ ናቸው። ለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ ለሚራራላቸው፣ ለሚፈራላቸው፣ እንደ ሕይወቱ ለሚጠብቃቸውና በመናፍቃን ተንኰል ተነጥቀው እንዳይጠፉ፣ ዘለዓለማዊ ሕይወት እንዳያጡ ለሚሳሳላቸው ምእመናን ወገኖቹ እንዲህ ሲል ጽፎአል።

«ወባሕቱ እፈርሕ ዮጊ ከመ አርዌ ምድር አስሐታ ለሔዋን በጕሕሉት እንዳዒ ለእመ ይማስን ልብክሙ እምየውሀቱ ወንጽሑ ለክርስቶስ፤...ነገር ግን ምናልባት የምድር እባብ ሔዋንን በተንኰል እንዳሳታት፣ እንጀ ልቡናችሁ ይለወጥ እንደሆን ብዩ እፈራለሁ፣ ክርስቶስ ከሚያድለው የውሀትና ንጽሕና ወጥቶ። ወደ እናንተ የሚመጣ ወደ አላስተማርናችሁ ወደ ሌላ ኢየሱስ የጠራችሁ ቢሆን ያልተቀበላችሁት የምትቀበሉት ሌላ መንፈስ ቢኖር፣ ያልተማራችሁት ሌላ ትምህርት ቢኖር ልትጠብቁን ይገባል።» (፪ኛቆሮ.፲፩፣፩–፱፣ ገላ.፩፣፰–፱)።

በዘመናችን እየታየ ያለው የመናፍቃን ችግር ይኸው ነው፤ ኢየሱስ ኢየሱስ በሚል ከንቱ ጩኸት ሰዎች መድኃኒታቸው ያልሆነ ሌላ ኢየሱስ እየተሰበከላቸው ብዙዎች ከእውነተኛው መንገድ ሲለዩ ይታያል። ያም የሚሆነው እውነት ሊመስል በሚችል ልዩ ልዩ ምልክት ነው። ስለዚህ ግን መጽሐፍ እንዲህ ብሎአል። «እስመ ሀለው ሐሳውያን ገብርተ ዐመፃ እለይትሜየኑ ወይትሜሰሉ ሐዋርያተ ክርስቶስ፤ ወዝኒ አኮ–ለ አንክሮ እስመ ለሊሁ ሰይጣን ይትሜሰል ከመልአከ ብርሃን። ወዝኒ ኢኮነ ዐቢየ ለእመ ይትሜሰሉ መላእክቲሁ ከመ መላእክተ ጽድቅ ወደኃሪቶሙሰ በከመ ምግባሮሙ። የሚተነኮሉ፣ ሐዋርያተ ክርስቶስ የሚመስሉ፣ ዐመፅን የሚያደርጉ ዋሾዎች አሉ። ይህም አያስደንቅም፤ እሱ ራሱ ሰይጣን እንደ ብርሃን መልአክ ይመስላልና። የሰይጣን መልእክተኞቹም የጽድቅ መላእክትን ቢመስሉ ታላቅ (የሚያስደንቅ) ነገር አይደለም። ፍጻሜያቸው ግን እንደሥራቸው ጥፋት ነው።» (፪ቆሮ.፲፩፣፲፫–፲፭፤ ፊልጵ.፫፣፪)።

የመናፍቃን እንቅስቃሴ ለጊዜው እንደ አበባ የፈካ መስሎ የሚታይ ሲሆን፣ ኃይለ እግዚአብሔር እና መንፈስ እግዚአብሔር የተለየው በሐሰት ላይ የተመሠረተ የዲያብሎስ ተግባር በመሆኑ ግን ውጤቱና ፍጻሜው ሞትና ጥፋት፣ ከንቱ ነገርም ነው።

«ወእልቦ ዘያስሕትክሙ በነገረ ከንቱ እስመ በእንቲአሁ ይመጽእ መዓተ እግዚአብሔር...በከንቱ ነገር የሚያስታችሁ አይኑር፤ በሱ ምክንያት በከሐዲዎች ልጆች የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣልና። እንግዲህ አትምሰሉአቸው።...ወኢትኅበሩ ምስለ እለ አልቦሙ ምግባር፤ ወዘጽልመት ኩለንታሆሙ፣ አላ ገሥጽዎሙ። እስመ ዘበጽሚት ይገብሩ ኀፍረተ ለነጊር። በሥራቸው ፍሬ ከሌላቸው፣ ሁለንተናቸው ጨለማ ከሆኑ ሰዎች ጋር አትተባበሩ፤ ነገር ግን ገስጹአቸው። ተሰውረው የሚሠሩት ሥራ ለመናገር የሚያሳፍር ነውና።» (ኤፌ.፭፣፮–፲፫)።

እንደዚህ ዓይነቱ ችግር ሲያጋጥም ሊወገድ የሚችለው በዓላማ ጽናት፣ በእምነት ከከፉ ሰዎች በመራቅና በጸሎት ኃይል እንደ ሆነ ሲያመለክት፣ ቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙሩን ጢሞቴዎስን እንዲህ በማለት ያስጠነቅቃል።

«አ ጢሞቴዎስ ዕቀብ ማኅፀንተከ፤ ተገሐሦሙ ለርኩሳን እለ ያመጽኡ ነገረ ከንቶ፤ ወያሴስልዋ ለጽድቅ በሐሰት፤ እስመ እሉ ስሕቱ እምተስፋ ሃይማኖት። ጢሞቴዎስ ሆይ አደራህን ጠብቅ ከንቱ ነገር የሚያመጡትን፤ እውነትን በሐሰት (እምነትን በክሕደት) የሚለውጡትን ርኩሳንንም ተለያቸው እነሱ በሃይማኖት ከሚገኝ ተስፋ ወጥተዋልና። ጢሞቴዎስ ሆይ በውሸት እውቀት ከተባለ፣ ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍና መከራከር እየራቅህ የተሰጠህን አደራ ጠብቅ፤ ይህ እውቀት አለን ብለው አንዳንዶች ስለ እምነት ስተዋልና (፩ጢሞ.፮፣፳)።

አዎ፣ መናፍቃን ለዚህ ዓለም የሚያመች ዕውቀት አለን ብለው በማስባቸው እምነትን በፍልስፍና ሚዛን ሊለኩ ቢጥሩም፣ ሚዛናቸው ሰባራ፣ ሥራቸውም ጐደሎ እየሆነ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሳቸው ባለመሆኑ መድረሻቸው ውድቀት ነው። የመናፍቃን በዓለም ላይ መብዛትም የመጨረሻ ክፉ ዓመታት ምልክት እንደሆነ ማንም ሊያስተውልና ሊገነዘብ ይገባል። ለዚሁም አሁንም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ያስጠነቅቃል።

«ወዘንተ ባሕቱ አእምር ከመ በደኃሪ መዋዕል ይመጽእ ዓመታት እኩያት...ነገር ግን በኋላ የሚያስጨንቁ ዘመናት እንደ ሚመጡ ይህን ዕወቅ። ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ፣ ገንዘብንና ደስታንም የሚወዱ ቀባጣሮች አሉቧልተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ አባት እናታቸውን የሚክዱ ምስጋና የለሾች፣ ከጽድቅ የወጡ ይሆናሉ። ርኅራኄ የሌላቸው መልካም ምግባርን የሚጠሉ ይሆናሉ። ኃጢአትን የሚያዘወትሩ፣ የተጠሉ፣ ከእግዚአብሔር ፍቅር ይልቅ ተድላ ደስታን የሚመርጡ ይሆናሉ። ይትሜሰሉ ጻድቃነ ወይክሕድዎ ለኃይለ ጽድቅ። ጻድቃን ይመስላሉ የጽድቅን ኃይል ግን ይክዱታል፤ እንደነዚህ ያሉትን ራቃቸው። በየሰው ቤት የሚገቡ፣ በኃጢአት የተያዙ ሴቶችን የሚማርኩ፣ ወደብዙ ፍትወት የሚያደርሱ ናቸው። ...ኢያኔስ ኢያንበሬስ፣ ሙሴን እንደ ተቃወሙት እነዚህም እውነትን ይቃወሙአታል፤ አእምሮ ያጡ ሃይማኖት የሌላቸው ሰዎች ናቸው።» (፪ጢሞ.፫፣፩–፰)

ይህ ቃል የእግዚአብሔር ቃል ነውና አሉ የሚባል ሊለወጥ ወይም በደካማ ፍላጐት በግብዝነት የሚለወጥ የመናፈቃንን ባሕርይ ግልጽ አድርጎ ያስቀመጠ በመሆኑ ያስደንቃል። ራስን ለመመርመር ራስን ለመጠየቅም ይረዳል። «ሁቁ እንከ አኀዊነ፣ ኢይትረከብ በላዕለ አሐዱሂ እምኔክሙ ልብ እኩይ ሕጹጸ ሃይማኖት ወንፉቅ ዘያርኀቀክሙ እም እግዚአብሔር ሕያው። አላ ሕቱ ነፍስክሙ ኵሎ አሚረ። ወንድሞቻችን እንግዲህ ዕወቁ፤ ከእናንተ ባንዱ ላይ ስንኳን ሃይማኖት የጐደለው፣ ተጠራጣሪ ከእግዚአብሔር የሚለያችሁ ክፉ ልብ አይኑር። ሁል ጊዜ ሰውነታችሁን መርምሩ፤ ዛሬ የሚባለውን ያህል ከናንተ ማንም ቢሆን ወደ ኃጢአት የሚያደርስ ስሕተት እንዳይጸና። የመጀመሪያዋ እምነታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ፣ በዚህች ጽድቅ ከክርስቶስ ጋር ነን። (ዕብ.፫፣፲፪–፲፬)።

መናፍቃን ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የምታገናኝ የክርስቲያኖች ሀብት ክብርና ሞገስ እቺ የመጀመሪያዋ እምነት መሆንዋን ስለሚያውቁ ክርስቲያኑ እስከ መጨረሻ ዘመን ድረስ በሷ ጸንቶ ሰማያዊ ክብር እንዳያገኝ ጸላኤ ሠናያት ሰይጣንን አጋዥ በማድረግ ይዋጉታል። አሁንም ስለዚህ ጉዳይ መጽሐፍ ያለውን አስተውለን እንመልከት።

«ወይእቲ አሚረ ይትከሠት ወልደ ዐመፃ ኃጥእ ዘሀለዎ ያጥፍኦ መንፈሱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወይስዕሮ በአስተርእዮተ ምጽአቱ ያን ጊዜም የዐመፅ ልጅ ኃጥእ ይገለጣል። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈሱ በምጽአቱ መገለጥም ያጠፋዋልና። ይሽረው ዘንድ ያለው።

«ወምጽአቱሰ ለዝንቱ በኀይለ ሰይጣን፣ በኵሉ ኃይል ወትእምርት ወመንክር ዘሐሰት።» የዚያ ሰው አመጣጡም በሰይጣን አጋዥነት፣ ኀይልን፣ ተአምራትን፣ በሐሰት የሚያስደንቅ ሥራንም በመሥራት ሁሉ ነው። ለጕስቋሉች ኃጢአትን በሚያስተምር ፍጹም ማሳት ነው።

ስለዚህም ምክንያት በእውነት ያላመኑ፣ ነገር ግን በዓመፅ ደስ ይላቸው የነበሩ ኹሉ፣ ፍርድን እንዲቀበሉ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል። (፪ተሰ.፪፣፰–፲፪)።

«ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ፤ እንዲሁም በመካከላችሁ ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ። እነርሱም በደሙ የዋጃቸውን ፈጣሪያቸውን የሚክዱ፣ ሐሰትን የሚያስተምሩ፣ ለጕስቁልናም ክሕደትን የሚዘሩ፤ ጥፋትንና መደምሰስን በቶሎ የሚያመጡ ናቸው። ብዙ ሰዎችም እነሱን ይከተሉአቸዋል፤ ስለዝሙታቸው እውነተኛ ትምህርትን ይነቅፉሉ። «በእንተ ዝሙቶሙ ይፀርፉ ላዕለ ፍኖተ ጽድቅ፤» በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል። ገንዘብንም በመመኘት በተፈጠረ ነገር ይረቡባችኋል። ፍርዳቸውም ከጥንት ጀምሮ አይዘገይም፤ ጥፋታቸውም አያንቀላፋም።» (፪ጢሞ.፩፣፫)።

«መንፈስ ገሃደ ይነግር ከመ በድኃሪ መዋዕል የአልው ሃይማኖቶሙ ብዙኃን፤ ወይትልውዎሙ ለአጋንንት መስሕታን ወትምህርተ ሰይጣናት ዘያነፍቅ። መንፈስ በግልጥ ይናገራል። በኋላ ዘመን ብዙዎች ሃይማኖታቸውን እንደሚክዱ፣ የሚያስቱ አጋንንትን የሚያጠራጥረውን የሰይጣናትን ትምህርትም እንደሚከተሉ። (፩ጢሞ.፬፣፩፤ ማቴ.፳፬፣፲)።

የመናፍቃን የመምጣት ነገርም መጻሕፍት አስቀድመው አስጠንቅቀዋል። «ወአነ አአምር ከመ ይመጽኡ እምድኅሬየ ተኵላት መስተ እለኢይምህክዋ ለመርዔት»። ከኔ በኋላ ለመንጋዩቱ የማይራሩ ነጣቂዎች እንደ ሚመጡ እኔ አውቃለሁ። ከእናንተ መካከል ሰዎችን ወደ እነሱ ይመልሱ ዘንድ ጠማማ ትምህርትን የሚያስተምሩ ሰዎች ይነሣሉ።

አሁንም ትጉ፤ እኔ ሁላችሁንም ሳስተምር ሦስት ዓመት ሙሉ ሌሊትም ቀንም ዕንባዩ እንዳልተገታ አስቡ። (ግብ ሐዋ.፳፣፳፱–፴፩)።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም፣ «ልጆች ሆይ መጨረሻው ሰዓት ነው፤ የክርስቶስም ተቃዋሚ ይመጣ ዘንድ እንደ ሰማችሁ አሁን እንኳ ብዙዎች የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ተነሥተዋል። ስለዚህም መጨረሻው ሰዓት እንደ ሆነ እናውቃለን ይላል። (ዮሐ.፪፣፲፰)።

እዚህ ላይ መጨረሻው ሰዓት ነውና መናፍቃን የክርስቶስ ተቃዋሚዎች የእውነት ጠላቶች የሰይጣን መልእክተኞች መነሣታቸው ግዴታ በመሆኑ ምን ማድረግ ይቻላል የሚል ሐሳብ ሊኖር ይችላል፤ ለዚሁ ግን አሁንም መጻሕፍት የመጻእያቱን ዘመናት ችግር ቀድመው ያወቁ በመሆናቸው ዘመኑ ለሚያመጣቸው የክሕደት ችግሮች በቂ መልስ አላቸው። ምክራቸውንና ማስጠንቀቂያቸውን በየአቅጣጫው ይለግሳሉ።

«ወአንትሙሰ አኀዊነ ቅድሙ አእምሮ፤ ወተዐቀቡ ከመ ኢትስሐቱ በዘኢይበቍዕ ትምህርት ከመ ኢትደቁ እምነ ምጽናዕክሙ። ወንድሞቻችን እናንተስ አስቀድማችሁ ዕወቁ፤ በማይጠቅም ትምህርት እንዳትስቱ ተጠንቀቁ፤ ከጸናችሁበት እንዳትወድቁ። (፪ጴጥ.፫፣፲፯)፡

የፍጥረታት ጌታ መድኃኔዓለም ክርስቶስም፣ በፍቅሩና በቸርነቱ ብዛት፣ በደሙ የዋጀው ፍጥረቱ፣ በመስሕታን እንዳይጠፉበት፣ የድኅነት አዋጁን እንዲህ በማለት አውጆልናል።

«ወብዙኃን ሐሳውያን ነቢያት ይመጽኡ፤ ወያስሕትዎሙ ለብዙኃን። ወእም ብዝኀ ዓመፃ ወእከይ ትቈርር ፍቅር እም ብዙኃን። ወዘሰ አዘለፈ ትዕግሥቶ ውእቱ ይድኅን። ብዙዎች ሐሰተኞች መምህራን ይመጣሉ፤ ብዙዎችንም ያስታሉ። ከዐመፅና ከክፋት የተነሣም ፍቅር ከብዙዎች ዘንድ ትጠፋለች። ትዕግሥትን ያዘወተረ (ገንዘብ ያደረገ) እርሱ ይድናል። (ማቴ.፳፬፣፲፩–፲፫)።

«ወአንትሙሰ አኀዊነ ተዘከሩ ቃለ ዘነገሩክሙ ቀዲሙ...ወንድሞቻችን እናንተስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሾማቸው ሐዋርያት መጀመሪያ ያስተማሩአችሁን ቃል አስቡ። በኋላ ዘመን በልበ ወለድ የሚያስተምሩ፣ በእነሱ ኃጢአት ሌላቸውን የሚያስቱ አሳቾች እንደሚመጡ የነገሩአችሁንም አስቡ። እሊህ ናቸው በኃጢአታቸው የሚለዩ፤ ልቡናቸው በወደደው የሚያስቱ መንፈስ ቅዱስ ያላደረባቸው» (ይሁዳ.፲፰፣፲፱)።

እንግዲህ መጻሕፍት ግልጹ በሆነ ቋንቋ ከጥፋት፣ ከሞት የምንድንበትን መንገድ ከነገሩን ዘንድ፣ መጻሕፍት በሚመክሩን ተጠቃሚዎች መሆን የትውልዱ ምርጫ ሊሆን ይገባል።

ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን፣ ዲያብሎስ አዳምንና ሔዋንን ሲያስት ወዳጅ መስሎ በለዘበ አንደበት አሳቢ ተቆርቋሪ በመምሰል እንጂ እኔ ዲያብሎስ ነኝ እኔ የእግዚአብሔር ጠላት ነኝ ብሎ አልነበረም። ዛሬም የእግዚአብሔር ጠላቶች መናፍቃን ሰው የሚጐዱበት ዘዴ፣ በለዘበ አንደበት በተደበቀ ክህደት መርዛቸውን በማር ሸፍነው እንጂ በግልጽ ቀርበው አይደለም።

ስለዚህ የመናፍቃን የተኩላት ጕረቤት በመሆኑ ከተኩላ ጕርብትናም ሞት እንጂ ሕይወት ስላይደለ ልብ ያለው ልብ ይበል፤ ጆሮ ያለው ይስማ አእምሮ ያለው ሁሉ ያስተውል። እኛም መንጋችንን ከተኩላት ለመጠበቅ እንትጋ። ✣

እግዚአብሔር ከመናፍቃን ወጥመድ ይጠብቀን አሜን ።




www.ethiopianorthodox.org

# አገልግሎታችን እንዴት ይሁን?

ከመምህር አምሳሉ ተፈራ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ዋና ጸሐፊ

«መንግሥተ ሰማያትን በብዙ መከራ»
(ሐዋ.፲፬፥፳፪)

ሰው የሚወደውን ለማግኘት ሲል ብዙ መከራ ይቀበላል እጅግ አብልጦ የሚሻውን ነገር ለማግኘት ደግሞ እጅግ የሚሆን ስቃይ ቢቀበል እንኳን ቅር አይሰኝም። እንዲያውም ሰው በተፈጥሮው የሚደሰተውና ታላቅ ክብርም የሚሰጠው ብዙ ዋጋ ላወጣበት መሆኑን የሥነ ልቡና ጠበብት ይስማሙበታል።

የዚህ ጽሑፍ ዓላማም ከዋጋና ስጦታ በላይ ለሆነችው የሰዎች የዘለዓለም መኖሪያ መንግሥተ ሰማያት ብዙ ፈተናና መከራ መቀበል እንደሚገባ ግንዛቤ መስጠት ነው። ለርዕሱ መነሻ የሆነውን ኃይለ ቃል የተናገረው ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ነው። የእግዚአብሔርን የመንግሥት ወንጌል በሚያስትምርበት ጊዜ በወቅቱ የነበሩ አይሁድ አብዝተው ደበደቡት፤ አንገላቱትም። እርሱ ግን ዓላማው ነውና በማግስቱ ሊያስትምር ተነሳ፤ ከበርናባስ ጋር ወደ ደርቤንም ሄደ። በዚህችም፤ ከተማ ሕይወትን የሚሰጥ እና የሚያጽናና ትምህርትን ያስተምር ጀመር «...እስመ በብዙሁ ሕማም ሀለወነ ንባእ ለመንግሥተ እግዚአብሔር»...ብሎ። ወደ ሰማያዊት የእግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ብዙ መከራ መቀበል አያሌ ፈተናን ማለፍ እንዳለብን አስተማረ። ይህ ነው ክርስትና የክርስቶስን መከራ መስቀል ተሸክሞ መኖር፤ ጊዜያዊ በሆነ ስቃይ (መከራ) ሳይሸነፉ ዘለዓለማዊውን ሕይወት በማሰብ መጽናት፤

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስን የደበደቡት ክፉኛ ስለ ነበር የሞተ መስሏቸው ከከተማ ውጭ እንደጎተቱት እንረዳለን (ሐዋ.፲፬፥፲፱) ይህም ብቻ አይደለም ስለ ወንጌል ብሎ ብዙ ጊዜ ታስሯል ተገርፏል። እስከ ሞት ድረስ ተደብድቧል፤ በበትር ተመትቷል፤ የሚጓዝበትን መርከብ አይሁድ ሰባብረውበታል፤ ሌሊትና ቀን በባህር ኖሯል፤ ወዘተ. (፪ቆሮ.፲፩፥፳፪–፳፱)

ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሁሉ መከራ የተቀበለው ጥሪውን ስላሰበ የመንግሥተ ሰማያትን ሕይወት ስላስታወሰ ነው። የአምላኩን ድምፅ ስለ ሰማ ያሳድደው እንዳልነበር ስለ እርሱ ተሰደደ ብዙ መከራንም ተቀበለ፤ በወገኖቹም ተጠላ። ጌታ በወንጌሉ «ስለ ስሜ ትጠላላችሁ» ብሏልና (ዮሐ.፲፮፥፴፫) ጻድቃን፤ ሰማዕታት በሙሉ ይህንን ፈጽመዋል። ይህን ሁሉ ስናስብ እኛም እንዴት አድርገን መጽናት እንዳለብን ራሳችንን መጠየቅ የግድ ነው። የአባቶቻችን የቅዱሳንን ተጋድሎ ስናስብ እኛስ እንዴት ነው አምላካችንን የምናገለግለው ብለን መጠየቅ አለብን። ለዚህ እንዲረዳን የሚከተሉትን ነጥቦች ደረጃ በደረጃ እንፈጽማቸው።

## ፩ኛ. ሃይማኖታችንን በትክክል መረዳት፤

ሃይማኖት የሌለው ሰው ስለ መንግሥተ ሰማያት ቢነግሩት አይገባውም። ነገር ግን ሰው በእምነቱ ከጸና የሚለምነውን ያገኛል፤ የሚያስጨንቀውን ለአምላኩ ያሳስባል፤ አምላኩም ስለ በጎ ልመናው የልቡን ይፈጽምለታል (ማር.፲፩፥፳፬፤ ፩ጴጥ.፭፥፯) ስለዚህ ስለ መንግሥተ ሰማያት መኖርና ለሰዎች መስጠት ማመን፤ ተቀዳሚ ነው። በቀጣይነትም ሃይማኖታችን የሚፈቅደው እንዴት መኖርን ነው? የሚለውን ዐቢይ ቁም ነገር ማሰብ ያስፈልጋል። በተለይም ፈተናና አንቱል ፍልስፍና በበዛበት በዚህ ዘመን ሃይማኖትን ለመማር ራስን ማዘጋጀት፤ የሕይወት ቃል የሆነውን ወንጌልን ለመስማት መፋጠን ታላቅነት ነው። ዛሬ ከእኛ የሚጠበቀው የመጀመሪያው ደረጃ ይህ ነውና ሃይማኖታችን የሚያዘንን ማለትም ጾሙን፤ ጸሎቱን፤ ስግደቱን፤ ምጽዋቱን፤ ቅዳሴውን ወዘተ. መፈጸም እምነታችንን በትክክል እንድንረዳ ያስችለናል።

## ፪ኛ. የድርሻችንን ማገልገል፤

ሰው የሚሮጠው በአቅሙ ነው። ክርስቲያንም ሸክሙን የሚሸከመው በደረጃው ነው። ጌታችን በወንጌሉ እንዳስተማረን ለሦስቱ ሰዎች የተለያየ መክሊት ነው የሰጣቸው፤ በኋላም ከእነርሱ የጠየቃቸው በተሰጣቸው መጠን መሥራት አለመሥራታቸውን ነበር (ማቴ.፳፭፥፲፬–፴) ዛሬም ከእኛ የሚጠበቀው በደረጃችን (በአቅማችን) ማገልገል መቻል አለመቻላችንን ነው።

ዓይነቱ ይልያይ እንጂ እግዚአብሔር ከእያንዳንዳችን አገልግሎትን ይፈልጋል፤ በመታዘዝ፤ በመላላክ፤ በሐሳብ በመርዳት፤ አስራት በኩራት በማውጣት፤ በማስተማር፤ በመዘመር፤ ወዘተ. ቤተ ክርስቲያንን እያገለገልን ለመንግሥተ ሰማያት እጩዎች መሆን ይገባናል። ወጣቶች በሰንበት ት/ቤት፤ አረጋውያን በቤተ ክርስቲያን፤ ካህናት በቤተ መቅደሱ እንደ ሀብታችን ማገልገል አለብን። ነገር ግን እነዚህን ሁሉ አገልግሎቶች ማበርከት እንዳለብን ብናስብም በተለያዩ ምክንያቶች ስንሸነፍ እንታያለን። ለመታዘዝ ስናስብ ትዕቢት፤ ለመላላክ ስንነሳ እምቢተኝነት፤ ይፈታተነናል። አሥራት በኩራት እና ምጽዋት እንስጥ ስንል ስስት፤ እንዘምር ብለን ስንነሳ ኩራት ይይዘናል። ሆኖም ግን መንግሥተ ሰማያትን ለመዋጀት የድርሻችንንና የሚጠበቅብንን ማገልገል ይፈለግብናል። ይልቁንም ቅዱሱ አምላካችን ከሚያደርግልን ብዙ የቸርነት ሥራ አንጻር እኛ የቱንም ያህል ብናገለግለው እንኳ ዋጋው እንደሚያንሰው ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል (መዝ.፩፻፲፭፥፫፤ ፪ቆሮ.፱፥፭) ስለዚህ እሱን በብዙ ማገልገል ይገባናል ብዙ ከተሰጠው ሰው ብዙ ይጠበቃልና።

## ፫. በፈተና መጽናት

ፈተና ማለት ከባድ ችግር፤ ስቃይ፤ እንግልት፤ ረሃብ፤ ጉዳት ወዘተ. የሚሉትን የሚያጠቃልል ነው። ክርስቲያን ከሚኖርበት አካባቢ በሚመጡበት ልዩ ልዩ ፈተናዎች አይሰቀቅም። ምክንያቱም ተስፋ አለውና ጌታችን ክርስቶስ ተፈትኖ ሰይጣንን በማሳፈር አብነት ስለሆነ ነው። አባቶች በብሂላቸው «ወርቅ በእሳት ይፈተናል» እንደሚሉት ሁሉ የክርስቲያንም መለኪያው በፈተና መጽናት ነው። ስለ ስሙ መከራ ልንቀበል ጭምር እንጂ በስሙ ልናምን ብቻ አልተጠራንምና።

ፈተና በተለያዩ ምክንያቶች ሊመጣ ይችላል። ከሁሉም ይልቅ ክርስቲያን በመሆናችን፤ በወንጌል በማመናችን፤ ከዓለም በመለየታችን የሚመጣብን ፈተና ቢኖር በትዕግሥት መጽናት ይገባናል። ምክንያቱም የዚህ ዓለም ገገር የሆነው ሰይጣን የእሱ በሆኑት ላይ ለጊዜው የሚያሳያቸው ደስታውን ዘፈኑን ነውና። በመጾም በመጸለይ ሕይወት የሚገኝ አይመስላቸውም። እውነተኛ ክርስቲያኖች ግን ኑሯቸው ሁሉ ክርስቶስን መምሰል ነውና ከዓለም ዳንኪራ የተለዩ ናቸው። ከዚህም በከፋ መልኩ እስከመሰደድ ይደርሳሉ። ጌታችንም «ወበዓለምሰ ሕማመ ትረክቡ ወባሕቱ ጽንሁ እስመ አነ ሞዕክዎ ለዓለም» በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ነገር ግን አይዟችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁና። (ዮሐ.፲፮፥፴፫) ብሎ ያስተማረን በሚመጣብን ፈተና እንድንጸና ሲያስተመረን ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም «በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው። ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወት አክሊል ይቀበላልና» (ያዕ.፩፥፲፪) በማለት የምንወርሳትን መንግሥተ ሰማያትን በእምነት ያሳየናል።

ስለዚህ የጊዜ ስፍሩ ከወዲያኛው ዓለም ሲነጻጸር እጅግ አጭር በሆነው በዚህ ዓለም ምንም እንኳ ከባድ የተባለ ችግር ቢደርስብን ከሞት በኋላ ከምንወርሳት መንግስተ ሰማያት አይበልጥምና እንጽና። «በትንሹ የታመነ በብዙ ይሾማል» የሚለው አምላካዊ ቃል (ማቴ.፳፭፥፳፩) የሚያሳስበንም በዚህ ዓለም በትንሹ በፈተና የጸና በመንግሥተ ሰማያት ለዘለዓለም እንደሚኖር ነው።

## ፬. ሰማዕትነትን መቀበል

ሰማዕትነት የሚለው ቃል ምስክርነትን የሚያሳይ ሲሆን ሁለት ዓይነት ፍቺ አለው። የመጀመሪያው ስለስሙ መከራን ተቀብሎ ደምን አፍሶ ሕይወትን ስለ እግዚአብሔር መስጠት ሲሆን ሌላው ደግሞ ደምን ሳያፈሱ አጥንትን ሳይከሰክሱ በማስተማርና በመመስከር ሃይማኖትን በፍጹም ጽናት መግለጥ ነው።

ሰማዕትነትን መቀበል ማለትም ስለ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት በአላውያን (በማያምኑ) ሰዎች ፊት መስክሮ መሞት ማለት ነው። ሞትን ስናነሳ የሰዎች በተለያየ ሁኔታ መሞት በየጊዜው የምናየው ሐቅ ስለሆነ ብዙ አይገርምም። ግማሹ በድንገተኛ ሕመም፤ ሌላው በብዙ ስቃይ፤ ግማሹ በረሃብ በጦርነት...ወዘተ ይሞታል። መሞትም ለሰው ልጆች የተሰጠ ሰብአዊ ባሕርይ ነው። ነገር ግን ማሰብ ያለብን ሞት የማይቀር ከሆነ አሟሟታችን ስለ ወንጌል በመሰደድ ስለ ክርስቶስ በመመስከር በክብር ለምን አይሆንም? የሚለው ነው።

ለዚህ አብነት የሚሆኑን ቅዱሳን ሐዋርያትና ሰማዕታት ናቸው። ልበ አምላክ ዳዊት «እስመ በእንቲአሁ ይቀትሉነ ኵሎ አሚረ። ወኮነ ከመ አባግዕ ዘይጠብሑ...ስለ እርሱ ሁል ጊዜ ዕለት ዕለት ይገድሉናል እንደሚታረዱ በጎችም ሆንናል።» (መዝ.፵፫፥፳፪) ብሎ እንደ ተናገረው ሰማዕታት ቈዳቸው ተገፏል፤ ሰውነታቸው ቆስሏል። ሐዋርያት በሰይፉ ተቈራርጠዋል፤ በመጋዝ ተቀርድደዋል ሰይፉና ስለት ተፈራርቆባቸዋል። በዚህ ሁሉ ግን መከራቸው ሳይሆን የሚታያቸው የመንግሥተ ሰማያት አክሊል፤ ነበር።

ያለመከራ ጸጋ ያለ ድካም ዋጋ አይገኝምና ቅዱሳን በድካም በመገረፍ በመሞት ቢፈተኑም እንኳ ተስፋቸውን አግኝተዋል። ክርስቲያንም የሞተለትን አምላክ ዋጋ ሙሉ በሙሉ ለመመለስ ባይችልም የማያምኑ ሰዎች በእግዚአብሔር አምላክነት ሲያላግጡ ምስክርነት (ሰማዕትነት) እንዲሰጥ ይጠበቅበታል።

እኛንም ዛሬ እግዚአብሔር የሚጠይቀን በደረጃችን ሰማዕትነትን እንድንቀበል ነው። ይህም ሲጠቃለል ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ማክበርና ሕገ እግዚአብሔርን መጠበቅ ነው። ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ደግሞ እንደ ክርስቲያንነታችን ስንኖር ማድረግ ያለብንን ያሳያል። ይህም ማለት መጾም፤ መጸለይ፤ መስገድ መመጽወት ወዘተ...እጅግ አስፈላጊያችን ስለሆነ መፈጸም አለብን። ነገር ግን ልዩ ልዩ ምክንያቶችን በመዘርዘር አንጾምም፤ አንጸልይም፤ አንሰግድም። ይህም መንፈሳዊ ሕይወታችንን ያቀጭጨዋል። ሆኖም ግን ለመንግሥተ ሰማያት መጋደል ይገባናልና መትጋት ይኖርብናል። በሌላ አንጻርም ክርስትናችንን ማጣት፤ መራቆት፤ መጠማት፤ መሰደድ፤ መሞት ወዘተ... ሊቀይረው አይገባም። ይህን ሲያስገነዝበን ነው ሐዋርያው «ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል... በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን» ያለው (ሮሜ.፰፥፴፭–፴፰)

ባጠቃላይ እምነት በሥራ የሚገለጥ እንዲሆን ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን የጽሑፋችንም መነሻ እንዳደረግነው «መንግሥተ ሰማያትን የምንዋጃት በብዙ ምግባር ትሩፋት ነውና ሕሊናችንን ለጽድቅ እናዘጋጀው። በክርስትና ጉዞአችን ላይ ብዙ መከራ መቀበል ካለብን ሲባል ደግሞ ማሰብ ያለብን በሥራችን ሁሉ ላይ የአምላካችንን ረድኤት ተስፋ ማድረግ አለብን ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች እናስተውላቸው። «ትታገሱ ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል» (፩ቆሮ.፲፥፲፫) «የሰማይ አምላክ ያከናውንልናል እኛም ባሪያዎቹ ተነስተን እንሠራለን» (ነህ.፪፥፳)

አምላካችን ለሁላችንም ጽናቱን ያድለን! ✣



www.ethiopianorthodox.org

# ከወጣቱ ለወጣቱ

## አንድነታችን የሚገለጠው በኅብረታችን ነው

(የብዕር ቅኝት መምህር ዕንቈባሕርይ ተከሥተ)



በዝሬው ከወጣቱ ለወጣቱ ይገፍላችሁ የቀ ረብኩት በዚህ በመንበረ ፓትርያርክ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ለበርካታ ዓመታት ከአቃቂ እየተመላለሱ ትምህርቱን ከተከታተሉ መካከል የመዘመርና የመያዝ ትልቅ ተሥጥዎ ያላት ወጣት ሉሊት ማንደፍሮ ናት ነው።

ወጣት ሉሊት ማንደፍሮ ዕድሜዋ ፳፪ ዓመት ሲሆን በሰንበት ትምህርት ቤት አባል ሆና ማገልገል ከጀመረች ፲፩ ዓመታትን አ ሳልፋ ፲፫ኛ ዓመትዋን ይዛለች።

ወጣት ሉሊት ማንደፍሮ በአቃቂ አካባቢ ከሚገኙ የሰንበት ትምህርት ቤት አባላት ጠን ካራና ባለጽኑዕ ዓላማ፤ ለሰንበት ትምህርት ቤትዋ ብዙ ያገለገለችና በማገልገል ላይ የምትገኝ ነች። ወጣት ሉሊት ማንደፍሮ ለወ ጣቶች ብዙ የምትለን አለና በጥሞና እናዳ ምጣት። መልካም ንባብ።

ፈለገ ጥበብ – ሉሊት አሁን ያለሽው በዚህ በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በሚዘጋጀው የመዝሙር ዝግጅት ለ፭ ዓመታት ከዚያም በላይ ቆይተሻል፤ ስለዚህ በዚህ ረገድ ያለው እንቅስቃሴ ብትገልጭልኝ።

ሉሊት – የመጣሁት ከሳሉ ደብረ ፀሐይ ቅዱሳ ጊዮርጊስና ቃሊቲ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤት ነው። ሰንበት ትምህርት ቤቱ ሊወክለኝ የቻለው ከሕፃንነቴ ጀምሮ በሕፃናት ክፍል ያደኩ እና አሁንም በሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ ያለሁኝ ነኝ። በዚሁ መሠረት ነው ልወክል የቻልኩት። ሰንበት ትምህርት ቤቶችን በአሁኑ ጊዜ ብዙ ለውጥ አለን፤ ማለት ከዚህ ማጥናት ከጀመርን ጀምሮ በፊት ዝም ብለን ነው የምንዘምረው በአሁን ጊዜ ግን በየወቅቱ የሚዘመሩት እዝል፤ ግዕዝ፤ ዓራራይ በየወቅቱ እንደ በዓሉ ሁኔታ እንዘምራለን።

ፈለገ ጥበብ – መቼ ነው ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት የገባሽው እንዴትስ ገባሽ?

ሉሊት – ማለት በልጅነቴ ቤተሰብ ወደ ቤተክርስቲያን ያመጡኛል በዚያ ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ገባሁ እንዴት እንደገባሁ አላውቅም።

ፈለገ ጥበብ – ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ከገባሽ ጀምሮ ስንት ዕድሜ ይሆናል?

ሉሊት – ከ፲፱፻፹፬ ዓ.ም ጀምሮ ነው።

ፈለገ ጥበብ – አሁን በሰንበት ትምህርት ቤቱ ያለው ጠቅላላ እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?

ሉሊት – በሰንበት ትምህርት ቤቱ ጥሩ እንቅስቃሴ ነው ያለው፤ በፊት አዳራሽ አልነበረም፤ በሥርዓቱ የተዘጋጀ መዝሙር አልነበረም፤ በአሁን ጊዜ እነዚህ ሁሉ ተሟልቷል ጥሩ እንቅስቃሴ ነው ያለው።

ፈለገ ጥበብ – ሰንበት ትምህርት ቤቱ ስንት ያህል አባላት አሉት (ይኖሩታል?)

ሉሊት – በመዝሙር አገልግሎት ያሉት ጥቂት ናቸው። ጠቅላላ አባላት ግን ከአንድ ሺህ በላይ ናቸው።

ፈለገ ጥበብ – በትምህርት ቤቱ የትም ህርት አሰጣጥ መርሐ ግብር ምን ይመስላል?

ሉሊት – የመምህራን ዕጥረት አለብን፤ እንደዛም ሆኖ ከሥነ ፍጥረት እስከ ዶግማ ድረስ በተከታታይ እንማራለን። ይህም ማለት ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን፤ ስብከት፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፤ መዝሙራት፤ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ምግባር ናቸው።

ፈለገ ጥበብ – ጠቅላላ የሰንበት ትምህርት ቤቱ ሕይወት ምን ይመስላል? አሁን ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው አገልግሎት፤ ከአባቶች ጋር ያለው ግንኙነት፤ ከአስተዳደር ጋር ያለው ታዛዥነት ዘርዘር አርገሽ ብትነግሪኝ?

ሉሊት – ከአባቶች ጋር በጣም ቆንጆ የሆነ ግንኙነት ነው ያለን።

ፈለገ ጥበብ – በሥራ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች አሉ?

ሉሊት – ችግሮች አልፎ አልፎ ይከሰ ታሉ ለምሳሌ በመንበረ ፓትርያርክ ስብሰባ ሲደረግ የሚወከሉት ፪ ሰዎች ብቻ ናቸው ለምን ቢባል ከቦታ ርቀትና ከአቅም ማነስ ነው ራሱ ይህ ችግር ነው። በጣም የጐላ ችግር ግን አላጋጠመንም።

ፈለገ ጥበብ – ችግሩ ምንድነው?

ሉሊት – ለእኛ ሲገልጹልን በወጪ ምክ ንያት እንደሆነ አድርገው የሚነግሩን፤

ፈለገ ጥበብ – የሰንበት ትምህርት ቤት አባል በመሆንሽ የገጠመሽ ችግር የምትዩው አለ? መንፈሳዊ ስሜትሽ ምን ይሰማሻል?

ሉሊት – የሰንበት ትምህርት ቤት አባል በመሆኔ ምንም ያጋጠመኝ ችግር የለም። የሰ ንበት ትምህርት ቤት አባል መሆኔ ከብዙ ነገር ጠብቆኛል። ዛሬ በቤተክርስቲያን ሕይወት መኖር በጣም ጠቃሚ ነው። ራስህን ከማ ንኛውም ነገር እንድትጠብቅ ያደርግሃል።

ፈለገ ጥበብ – አንቺ ከመጀመሪያዎቹ የማዕከላዊ መዘምራን አንዷ ነሽና በመጀመሪያ ስትጀምሪው እንደዚህ ሆኖ ለሙያ በቅቶ ለምረቃ እደርሳለሁ ብለሽ አስበሽ ነበር?

ሉሊት – እኔ እንደዚህ ሁኖ ለዚህ እንበ ቃለን ብዩ እንኳ አስቤ አላውቅም። ዝም ብሎ ስለተመደብን ነው የጀመርነው። ለዚህ በመብቃታችን ደስታዬ ወሰን የለውም።

ፈለገ ጥበብ – የወጣቱ እንቅስቃሴ ለወደፊቱ ዕድገቱ ሊሻሻል የሚችለው በምን ዓይነት ነው ብለሽ የምታምኚው?

ሉሊት – የጋራ ዕድገት ሊመጣ የሚ ችለው በመዝሙርና በትምህርት አንድ ዓይነት ወጥ የሆነ ሲኖር ነው። አሁን የተማርነው መዝሙር በኅትመት ውሎ ሁሉ ቢጠቀምበት ጥሩ ነው።

ፈለገ ጥበብ – ለወጣቱ በተለይም ለሴት እኅቶቻችን የምታስተላልፊው መልእክት ካለ?

ሉሊት – እኔ የማስተላልፈው መልእክት በቤተክርስቲያን መኖር ከሁሉም በላይ የበለጠና ጠቃሚ ነው። በመዝሙር በኩልም የቅዱስ ያሬድ ፈለግ ተከትለን የምንሄድ መሆን አለብን እንጂ ሙያውን ሳይዙ ስም ብቻ ይዞ መሄድ የትም አያደርስም። በተለይ በአቃቂ አካባቢ ለምንገኝ ወጣቶች ከዚህ ማዕ ከላዊ መጥቶ ያጠና የእኛ ሰንበት ትምህርት ቤት ብቻ ነው።

ስለዚህ በአካባቢው ያሉ የሰንበት ትምህርት ቤቶች የሚዘምሩት የካሴት መዝ ሙር ነው። ይህም ለአንድነታችን መለያየትን ይፈጥራል። ስለሆነም መዝሙሩ አንድ እንዲሆን ከእኛ ደብር መጥተው ቢማሩ ጥሩ ነው እላለሁ። ምክንያቱም አንድነታችን የሚገለጠው በኅብረታችን ነውና።

## በሰንበት ትምህርት ቤት ሕይወት በመኖሬ በጣም ደስ ይለኛል



ወጣት ይርጋዓለም ተካ ትባላለች የመጣችው ከደቡብ ክፍለ ከተማ ከጽርሐ ንግሥት ቅድስት ሐና ሰንበት ትምህርት ቤት ነው።

ወጣት ይርጋዓለም በሰንበት ትምህርት ቤቱ ማገልገል ከጀመረች ፲፪ ዓመታት ሆኗታል ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት በመግባቷም በጣም ደስተረኛ ነኝ። የሰንበት ትምህርት ቤት አባል በመሆኔ ከብዙ ፈተና ድኜአለሁ ትላለች።

ወጣት ይርጋዓለም ተካ የ፳፱ ዓመታት ወጣት ስትሆን ግማሹ ዕድሜዋ ያሳለፈችው በቤተ እግዚ አብሔር (በሰንበት ትምህርት ቤት) ነው። ይህ በሕይወትዋ ትልቅ ሥፍራ አለው። ለሁሉም ይርጋዓለም ለወጣቱ ብዙ የምትለው አላት እና እንከታተል።

ፈለገ ጥበብ – በስንት ዓመተ ምሕረት ነው የተወለድሽው ወደ ሰንበት ትምህርት ቤትስ የገባሽው?

ይርጋዓለም – የተወለድኩት በ፲፱፻፷፪ ዓ.ም መስከረም ስድስት ቀን ነው። ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት የገባ ሁበት በውል አላውቀውም። እድገቴ በሰንበት ትምህርት ቤት ስለሆነ በደ ንብ አድርጌ ተከታትዩ አለሁ። ብዬ የማምነው ፲፪ ዓመታት በላይ ነው።

ፈለገ ጥበብ – ወደዚሁ የማዕ ከላውያን የመዝሙር ሥልጠና ለመምጣት ያስቻለሽ ምንድነው? ልዩ ድምፅ ስለነበረሽ ነው? ወይስ በምን መመዘኛ ነው?

ይርጋዓለም – ወደዚህ ለመ ምጣት የቻልኩበት ምክንያት መጀ መሪያ ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ከሕፃንነቴ ጀምሮ እሄዳለሁ። እንደ አባል ሆኜ መማር ከጀመርኩ ፲፪ ዓመ ታት ሆኖኛል፤ በዚህ ዕድሜ ውስጥ በሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎት በሕፃናት ክፍል እና በተለያዩ የአገልግሎት ዓይነቶች አገልግያለሁ። በ፲፱፻፹፮ ዓ.ም በመዝሙር ክፍል ሆኜ እንዳገለግል ተመረጥኩኝ። ከዚያ በኋላ ከዚህ ማደራጃ መምሪያ በሄደው ደብዳቤ መሠረት በማደራጃ መም ሪያው ከጓደኞዬ ከዘሪቱ ጋር አብረን ሁለታችን ተመደብን።

ፈለገ ጥበብ – ሰንበት ትምህርት ቤታችሁ ከዚህ ቀደም ጠንካራ ነበር፤ በአሁን ጊዜ ደግሞ ቀዝቀዝ ያለ ነው የሚመስለው ደረጃው ከምን ላይ ነው ያለው?

ይርጋዓለም – እንዳልከው ሰንበት ትምህርት ቤቱ ከዚህ ቀደም ጠንካራ ነበር። የነበሩ የሥራ አመራር ለሰንበት ትምህርት ቤቱ ዕድገት በጣም የሚጥሩ የነበሩ ናቸው። ከጊዜ በኋላ ግን በሰንበት ትምህርት ቤቱ የነበሩ አባላት ግማሹ ወደ ውጭ ዓለም ሲሄድ ሌላው የራሱ ሕይወት መም ራት ሲጀምር ለታናናሾቹ አንዳንድ ነገር ነው። አስተላልፎ የሄደው፤ በዚያ ምክንያት ከአካባቢው ትንሽ ራቅ ስለሚል የአባላት ማነስ አለ።

ፈለገ ጥበብ – አንድ ነገር ሰም ቼአለሁ የራሳቸው ሕይወት መምራት ሲጀምሩ ሰንበት ትምህርት ቤቱን ይተዋሉ የሚል ነው። አሁን ያለው የእናንተው የሰንበት ትምህርት ቤት የሥራ አመራር የሰንበት ትምህርት ቤቱ አባላት ኑረው የራሳቸው ሕይወት መምራት ሲጀምሩ ሰንበት ትምህርት ቤቱን የተው ለማሰባሰብ ያደረገው ጥረት አለ? ፕሮግራም አዘጋጅቶ ይጠራቸዋል ወይ?

ይርጋዓለም – በበዓላት ዝግጅት ይኖራሉ የሰንበት ትምህርት ቤቱ ዓመታዊ በዓል እነዚያን አባላት ይጠራሉ እንጂ ያገቡም ያላገቡም በራሱ ፕሮግራም አዘጋጅቶ አይጠ ራቸውም።

ፈለገ ጥበብ – በአካባቢው አሉ የምትያቸው ችግሮች ካሉ ዘርዘር አድርገሽ ብታስረጅኝ? በሰንበት ትምህርት ቤቱ ዙሪያ ሊነሡ ይገባ ቸዋል የምትያቸው ችግሮች?

ይርጋዓለም – ለሰንበት ትም ህርት ቤቱ ተጽዕኖ ይኖረዋል ብዩ የማ ምነው ትንሽ ቤተክርስቲያንዋ ራቅ ትላለች ከዛም አንጻር ያለው ሕዝብ በአካባቢው አምልኮ ባዕድ የበዛበት ነው። ያንን ለመለወጥ በፊት ብዙ ጥረት ተደርጓል። አሁንም ትንሽ ለውጥ እየታየ ነው።

ፈለገ ጥበብ – እንደምታይው አሁን በማዕከላዊ ደረጃ መዝሙር እየተጠና፤ ለሁሉም እየተዳረሰ ነው። እናንተም ለዚሁ ምረቃ ደርሳችኋል። መጽሐፉም ለሕትመት እየበቃ ነው። ከዚህ አንጻር በመዝሙር ያለው ችግር እንዴት ነው የምትቋቋሙት?

ይርጋዓለም – አዎ በዚህ የመ ዝሙር ጉዳይ ብዙ ያከራከረን ጉዳይ ነበር። ለምን የካሴት መዝሙር ሲጠና ምንችግር አለው? የግእዝ በሚለው ብቻ ብዙ ተከራክረናል። ከጠቂት ዓመታት በኋላ ግን እነዚህ ነገሮች እየተስተካከሉ ነው። የምናስጠናቸው ማደራጃ መምሪያው እርማት ሰጥቶ ያዘጋጀው መዝሙር ነው።



www.ethiopianorthodox.org

**ፈ**ለገ ጥበብ – እነዚህ በግል ሳያስመረምሩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስም የሚያ ወጡ ምን ያህል ተጽዕኖ ያሳድራሉ ብለሽ ታምኛለሽ?

**ይ**ርጋዓለም – ተጽዕኖ በጣም አለው የትኛው የቤተክርስቲያን ዜማ መሆኑ ለይተህ ከማታውቅበት ደረጃ ያደርሳል። ግን እኛ የምንቋቋመው ሥርዓትና ደንቡን ተከትሎ በወጣው ቢሆንም ለሰንበት ትምህርት ቤቶች ወጣቶች በመዝሙር በኩል መከ ፋፈል የፈጠረው በግለሰቦች የሚታ ተመው፤ በካሴቱ ሽፋን የሚታተም ወረቀቶች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ደንብ ጠብቆ የወጣ ነው። ስለሚሉ ያ አሳማኝ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል። ይህ ደግሞ ለቤተክርስቲያን በጣም ችግር ነው። እንኳን ለምዕመን ለሰንበት ትምህርት ቤቶች አባላት በጣም አሸጋሪ ነው አንድ እልባት ሊሰጠው ይገባል። እኛ የምንቋቋመው በማዕ ከላዊ ተመርምሮ ያልወጣ መዝሙር ባለመቀበል ነው። አሁን የተመረጠው የመዝሙር ክፈል የእኛ እንዳለ ሆኖ በራሱ ደግሞ አንዳንድ የመዝሙር ካሴቶች በመምረጥ አምኖ በማስጠናት በእኛ ላይ ችግር ይፈጥርብናል ማለት ተጽዕኖ እያደረገብን ነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – የሚያምንባቸው ይቀበላል፤ የማያምንባቸው ይተዋ ቸዋል ብለሽኛል እና የሰንበት ትም ህርት ቤት የሥራ አመራር ወጣቱን ለመምራት እንጂ ይሄ ጥሩ ነው ሌላው ጥሩ አይደለም ብሎ ለመቀበል ሆነ ላለመቀበል መብትና ችሎታ አለው ወይ? ከሌለው ደግሞ እንዴት ሊቀበል ቻለ?

**ይ**ርጋዓለም – በእርግጥ ችሎታ የለውም፤ የሚሠራው በሚመስለው ነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ይኸንን ልተ ወውና ኮርስ ታስተምራላችሁ? በአ ሁን ጊዜ የኮርሱ አካሄድ እንዴት ነው? መምህራኑስ ከየት አቅጣጫ ነው የሚመጡ?

**ይ**ርጋዓለም – በኮርስ ማስተማር ከጥቂት ዓመታት በፊት የተጀመረ ነው። ሰንበት ትምህርት ቤቱ በየስ ድስት ወሩ እያስተማረ ያስመርቃል። ቀዳማይ፤ ካልአይ በማለት አዲስ አባላትን በቀዳማይ ከዚያ ተመርቀው የሚወጡት ደግሞ ካልአይ ያስተ ምራል። እንደዚያ እያለ ይቀጥላል። ለዚሁ ሁሉ ትምህርት ለማስተማር የሚመጡ መምህራን ከተለያዩ አብ ያተ ክርስቲያናት ናቸው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በሰንበት ትም ህርት ቤት ደስ የሚልሽና ጥሩ ዕድል ገጥሞኛል የምትዩው ምንድነው?

**ይ**ርጋዓለም – በሰንበት ትም ህርት ቤት ሕይወት በመኖሬ በጣም ደስ ይለኛል። ብዙ ነገሮች እንዳውቅ፤ ለራሴም ለውጥ እንዳደርግ ነው የረዳኝ። ብዙ ዕውቀት አግኝቼአለሁ። የራሴ የሆነ መሻሻል አግኝቼበታለሁ ብየ አምናለሁ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – የማትረሸው ትዝታ የገጠመሽ ቀን አለ?

**ይ**ርጋዓለም – አዎ በጣም የማ ልረሳው ነው አንድ ጊዜ ኅዳር ፲፩ ቀን በበዓላችን ቀን መዝሙር አስጠኝ ነበርኩ እኔ በመድረክ ላይ ይቀርባል ብየ አዘጋጅቼ ለሥራ አመራሩ አቅርቤ ሥራ አመራሩ መቅረብ የለባ ቸውም ብሎ አንገራገረ። እኔ ግን ወጣ ቶቹ እንዲ ቀርቡ ወስኘአለሁ ያው በዓሉ ሊከበር እንደ ነገ ሊሆን በዋዜ ማው የሥራ አመራሩ እነዚህ ልጆች ይውጡ አለ፤ ልጆቹ ደግሞ ለምን እን ወጣለን ጉባኤው በሙሉ ልቅሶ በል ቅሶ ሆነ በጣም ራሴን የሳትኩበት፤ በጣም ያለቀስኩበት ዕለት ያን ቀን ነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ሥራ አመራሩ በዚያን ጊዜ የወሰነው ትክክለኛ ነበር ወይስ ስህተተኛ ነበር?

**ይ**ርጋዓለም – ሳስበው ትክክለኛ ነበር የሚል ግምት አለኝ። ግን ደግሞ በአለቀ ሰዓት ማከልከሉ አሳዝኖኛል።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በአጠቃላይ ልታስተላልፊው የምትፈልጊው መልእክት አንቺን መሰል ለሆኑ እህቶችሽ በተለይ በዚህ ዘመን ኤድስን በሚመለከት ተጠቂው ወጣቱ ትውልድ ነውና የበሽታው ሰለባ እየሆነ ያለው በዚህ በኩል ልታስ ተላልፊው ያሰብሽው መልእክት ካለ ብትነግሪኝ?

**ይ**ርጋዓለም – ወጣት እንደ መሆኔ መጠን መጀመሪያ ወጣቱ ዓላማውን ሕይወቱን፤ ማወቅ አለበት፤ እምነቱ፤ መሠረቱ ማወቅ አለበት፤ እንጂ ዝም ብሎ እንደ እንስሳ እየተገፋ ወደ መጥፎ መንገድ የሚሄድ መሆን የለበትም። ሌላው በቤተክርስቲያን ብዙ ዓይነት ለውጦች እንዳሉ፤ እውቀቶች እንዳሉ፤ ጥበቦች እንዳሉ ነው የማ ምነው። ስለዚህ ወጣቱ ወደ ቤተክ ርስቲያን ቢቀርብ ራሱን ይለውጣል ጥበብን ዕውቀትን፤ ያገኛል፤ መሻሻልን ያመጣል። ሌላው በኤች አይቪ ዙሪያ ብዙ ተብለዋል በቤተ ክርስቲያን በዚህ ዙሪያ ብዙ ትነጋገረናል ግን የተወሰኑ ክፍል ቢለወጥም አብዛኛው አልተለወጠም።

ስለዚህ ወጣቱ ራሱን ማወቅ አለበት፤ እየተማረ በተግባር የማይ ሠራው ከሆነ በጣም ራሱን ይጐዳል ማለት ነው። በሕግ መወሰን አለበት የሚል እምነት አለኝ። ከሀገር ውጭም ከሀገር ውስጥም ላሉት ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን በመቅረብ የራሳቸው ሕይወት መምራት አለባቸው፤ እንዲሁም ስለኤች አይቪ በቤተክ ርስቲያን የሚሰጡት ትምህርቶችን ተከታትለው ከዚህ አስከፊው በሽታ ራሳቸውን መጠበቅ አለባቸው። ❖



# ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

*ይህ አምድ በሰው ልጅ ሥነ ምግባርና በኤች አይ ቪ (ኤድስ) ዙርያ ጥናታዊ ትምህርት ይቀርብበታል።*

## ከወጣቱ የሚጠበቅ ክርስቲያናዊ ግዴታ

ከመ/ስ/ዳኛቸው ካሣሁን

### ከየትኛው ክርስቲያን ወጣት?

### በማን እና በምን አስተዳደግ ካደገ ወጣት?

ባፍም በመጣፍም ሲነገር እንደሚሰማው ያልዘሩትን ማጨድ ያልበተኑትን መሰብሰብ፤ ያላስቀመጡትን ማንሳት አይቻልም። ካልተከ ሉት ዛፍ ፍሬን፤ ካላረቡት መንጋ ወተትን የሚ ጠብቅ የለም።

ልጆች የሕይወት ጣዕም የሚሰጡ ጣፋጭ ፍሬዎች ሆነው እንዲያድጉ ወላጆች መልካም ዛፎች መሆን ይኖርባቸዋል። ከል ጆች የሚጠበቀውን አገልግሎት በጊዜው ለማግኘት ወላጆች የሚገባውን ሥጋዊና መን ፈሳዊ ምግብና አዋሕደው በጥራትና በእንክ ብካቤ በትኩረትና በጥንቃቄ የማሳደግ ኃላፊ ነት ይኖርባቸዋል።

አካላዊና መንፈሳዊ ጤንነታቸው የተስ ተካከለ፤ የአእምሮ ሚዛናቸው የተደላደለ ልጆች ለማፍራት ወላጆች ከጡታያ ዕድሜ ጀምረው ብርቱ ጥረት ማድረግ አለባቸው። ጎብጠው እንዳያድጉ ሌሎችን መርዳትና ማገ ልገል ሳይሆን ለራሳቸውም ሳይሆኑ እንዳ ይቀሩ ከልጆች የሚጠበቀውን ማግኘት የሚ ችሉ አስቀድመው ለልጆች ስለ ልጆች አስተዳደግ ጥንቃቄ የሚያደርጉና ልዩ ትኩ ረት ሰጥተው በተመጣጠነ ሥጋዊና መንፈሳዊ ምግብ የሚያሳድጉ ወላጆች ናቸው።

ልጆች በሥጋዊ ጠባይ እንዳያራቡ ምግ ቡን፤ እንዳይጠሙ መጠጡን፤ እንዳይታረዙ ልብሱን ማቅረብ እንዳለባቸው ወላጆች በተ ፈጥሮ ሕግ ያውቃሉ። ከምግቡም ደረቁን ሳይ ሆን ለስላሳውን፤ ከእንቁላሉ ቅርፊቱን ሳይሆን አስኳሉን፤ እየመረጡ ወተቱን ፍትፍቱን እያመቻቹ ይመግቡአቸዋል። የቤትና የኑሮ ደረጃ በሚፈቅደው መጠን ይህ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ልጆች በመንፈሳዊ ምግብና የሚያድጉበት በሰብአዊ አመለካከት የሚጎለብቱበት የሃይማ ኖትና የሥነ ምግባር ትምህርት ያስፈልጋቸ ዋል። የነፍስ ምግብ ቃለ እግዚአብሔር ነው፤ ነፍስ ያንን ስታጣ ትጎዳለች። በአስተዳደግ የተጎዳ ሰውነት ደግሞ ማገገሚያ የለውም። ሁል ጊዜ ሕመምተኛ ዘወትር ብሶተኛ ነው። የነፍሱ (የመንፈሱ) ፈቃድና ኃይል በሥጋ ዊው ፈቃድ ይዋጣል። የመንፈስ ልምላሜ የተለየው ሕይወት ደረቅ ይሆናል፤ ደረቅ ነገር ደግሞ ይሰበራል፤ አይታዘዝም።

«ሕጉን በቀንና በሌሊት (አዘውትሮ) የሚመለከት ሰው በፈሳሽ ውሃ እንደ ተተከለች ልምላሜዋ እንደማይደርቅ ቅጠልዋ እንደማ ይረግፍ በወራቱ ሁሉ ከልምላሜ ከጽጌ (አበባ)ና ከፍሬ እንደማትለይ ፍሬዋን በየጊ ዜው ለባለቤቱ እንደምታቀርብ ዕፅ (ዛፍ) ንዑድ ነው፤ ክቡር ነው» ተብሎ የተጻፈው ስለዚህ ነው። (መዝ.፩፡፫)

### ቤተ ክርስቲያን በቤተሰባዊ አገልግሎት ያላት አስተዋጽኦ ምን ይመስላል?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከኅብረተሰቡ መካከል ሳትለይ የዕለት ከዕለት ኑሮው ተሳታፊ እንደ መሆኗ በቤተሰብ ሕይወትና በልጆች አስተዳደግ የላቀ አስተዋጽኦ ስታበረክት ኖራለች።

ልጆች ተወልደው አበ...እመ...በማለት በወላጆች ስም አፋቸውን ማምዋሸት ሲጀምሩ ቃለ እግዚአብሔርን ታጎርሳቸዋለች። ዕድሜ አቸው ዕውቀት ለመቀበል ከሚችልበት ደረጃ ሲደርሱ የፊደልን ገበታ ታቀርብላቸዋለች። ሀ.ሁ.ሂ በማለት ሆሄያትን እየቆጠሩ የዕው ቀትን ጣዕም በምላሳቸው መቅመስ ይጀም ራሉ። በቤተ ክርስቲያናችን የአስተዳዳግ ሥርዓትና ትምህርት ለሕፃናት የሚቀርበው የፊደል ከረሜላ ነው።

አ ቡ ጊ ዳ...፤ የሐዋርያት መልእክታት በተከታታይ ይቀጥላሉ መሠረተ ትምህርት። እነዚህን መላልሰው በማንበብ ያጠኑአቸዋል። ቃሉም ድምፁም በአእምሮአቸው ይቀረጻል ትውስታው በሕሊናቸው ያድራል። ከዚሁ እየተጓዙ በየደረጃው ወደሚቀጥለው የጥበብ ጎዳና ይረማመዳሉ። በወላጆች ፍቅር ምክርና ማበረታቻ በመምህራን ተግሳጽና ጥረት ሕግና ሥርዓትን፤ መታዘዝና ማስተዋልን እያገናዘቡ ያድጋሉ።

በመምህራንና በተማሪዎች፤ በወላጆችና በልጆች መካከል ሊኖር የሚገባውን ቤተሰ ብአዊ ሕይወት ፍቅሩንና አክብሮቱን፤ ትህት ናውንና መተሳሰቡን በተግባር እየተለማ መዱት ያድጋሉ። በአካል እያደጉና እየጎለበቱ በሄዱ መጠን የሰብአዊነቱና የምግባረ ወንጌሉ ባህርይም በውስጣቸው ያድጋል። ይህም ወጣትነትን በሚፈታተነው ሥጋዊ ፈቃድ ላይ ድል እንዲቀዳጁና ፈቃድን የመግዛት አቅም እንዲኖራቸው ይረዳቸዋል። «ዓለምን ከመ ግዛት ይልቅ ፈቃድን መግዛት ይከብዳልና» በዘመናችን ብዙዎችን እንደ እሳት ራት እያከነፈ ወደ መከራ እሳት የሚጨምራቸው በነፍስ ፈቃድ ላይ የሚሠለጥነው የሥጋ





www.ethiopianorthodox.org

ፈቃድ ገዥነት ነው። ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ ሰውነትን (ሕይወትን) የጦር ሜዳ አድርገው ከሚታገሉ ሁለት ኃይሎች (የነፍስና የሥጋ ፈቃድ) ጦርነት የሚገላገል ይልቁንም በትግሉ አሸንፎ ወደ ጥፋት ከሚወስደው የሥጋ ፈቃድ ምርኮኝነት የሚያ ድነው በመሻት የሕሊና ጩኸት ድምጽ ያሰ ማው ትግሉና ፈተናው ቀላል አለመሆኑን ለሁ ላችን ጭምር ለማስተማር ነው። (ሮሜ. ፯፥ ፲፭–፳፬)

ቅዱስ ጳውሎስ እንዳመለከተው ካለው የሕይወት ፈተና ለመዳን የሚያስችል ትምህ ርትና ጥበብ ለዛሬው ወጣት ይኖራል። ቀደም ባለው ጊዜ ወላጆች፣ ቤተ ክርስቲያን እና ት/ቤቶች በስፋትም ኅብረተሰቡ በልጆች አያያዝና አስተዳደግ የተቀራረበ አመለካከትና ጥረት ነበራቸው። «አባትህንና እናትህን አክ ብር» የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ መሠረት አድርገው ልጆች ፍቅርን፣ ትህትናን፣ አክብሮትን፣ ፈሪሃ እግዚአብሔርን ተምረው የሚያስረግማቸውን ሳይሆን የሚያስመር ቃቸውን፣ የሚያስጠላቸውን ሳይሆን የሚያስ ወድዳቸውን ከነሱ የዕድሜ ደረጃ የሚጠ በቀውን መልካም ሥራ ሁሉ እየሠሩ እንዲያ ድጉ ያስቡላቸውና ይጨነቁላቸው ነበር። ወላጆችን ብቻ ሳይሆን በወላጆች ደረጃ ያሉ ትን፣ በዕድሜ ፀጋ የበለጸጉትን እንዲረዱ እንዲያከብሩና እንዲደግፉ ያስተምሩ ነበር።

ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤቶች ሌላ በዘመናዊ ትምህርት ቤቶች የሃይማኖትና የሥነ ምግባር ትምህርት ይሰጥ ነበር። ልጆች በፈሪሃ እግዚአብሔር ታንፀው ሥርዓትና ትህትናን የሀገርና የወገን ፍቅርን ተምረው ለራሳቸውም ለሌላውም የሚጠቅሙ ጣፋጭ ፍሬዎች እንዲ ሆኑ ብርቱ ጥረት ይደረግ ነበር። አእምሮ አቸው በሥነ ጥበብ ዕውቀት ብቻ የሚሞላ አልነበረም።

## የዛሬውስ ይዘት ምን ይመስላል?

ዛሬ ግን ያ ሁሉ የአስተዳደር ባህልና የጨዋነት ባህርይ ከብዙ አካባቢዎች እየሰከመና እየጠፋ፣ በተቃራኒው ልጅን ተቆጥቶና ቁጉ ጥሙ ማሳደግ እንደ ወንጀልና ኋላ ቀር ልማድ እየታሰበ ውግዘት የሚተላለፍበት ዘመናዊ ባህል ሆኗል። የትምህርቱ ሥርዓትና የአቀራረቡ ዘይቤ ሁሉ መልኩን እየለወጠ በብዙ ሁኔታ ማስተዋል እንደሚቻለው ብዙ ልጆች በወላጆች ደረጃ፣ ብዙ ደቀ መዛሙርትም በመምህራን ቦታ ተለዋውጠው የሚታዩበት ይመስላል። በሌላም በኩል ወላጆች በሽም ግልና ወራታቸው ከልጆች የሚጠብቁትን ድጋፍና እርዳታ በተገላቢጦሽ ልጆች ከወላጆች የሚጠብቁበት ጊዜ እንደሆነ በስፋት ይስተዋላል። ወላጅ አልባ የጭንቅና የግዳጅ ኑሮ የሚኖሩ ልጆችም ሁኔታ በኅብረተሰቡ የሕይወት ውርስ ቅብብሎች ውስጥ የራሱ የሆነ አሳሳቢና አደገኛ ክስተት እየተስፋፋበት የሚታይ ነው።

የክርስትናው እምነት መጠሪያ ስምና የአስተማሪው ብዛት የትምህርቱ ስርጭትም በዚያው መጠን ጎራ የሚያጋባና መንፈስን የሚያስጨንቅበት ዘመን ነው። ታዲያ በዚህ ሁኔታ «ከወጣቶች የሚጠበቅ ክርስቲያናዊ ግዴታ» ለተባለውና ግዴታው ምን እንደሆነ ምላሽ በመጠበቅ ለተቀመጠው ርእስ ትክክለኛ ነጥብ መጠቆም (ማስቀመጥ) የሚቻለው በየት ኛው መንደር በማንኛው የክርስትና ክልልና የአስተዳደግ ባህል ካደገው ክርስቲያናዊ ወጣት ነው?

ይሁንና ይህ ጥያቄ ወደሌላ አቅጣጫና ሰፊ ዝርዝር ሊወስደን ብዙም ሊያነጋግረን ስለሚችል የሆነው ቢሆን የተባለው ቢባል እኛ በምንከተለው መንገድ በኦርቶዶክስ መርከብ ከተሳፈረው ወጣት ስለሚጠበቀው ክርስቲያናዊ ግዴታ ጥቂት እንበል።

## የሚጠበቁ ግዴታዎች

- የእግዚአብሔርን ትእዛዝና የወላጆችን ፈቃድ መፈጸም፣ ለሰውም ለእግዚአብሔርም መታዘዝ በይስሐቅና በአብርሃም፣ በአብርሃምና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን የእምነት የፍቅርና የመታዘዝ ታሪክ ማስተዋል፣
- አብርሃም ከአባቱ አስበልጦ እግዚአብሔርን ወደደው፣ ከልጁም አስበልጦ ወደደው፣ መውደዱ (ፍቅሩ) ምን ያህል ጥልቀት እንዳለው ለማወቅ ተፈተነ፣ የእምነቱን መንገድ ምን ያህል እንደ ተመላለሰበት የቱን ያህል እግዚአብሔርን እንዳ ወቀው እንደተከተለው መረዳት የሚያስችል ነበር። ፈተናው አብርሃምን ጥሩ ሰው እንዲሆን ብቻ አይደለም። ትልቅ ሰው እንዲባልም ረድቶታል።

ወጣቱ ይስሐቅ («አባባ (አባዬ) እንጨቱ እሳቱ ስለቱ ይኸው አለ። የመሥዋዕቱ በግ ወዴት ነው? ብሎ አባቱን ይጠይቅ ነበር። ይህ አነጋገር ከወለዱት ካሳደጉትና ከሚወዱት ልጅ አንደበት ለወላጅ ሕሊና ሲቀርብ በይስሐቅ አንገት ላይ ሊያርፍ ከተሳለው ቢላዋ ይልቅ የአብርሃምን ልብን የሚሰነጥቅ ነበር። በጥልቀት ሊያስተውሉት የሚገባ ምስጢር አለው። በአብርሃምና በእግዚአብሔር መካከል የቆመ የእምነት መሰላል የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ አብርሃም የአብርሃም ሕይወት ወደ እግዚአብሔር የሚመላለስበት አብርሃምና እግዚአብሔር የሚተያዩበትና የሚነጋገሩበት የአብርሃምን ልብ ከእግዚአብሔር ጋር ያስተሳሰረ የፍቅር መውጫ መውረጃ። አብርሃም ከልጁ ፍቅር የእግዚአብሔርን ፍቅር ያበለጠበት የምስጢር መሰላል። ከሁላችንም ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ እንደሚቃጠል መስዋዕት ወደ ላይ የሚያርግ ልብ ይፈለጋል፣ ይጠበቃል፣ በየደረጃው ከወላጆች እንደ አብርሃም ከልጆች እንደ ይስሐቅ ያለ ፍቅር ታማኝነት፣ ታዛዥነትና መስዋእትነት።

አብርሃም ለእግዚአብሔር ይስሐቅ ለአብርሃም ታዘዙ የመታዘዛቸውንም ዋጋ ተቀብለዋል። ልጄ ሆይ «የመስዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል» ነበር ያለው በጊዜው በቦታው ሲደ ርሱ ግን በመጨረሻው «ልጄ ሆይ አትጎዳበትም ለመስዋዕት የቀረብከው አንተ ነህ አለው።» አብርሃም የ፩፻፸፭ ዓመት አረጋዊ፣ ይስሐቅ ከ፳፭–፴፫ ባለው የዕድሜ ክልል የነበረ ወጣት ነበር። ይስሐቅ በልቡ ከአባቱ ከአብርሃም ፈቃድና ውሳኔ፣ ፍቅርና ታዛዥነት ውጪ አልነበረም። ባይሆን ኖሮ ግን የወጣት ጉልበት ነበረው። ነጥቆ ለመሮጥ ሮጦ ለማምለጥ፣ አልሞከረም። አብርሃም ከላይ የተጠየቀውን መስዋዕት ለማቅረብና የታዘዘውን ለመፈጸም ለመስዋዕቱ የሚያደርገውን ዝግጅት ሁሉ ይስሐቅ በጥሞና ይከታተል ነበር። በመጨረሻ የዓይኖቹን መንከራተትና በአንገቱ ላይ ሊያርፍ የተሰናዳውን ስለት አገናዝቦ አባቱ አብርሃም የመሳሳትና የመጠራጠር ስሜት ፈተናውን እንዳያደናቅፈው አመቺ የሆነውን ምክር ከማካፈሉ በቀር ከይስሐቅ የቀረበ ተቃራኒ መንፈስ አልነበረም። የዓይኖቹ መንከራተት አሳዝኖህ መስዋዕትህን ከማቅረብ ወደኋላ እንዳትል በልቤ ደፍተህ ሠዋኝ ነበር ያለው። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ፣ የወላጅን ፈቃድ መፈጸም እንደዚህ ባለ ታዛዥነት ለመስዋዕት መቅረብ ነው ከወጣቶች የሚጠበቀው።



ወጣቶች (ልጆች) ይስሐቅን በሚያስ መስል የታዛዥነት ጠባይ ጸንተው ሲገኙ ለሕ ይወታቸው ቤዛ የሚሆን በረከትን ያገኛሉ። «የመስዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል» ብሎ ነበር፣ የመስዋዕት በግ ተዘጋጅቶ ቀረበ። «እጅህን በብላቴናው ላይ አትዘርጋ አንዳች ታደርግ ዘንድ» ነበር የተባለው። በዓለም ላይ ሁል ጊዜ መስዋዕትነት የሚጠይቅ ፈተና አለ። ፈተናውን መቋቋምና ማለፍ የሚቻለው በታዘዘውና በተጻፈው መሠረት ለእናትና አባት በመታዘዝ በምክራቸው በመጠቀም፣ የወላጆችን ፈቃድ በተአማኒነት በመፈጸም ነው። ወጣቶች በዓለም ላይ የሚከሰተውን የሕይወት ፈተና እሳቱን ስለቱን መቅሰፍቱን፣ ቅጣቱን ማለፍ የሚችሉት የሕይወት ቤዛ የሚያገኙት ለእግዚአብሔርና ለወላጆች ሲታ ዘዙ፣ የእግዚአብሔርንና የወላጆችን ፈቃድ ለመፈጸም ታማኞች ሆነው ሲገኙ ነው። (ዘፍ.፳፪፥ ፩–፲፩)

«የእግዚአብሔር መስዋዕቱ የዋህ ልቡና ነው» የተሰበረ መንፈስ ይሉታል። «እግዚአ ብሔር ትሁት ሰብእናን የዋህ ልቡናን አይን ቅም አያቃልልም» (መዝ.፶(፶፩)፥ ፲፯)

እግዚአብሔርን የማያውቁ ሰዎች ጥበብ የላቸውም፣ እግዚአብሔርን ካላወቁ ሊፈሩት ሊያከብሩት አይችሉም። እግዚአብሔርን የመ ፍራት ጥበብ በልባቸው ያላደረባቸው ሰዎች የጥበብን ፈለግ ሊያገኙት አይችሉም። ጥሩ ዕውቀትና ጥበብ ሁሉ የሚገኘው ከእውነተኛ ሃይማኖት ነው። የዕውቀት መሠረቱ ሃይማኖት ነው። እግዚአብሔርን ማወቅ ማመን መፍ ራትና መታዘዝ

«የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ቅዱሱንም ማወቅ ማስተዋል ነው። ዘመንህ በእኔ ይበዛል፣ የሕይወትህም ዕድሜ ይጨምርልሃል» (መዝ.፩፻፲፥ ፲፣ ምሳ.፲፯፥ ፱–፲)

ሌላው ከወጣቱ የሚጠበቀው ክርስቲያናዊ ግዴታ የክርስቲያንነትንና የሰብአዊነትን ድኅነት (Poverty of Christianity and poverty of humanism) ከአካባቢ በስፋትም ከዓለም ሕዝብ ልቡና ለማስወገድ በሥልትና በጥበብ መታገል ነው። በመምሰልና በመሆን፣ በመናገርና በመሥራት መካከል ያሉትን ልዩነቶች አበጥሮ በየመደባቸው ማስቀመጥ።

ክርስቲያንነት፣ ሰብአዊነት የሚባሉት ቃላት በሰፊው ይስተጋባሉ፤ ስማቸውና ድምፃቸው በምንተነፍሰው አየር መጠን ዓለምን ሞልቶታል። ከስሙና ከድምፁ ባሻገር የሚ ታየው ግን ከሁለቱም የሚጠበቀውን ያህል ሆኖ አይታይም። ለክርስትና ሕይወት ለሰብ አዊ እኀላገሎት ቆመናል የምንል ሁሉ ቃላቸ ንን በተግባር የማንተረጉምና በክርስትናውም ሆነ በሰብአዊነቱ ሌሎችን የማንጠቅምበትና የማንረዳበት ከሆነ ውጤቱ ኪሳራን እንጂ ትርፍን አያሳይም።

ክርስቲያናዊ ወጣት ይህን የኪሳራ መዝገብ መመርመር ክርስትናም ሆነ ሰብአ ዊነት በተግባር መገለጥ የሚኖርበት ታላቅ የሕይወት ምሥጢር መሆኑን ማረጋገጥ ነው።

- ከዚሁ በተቀራረበ መልኩ ሙቀትና ድምቀት፣ ውበትና ለዛ ልምላሜና ጽጌ እየተለየው እየገረጣና እየጠወለገ የሄደውን ኢትዮጵያዊ የጨዋነት ባህርይ ወደ ሕይወቱ ለመመለስ ለማደስና ትውልዱ እንዲያጌጥበት ለማድረግ መታገል፣
- አስቀድሞ ራስን ከስሕተትና ከጥፋት ሥራዎች በማራቅ ለክርስትናው እምነትና ትምህርት፣ ሕግና ሥርዓት በመቆም ግራ ቀኙን መመልከት፣ እያወቁም ይሁን ባለማ ወቅ በስህተትም ይሁን በድፍረት ወይም በሌላ የኑሮ ተጽእኖ የመቅሰፍትን ጅራት ለመጨበጥና ሞትን ያለወቅቱ ወደ ሕይወታቸው ለመጋበዝ የሚቀብጡትን ወጣቶች ለመመለስና ለማዳን ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ፣
- የዕድሜና የዕውቀት ሕፃናት የሆኑ ወገኖችን ከአስተሳሰብ ጀምሮ የአለባበስን፣ የአቈራረስን፣ የአነጋገርን፣ የአመለ ካከትንና ከሰው ጋር አብሮ የመኖርን የጨዋነት ባሕርይ ማስተማር፣ የሀገርና የሃይማኖት ፍቅር በሕሊና ሁሌዳቸው እንዲቀረጽና የነገ ታሪ ካቸው ተረካቢዎች የራሳቸው ባለቤቶች እንዲሆኑ ማድረግ፣
- የሰው አገር የሚያስናፍቁ፣ የሰው ኑሮ የሚያስመኙ፣ ዝንባሌዎችን መግታት፣ በትዕግሥት በመጽናትና ባለው በመርካት ከአጥር ውጪ የሚመለከቱ ዓይኖችን ወደ ውስጥ በመመለስ

«ከሰው ቤት...መረቁ

የእናት ቤት ይሻላል...ደረቁ» የሚለውን የእናት ፍቅር መዝሙር እየዘመሩ ደረት የዘንጋዳ እንጀራ እያቋሹ «ልጄ መች ደርሶ» በማለት በአንቃዕድዎ ልቡና፣ በስቂለ ሕሊና እየተጠባበቁ በችግር የሚንጠራወዙውን ወገን መርዳት፣ ከድኅነት አዘቅት ማውጣት

- በቅዱስ መጽሐፍ እንደ ተገለጠ በመካሊቱ እንጃር የተሰጠውን ዕውቀት፣ ጉልበት፣ የወጣትነት ጊዜ ተግባራዊ በማድረግ ብቻ በብዙ ሠርቶ ብዙ ማትረፍ ባይቻል ዋናውን ጠብቆ ለመገኘት ሰው መሆን ኢያንዳንዱ ወጣት (ሴቱ ወንዱ) እያንዳንዱ ሰው ዋናውን ማለት ራሱን ከጠበቀ ሁሉ ከጥፋት ይጠበቃል፤ አጥፊ ከሌለ ጥፋት የለም።
- ከዚህም ሁሉ ጋር በሃይማኖት መጽናት፣ ዛሬ ካንዱ ነገ ከሌላው እንደ ውሃ ቀጂ መመላለስን መተው፣ ፍቅረ እግዚአብ ሔርንና ፍቅረ ቢጽን እንደ አንገት ድሪ፣ እንደ ጆሮ ጉትቻ የሕይወት ጌጥ አድርጎ መያዝ፤ በራስ ከመመካት፣ በሰው ከመታ መን፣ በኃላፊ ሀብት ከመደገፍም ይልቅ በእግዚአብሔር መታመን፣ እሱን ተስፋ ማድረግ፣ ክርስትናን በተግባር መተርጎም እንደ ኖኅ ልጅ በአረጋውያን ከመሳቅ በእናትና አባት ስም ከመሳለቅ ታቅቦ ራስን ከሚያስነቅፉ ሥራዎች መራቅ ላስተዋለው ሰው እጥንትን የሚሰብር የእንደበት ፍላፃን ከትውልዱ እንደበት ማጥፋት ነው።

«እግዚአብሔር በተስፋ ለሚጠብቁት ለምትሻውም ነፍስ መልካም ነው። ሰው ዝም ብሎ የእግዚአብሔርን ማዳን ተስፋ ቢያደርግ፣ በትንሽነቱም ቀንበር መሸከምን ቢለምድ መልካም ነው» (ሰቆ.ኤር.፫፥ ፳፭–፳፰)

- በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ ቢጽ የታነጸ ሕይወት ያላቸው ወጣቶች ሌላውን ለመርዳት ኃላፊነትን ለመሸከም የሚያስ ችል ጉልበት ይኖራቸዋል። በሁሉም ተስፋቸው ብሩህ ነው። «ብላቴኖች ይደ ክማሉ፣ ይታክታሉ፣ ጎበዛዝትም ፈጽ መው ይወድቃሉ፣ እግዚአብሔርን በመተ ማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድ ሳሉ፣ እንደ ንስር በክንፍ ይሮጣሉ፣ አይታክቱም፣ ይሄዳሉ፣ አይደክሙም (ኢሳ.፵፥ ፴)። በእግዚአብሔር የሚያምን፣ ለእግዚአብሔር የሚታመን ልብ ያላቸው ወጣቶች ይዋደዳሉ፤ ይስማማሉ፤ በሕይወታቸውና በሞታቸው አይለያዩም። ከንስር ይልቅ ፈጣኖች ከአንበሳ ይልቅ ብርቱዎች ይሆናሉ። (፪ሳሙ.፩፥ ፳፫)

ወጣቶች ሆይ:-

«ሕዝብ ሁሉ እያንዳንዱ በየአምላኩ ስም ይሄዳል፤ እኛም በአምላካችን በእግዚአብ ሔር ስም እንሄዳለን» (ሚክ.፬፥ ፭) ✣



www.ethiopianorthodox.org

# እኔም መጣት ነበርኩ

## ድፍን አምሳ ዓመታት በቤተ ጉባኤ

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በእቅፍዋ የሚገኙ መተኪያ የማይገኝላቸው ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን አሏት። በየዘርፉ ታሪክን፣ ዜማን፣ ቅርስን፣ ትውፊትን፣ ታማኝነትን፣ ደግነትን፣ ሃይማኖትን፣ ባህልን ጠብቀው ለትውልድ ያስተላለፉ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ብዙ ናቸው። እንደ እድል ሆኖ እኛም ደርሰንባቸው ምሥጢርን ለመጠየቅ በቅተናል።

ከእነዚህ መካከል የተክሌው አርበኛ የአቋቋም ድምፀ ንጉድጓድ የኔታ ቤተ ማርያም ግዛው ናቸው።

የተክሌ ዝማሜ ሰምቻለሁ የሚል ሰው የኔታ ቤተ ማርያምን በሕሊናው ያስታውሳል።

የኔታ ቤተ ማርያም የተክሌ አቋቋምን ሊዘሙ ለተመለከተ ሰው መልአክ ሰማያዊ ናቸው ወይስ ምድራዊ ሰው? ብሎ መደነቁ አይቀርም። የተክሌ አቋቋም ለሳቸው፣ እሳቸውም ለተክሌ አቋቋም የተፈጠሩ ይመስላሉ። በእርግጥ የእግዚአብሔር ስጦታ ስለሆነ ከማድነቅ ሌላ ምን ማለት ይቻላል? ለዚህም ነው የአቋቋም ምስክር ለመሆን የበቁት።

የኔታ በትረማርያም ዛሬ የ፹፰ ዘመን የዕድሜ ባለጸጋ ሲሆኑ ጉባኤ ዘርግተው ማስተማር ከጀመሩ ድፍን ፶ ዓመታት ሆኖዋቸዋል። ዛሬም በማስተማር ላይ ይገኛሉ። ከእኚህ ታላቅ ሊቅ ብዙ እንግራለንና ለዛሬ እንግዳ አድርገን አቅርበናቸዋል።

«የብዕር ቅኝት መምህር ዕንቁባሕርይ ተከስተ»



ፈለገ ጥበብ – ከሕፃንነትዎ ጀምሮ እስከ ቤተ ጉባኤ ድረስ ያለው የወጣትነት ጊዜዎ ምን ይመስል እንደ ነበረ ዘርዘር አድርገው ቢገልጹልኝ፡

የኔታ ቤተማርያም – የተወለድኩት ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፱ ዓ.ም ነው። አባቴ አቶ ግዛው፣ እናቴ ወ/ሮ እትተ ማርያም ይባላሉ። ትምህርትን መማር የጀመርኩት በተወለድኩ በአራት ዓመቴ ነው። ከዚያ አያይዞ ከጉረቤ ታችን ንባብና ዳዊት፣ ሰዓታት የሚያስተምሩ መምህር ነበሩ። ከእሳቸው ንባብና ዳዊት ሰዓታት ተምሬያለሁ።

ፈለገ ጥበብ – ንባብና ዳዊት እንዲሁም ሰዓታት ከተማሩ በኋላ ወደ-ት ነው ያመሩ?

የኔታ ቤተማርያም – በ፲፫ ዓመቴ አቡነ ቄርሎስ ከሚባሉ ግብጻዊ ጳጳስ አዲስ አበባ መጥቼ ዲቁና ተቀበልኩ፣ ከዚያ በኋላ ፲፰ ዓመት እስኪሆነኝ ድረስ፣ ወንበርያ ሚካኤል አለቃ ጥበቡ ከሚባሉ መምህር ድጓ ተምሬአለሁ።

ፈለገ ጥበብ – ቅኔ በጣም እንደሚያውቁ ይነገራል። ቅኔን የተማሩት ከማን መምህርና በየትኛው ቦታ ነው?

የኔታ ቤተ ማርያም – ቅኔ መጀመሪያ እዚህ ደብረአሚን ተክለ ሃይማኖት የነበሩ፣ አባ ሀብተማርያም ከሚባሉ ባሕታዊ በጠላት ጊዜ ከጎጃም መጥተው የነበሩ ናቸው። ከትውልድ ሀገሬ ከይፋት በ፲፰ ዓመቴ ኮብልዬ ኤልሻማ መድኃኔዓለም ገባሁ። በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ጠላት በመጣ ጊዜም ሀገር ቤት (ይፋት) የተማርኩትን ዜማ ኤልሻማ ከነበሩት መምህር ጾመ ድጓና ምዕራፍ ከልሼ ተምሬአለሁ። በኋላ ጃንሆይ ጠላትን ድል አድርገው ሲመለሱ ኤልሻማ ከነበሩ አለቃ ምሥራቅ ከሚባሉ እንደ ገና ቅኔ ተምሬአለሁ።

ፈለገ ጥበብ – ከዚያ በመቀጠል ወዴት ነው ያመሩ?

የኔታ ቤተ ማርያም – በ፲፱፻፴፰ ዓ.ም ወደ ደብረ ታቦር በመጓዝ ከየኔታ አለቃ ቀለመወርቅ ወ/ሰንበት በደብረ ታቦር ከዚያ ቀደም በኤልሻማ መድኃኔዓለም ከነበሩት አለቃ ተክለማርያም ዘንድ ዘልቄው ስለ ነበር ብዙ አልፈጀብኝም ደብረ ታቦር የቆየሁ ለ፫ ዓመታት ብቻ ነው።

በሰኔ ወር ማለት በ፲፱፻፵፩ ዓ.ም ወደ ጉንደር ከተማ ሄድኩ። በዚያም ከየኔታ ክፍሌ በበዓታ የታች ቤት አቋቋም በመማር ወስኘ ውአለሁ። አሁንም ከዝማሜ በስተቀር ጸና ጽሉን ሁሉ የማስቀጽለው የበዓታ ቀለም ነው።



ፈለገ ጥበብ – ጉባኤ ዘርግተው ማስተማር ከጀመሩ ስንት ዘመን ሆኖዎታል?

የኔታ ቤተ ማርያም – ጉባኤ ዘርግቶ ማስተማር የጀመርኩት በ፲፱፻፵፫ ዓ.ም ነው። አሁን ድፍን ፶ ዓመታት ሆኖኛል።

ፈለገ ጥበብ – የእርስዎን ፈለግ ተከትለው ሙያዎትን ለማስተማር የበቁ ደቀ መዛሙርትና በትምህርት ጊዜዎ በጣም የሚያደንቁዋቸው የትምህርት ቤት ጓደኞችዎ መካከል ቢጠቅሱልኝ?

የኔታ ቤተ ማርያም – ደቀ መዛሙርቱ ብዛታቸው በቁጥር አላውቃቸውም፣ ጉባኤ ሲሠፉ ከ፩፻፶ – ፪፻ ይደርሳል። ልጁ እኛ ማስተማር እንጂ ተማሪዎቻችን በቁጥር ወስነን እና ውቃቸውም ነበር። ከታዋቂ ሰዎች ሌላከው

ደብረ ሊባኖስ የሚያስተምረው እዚህ ታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም ሆኖ ያስተምር የነበረው ፍቅረ ማርያም እኔ ያስተማርኳቸው ናቸው።

ፈለገ ጥበብ – የኔታ? የተክሌ አቋቋም ከሌላው የአቋቋም ትምህርት የተለየ ጠባይና ይትበሐል ካለው ቢያስረዱኝ?

የኔታ ቤተማርያም – የአለቃ ተክሌ አቋቋም መነሻው ወይም መሠረት አድርጎ የተነሣው የቆሜ ዜማ ነው የሚባለው፤ ድምጹ ረዘም ይላል?

ፈለገ ጥበብ – ከሌላ ባይቀራረብም ከላይ ቤት ጋር የሚለየው ምንድነው? ቀደም ሲል በየኔታ እንደሻውና፣ በመሳሰሉት ሊቃውንት ጊዜ ባህሉ ነበረ ወይ? ከዚህ ሌላ የተክሌ አቋቋም እድገቱ ከመቼ ጀምሮ ነው?

የኔታ ቤተ ማርያም – የተክሌ ዝማሜ እኔ እንደ ሰማሁት በራስ ጉግሣ ጊዜ ነው። በደብረ ታቦር የተገለጠው፣ ፊት በጉንደር ለክብረ በዓል የሚሆን የማኅበር ቀለም ነው እንጂ ላይ ደግሞ እነ አለቃ መኮንን፣ እነ አለቃ በሪሁን፣ የእኛ መምህር የተማሩባቸው አለቃ መኮንን የጉንደር ቀለም ያውቁ ስለ ነበረ ትንሽም አጠር አጠር አድርገው ያደራጁት አለቃ መኮንን ናቸው። ማለት ያዘጋጁት፤ ያደራጁት።

ፈለገ ጥበብ – በዚህ ቅርብ ጊዜ የተክሌ አቋቋም ወስኖ የያዘ «ፍሬ ማኅሌት» የተሰኘው መጽሐፍ አሳትመዋል። ስለዚሁ መጽሐፍ ዋና ዓላማ ዘርዘር አድርገው ቢገልጹልኝ?

የኔታ ቤተ ማርያም – መጽሐፉ ከታች ቤት የግእዝንም የዓራራይንም፣ የዕዝልንም በተክሌ እንለየዋለን። ከበዓታ የሚለየው ሁሉ በመግለጫ አድርጌ አዋጄን አውጥቼአለሁ። በቀለም ቁጥር ሁሉ አንድ ቀለም ሁለት ቀለም፣ እያልኩ (እንደ ዜማ ልክ) ማለት ነው። ለሕትመቱ የረዱኝ የመንፈስ ቅዱስ ወንድሞቼ ናቸው በተለይ የመንፈስ ቅዱስ ለትውልድም እንዲተላለፍ በማሰብ ነው ያሳተምኩት።

ፈለገ ጥበብ – በአሁኑ ጊዜ የአቋቋም ትምህርት የተለያየ ነው ለምሳሌ ፋኖ፣ ታች ቤት፣ ላይ ቤት፣ ተክሌ ሳንኳ የሚባሉ ዜማዎችና ይትባሐሎች አሉ። ስለዚህ ለወደፊቱ ተማሪውም እንዳይደክም፣ አገልግሎቱም አንድ ዓይነት እንዲሆን፣ መለያየትም እንዳይፈጠር እነዚህን ሁሉ በአንድ ዓይነት ተቀምረው እንዲዘጋጁ ለማድረግ ምን ዓይነት ስልት ብንጠቀም ይሻላል ብለው ያምናሉ።

የኔታ ቤተ ማርያም – እይ ለመስተካከል አሁንም እግዚአብሔር አስተካክሎት የለ? እግዚአብሔር አስተካክሎታል ማለት ላይ ቤት ነበር። መምህራኑ (ሊቃውንቶች) አልቀዋል አሁን ያለው በፈጠራ ነው። ልብ ወለድ እየሆነ እያስተባበርም ምንጩ ከዚያ ደርቋል። እንግዲህ ዛሬ የታች ቤትና በእኛ በኩል የአለቃ ተክሌ ዘንጉ ብቻ ነው ያለው እኔ አሁን በዝማሜ ጊዜ ጉሮሮው የአለቃ ተክሌ ነው በባህል ግን በበዓታ ነው። በዓቶች የሚዘሙትን እዘማለሁ እነሱ የሚተውትን እተዋለሁ። ባህሉ በዚያ ነው።

ሊቃውንት እንደገና ቢሰበሰቡ የላይ ቤቱ ይታደስ ነበር። ላይ ቤቶች ይቅርባችሁ ቢባሉ ዓመቱን እየጠበቁ ቢያውቁትም ባያውቁትም በጅ አይሉም፣ በዚያ ነው የሚሄዱት። ሳንኳውም ያው ራሱን ችሎ ነው ያለው ዓይነቱ ብዙ ነው።

ፈለገ ጥበብ – በትምህርት ዘመንዎ ያጋጠመዎት ገጠመኝ ካሉት ትንሽ ቢጠቅሱልኝ?

የኔታ ቤተ ማርያም – ጨለማና ብርሃን እንደሚፈራረቅ በሰው ልጅም ሐዘንና ደስታ ይፈራረቃሉ። በእኔም ብዙ ሐዘንና መከራ ገጥሞኛል። እዚህ ላይ መዘርዘር ግን አይጠቅምም።

ፈለገ ጥበብ – የኔታ ከዚያ ከቅኔ ማዕበሉ አንድ ሁለት ቢሉኝ?

የኔታ ቤተ ማርያም



ቤት፣ ታች ቤት የሚባለው የነበረ የመጻሕፍት ቤት መጠሪያ ነው። ታች ቤት እንዲህ ይሉታል፣ ላይ ቤት እንዲህ ይሉታል ይባል ነበር እንጂ የአቋቋም ቤት መጠሪያ አልነበረም። አለቃ ተክሌ ከበዓታ ጉንደር ነው ተምረው የመጡት አለቃ ገብረ ሐና የአለቃ ተክሌ አባት ናቸው እሳቸው ከጣና መጻሕፍት ተመረው ሲመጡ አንድ የበቃ ባሕታዊ በአንተ አይነገርም በልጅህ ይነገራል ብሎ ተማርና ሂድ ስላላቸው አለቃ ገብረሐና ከእሳቸው ተምረው ልጃቸውን አስተምርዋል። በኋላ እየተስፋፋ ሊቃውንት ልጁ መልአክ ምሕረት ምሕረቱ በእርሱ ድካምና ጥረት ነው ለሕትመቱ የበቃው እግዚአብሔር ይርዳው። በመጀመሪያ መጽሐፉ ሲጻፍ ተበላሽብን፣ ዓምድ አልነበረውም፣ ፎቶ ለማስገባት አይመችም ነበር። እንደገና እንደ አዲስ ተጽፎ አሁን ባለው መልኩ እንዲታተም ሆኖአል። ለጊዜው ፪ ሺህ ኮፒ ነው የታተመው። የመጽሐፉ ስርጭት እንደሚፈለገው መልኩ አልተሰራጨም። ዋና ዓላማው ግን ከአሁን ጀምር የሚማር ተማሪ እገዛ እንዲሆነው፣ ለተማሩት ደግሞ ማስታወሻ እንዲሆናቸውና

### ዋዜማ ቅኔ

በምክረ ሚካኤል ወምልክአም
ኢትፀግብ ሰብእ ባሕረ ኤርትራ እሐቲ
ንጉሥ ምስለ ሠራዊቱ እስመ ቦአ ባቲ
ወዘእስራኤል አዕራረ እመ ደመሰሰት ይእቲ
እስራኤል ይብልዋ ዘመድነ አንቲ
ፍዳሆሙ እስመ ሜጠት ዛቲ

### ዋዜማ

ይቤሉሙ ለእሊዓሁ ኢሎ ፍላውያን ዳጎን
ኢትርሰ ኡኒ እም ዮም

www.ethiopianorthodox.org

ሌሊተ እስመ ቀጥቀጠኒ ኃይለ ፅዮን ህልም.
ወእንበለ መንፀፍ ሰከበ ላዕለ ፀበለ ምድር ህርቱም
እንዘ ተማህልሎ ይገብር ኀበ ማርያም
ቅጥቃጤሁ አኮኑ ግሩም

## መወድስ

ሲሣየ ዕለት ንጎሥሥ እመ ተጋባዕነ
ውስተ ደብረ ጽጌ ሐዲስ ካህናተ ፍጽም ወከዋላ
ኢይፍትሑ ብነ ጠበብተ ዓለም ኮላ
እስመ ኀበ ሀሎ ቅርፍተ ሥጋ
ይትጋብኡ አንሰር ተሰማይ ዘአልቦሙ ተድላ
ወየአግትዋ በምልእሙ
ርኁባን አዕዋፍ ለእንተ ፈረየትእመ ሠግላ
ኢንቅስምሂ ወኢንእርር እምገራኅተ ጽልመት ወግላ
ህየንተ ሥርናይ ብዝኃ ክርዳድ ወህየንተ ወይን አሚካላ
ለቤተክርስቲያን እምኑ በተፋቅሮ ናልዕላ
እስመ ወለደነ እምኔሃ ክርስቶስ ርእሰ መሐላ

## የአማርኛ መወድስ

ሀገረ ኢያሱ ጐንደር የጥበብ መፍለቂያ
የባረ ከሸን አምላክ እያመሰገንኩ ዛሬ
ታሪክሽን ሁሉ ልንገር ከደብረ ታቦር ጀምሬ
አንቺ ነሽና ብርሃናቸው
ለጐጀም፣ ለሸዋ፣ ለወሎ ለትግሬ፣
እንዲነገሩብሽ ጢትና ማታ
ድጓ፣ ጾመድጓ ምዕራፍ፣ መዋስዕት ወዝማሬ።
የአቋቋምሂ መምህራንሽ ተክሌ ጦጐንደሬ
ቀኝ ጌታ ላቀው ወመምህር ክፍሌ
አለቃ መኮንን አለቃ ብሬ
እንዳይገባብሽ ደግሞም የሚያስመስል ዱር አውሬ
ያባርርዋል እየተዋጋ የመጽሐፍ መምህርሽ ቀዳሙ በሬ።

## ክብር ይእቲ

ተሠወረ ግበ ፈራሒ መኮንነ ላዕሉ ኮከብ
እስመ ድምፀ ኮናት ተሰምዐ በገቦ ኢየሱስ መርህብ
ወታፈሪ ሎሙ እስካለ በረከት ለሕዝብ
እንተበስሉሰ ትትገመድ ሐረገ ወይን ቀትረ ዕለታ ለአርብ

## እጣነ ሞገር

ተሰርገወት ምድር ልበ ሐዋርያት ሐዲስ
በሥነ ጽጌሁ ለጌር ጰራቅሊጦስ
አምጣነ ሐለፈ በጊዜሁ ክረምተ ልምላሜ ግሁስ
ወቃለ ማዕነቅ መንፈስ ቅዱስ
በምድረ ገሊላ ተሰምዐ አኮኑ ሠርፀ ልምላሜሃ ለነፍስ
አውፀአ ዘሐዋርያት ሰብእና በለሰ
ተፈወሰ ፈውስ ዓለመ ሥጋ ሕሙመ ተስናን ወባዕስ
እስመ ወሐብዎ ሣዶቅ ወሐና ጠባብተ ፐኢና ወፈውሰ
ዘኮሉ ተሐዩ ዕፀ ጳጦስ
ወማህደረስብሐት ኮነት ከመ ሊባኖስ
እስመ ዛቲ ዘድንግል ተሰላስ

ፈለገ ጥበብ – በመጨረሻ ለሊቃውንት፣
ለወጣቱም፣ ለመሰል ጓደኞችዎም ሊያስተላልፉት የሚፈልጉት መልእክት ካለ?

የኔታ ቤተ ማርያም – የማስተላልፈው መልእክት ይህን መጽሐፍ ያዘጋጀሁት ከሰው እበልጣለሁ ብዬ አይደለም፣ ከመምህራኖቼ እንደበት የወጣውን ቃለ እግዚአብሔር ጽፌ ነበርና በዚህ ዓይነት ያ ከአባቶቼ የቀሰምኩትን ቃለ እግዚአብሔር በሕትመት ላይ በመዋሉ ፈጣሪ እግዚአብሔርን አመሰግናዋለሁ። ከዚ ህም ሌላ የታተመውን መጽሐፍ የቤተክ ርስቲያን ልጅ ሁሉ አንብቦ እንዲጠቀምበት መልእክቴን አስተላልፋለሁ ከሁሉም በላይ ግን አሁንም እግዚአብሔርን ደግሜ አመሰግነዋለሁ። ✣

## መልእክት ለአንባብያን

የፈለገ ጥበብ መጽሔት ቋሚ ደንበኛ ለመሆን ለምትፈልጉ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች የሚከተለውን የክፍያ መጠን በመፈጸም መጽሔቱን በየ3 ወሩ ማግኘት የምትችሉ መሆናችሁን እየገለጽን፣

ደንበኞች ክፍያውን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራት ኪሎ ቅርንጫፍ ለሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሂሳብ ቁጥር 1955 ገቢ በማድረግ የከፈላችሁበት ደረሰኝና ሙሉ ስማችሁን ከነ አድራሻችሁ በፖስታ ሳጥን ቁጥር 81286 መላክ የምትችሉ መሆናችሁን የምናረጋግጠው በደስታ ነው።

| ቦታ | የሁለት እትም ግማሽ ዓመት | የአራት እትም የዓመት |
|---|---|---|
| አዲስ አበባ | 6.25 | 12.50 |
| ክፍለ ሀገር | 7.00 | 14.30 |
| ውጭ ሀገር | 4 ዶላር | 8 ዶላር |

በተጨማሪ በደርዘን ለመውሰድ የሚፈልጉ ደምበኞቻችን በቅናሽ ዋጋ ጠቅላይ ቤተክህነት በሚገኘው ቢሮአችን ብቅ ቢሉ የፈለጉትን ያገኛሉ።

በአዲስ አበባ ሆነው መመዝገብ የሚፈልጉም በአካል ቀርበው መመዝገብ የሚችሉ መሆኑን እንገልጻለን።

# ዜና መጽሔት

## የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ የማዕከላዊ መዘምራንን አስመረቀ



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሐምሌ ፳፰ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በመንበረ ፓትርካናው የቅዱስ ሲኖዶስ አዳ ራሽ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፣ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ የቤተ ክህነት የየመምሪያው ኃላፊዎች፣ የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት ኃላፊዎችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት ከሁሉም የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት ለተውጣጡ ፻፭ ወጣቶች መዘምራን ቅዳሜ ቅዳሜ ለ፫ መቶ ቀናት በመዝሙር ያሰለጠናቸውን የምስክር ወረቀት ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ እንዲቀበሉ በማድረግ በደማቅ ሁኔታ አስመርቋል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የምስክር ወረቀት ከሰጡ በኋላ ለተመራቂዎች የሰጡት መመሪያ «እናንተ ዕድል ገጥሟችሁ መምህራን ተዘጋጅቶላችሁ ትምህርታችሁ እዚሁ ተምራችኋል። አባቶቻችን ግን ትምህርትን ለማግኘት ከሀገር ወደ ሀገር ተንከራትተው ነው ይህን ምሥጢርና ትምህርት ለእናንተ ያስተላለፉት።

ስለዚህ የአባቶቻችሁን ፈለግ እየተ ከተላችሁ ሃይማኖታችሁን፣ አንድነታችሁን፣ አጽንታችሁ ያዙ፣ የተማራችሁትን ትምህርት ለጓደኞቻችሁ አስተምሩ» ሲሉ አባታዊ መመሪያ ሰጥተዋል።

### ለየሀገረ አኅጉረ ስብከቱ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ኃላፊዎች ሴሚናር ተሰጠ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደ ራጃና ማስተባበሪያ መምሪያ ለየሀገረ ስብከቱ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ኃላፊዎች ሐምሌ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም የአንድ ቀን ሴሚናር ሰጥ ቷል። በሴሚናሩ የቀረበው ዋና ርእሰ ጉዳይ፦

፩. የሰንበት ትምህርት ቤቶች ዓላማና ደንብ፣ ከየሀገረ ስብከቱ የሰንበት ት/ቤቶች ኃላፊዎች ከማደራጃና ማስተባበሪያ ጋር ሊኖ ራቸው የሚገባ የሥራ ግንኙነት፣ በሊቀ ካህ ናት ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃና ማስተባበሪያ ዋና ኃላፊ፤

፪. የሰንበት ትምህርት ቤቶች እንቅ ስቃሴ፣ ችግሮቻቸውና መፍትሔው በመም ሀር ዕንቁ ባሕርይ ተከሥተ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃና ማስተባበሪያ መምሪያ ምክ ትል ኃላፊ የቀረቡ ሲሆን በውይይቱ ጊዜ ጠን ካራ የፍክክር መንፈስ የታየበት እንደነበር ከሥልጠናው ተሳታፊዎች ያቀርቡት ከነበረው ሐሳብ ለመረዳት ተችሏል። በመጨረሻም የጉባኤው ተሣታፊዎች ይህን የመሰለ ዓውደ ጥናት በየጊዜው መዘጋጀት እንዳለበት አበክረው አሳስቧል።

### በያቬሎ ካስተዋልኩት

በዘንድሮው ዓመት ጾመ ማርያም (ፍልሰታ) በተለያዩ አህጉረ ስብከት ትምህርተ ወንጌል ለምእመናን እንድንሰጥ ተመድበን ስምሪት አድርገናል።

እኔም በቦረና ሀገረ ስብከት በያቬሎ ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስ ቲያንና አካባቢዋ ተመድቤ ሁለ ገብ አገል ግሎት በመስጠት ሰንብቻለሁ።

በከተማዋ ያለችው ብቸኛ ቤተ ክርስ ቲያን ቅድስት ማርያም ስትሆን አሠራሯም እጅግ ማራኪና ዘመናዊ ነው በአካባቢው ምእ መናን አስተዋጽኦና በሰን ሻይን ኮንስትራክሽን ባለቤት አማካይነት ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ ተሠ ርቶ ከሁለት ዓመታት በፊት አገልግሎት ጀምሯል።

ሕዝበ ክርስቲያኑ ለእምነቱ ያለውው ፍቅር እጅግ ጽኑእ ነው። በሌሊት ሲጸልይ ያድራል፣ ጠዋት ምህላ የተለመደ ስለሆነ ለም ህላ ይሰበሰባል። የቅዳሴው ሰዓት ከመድረሱ በፊት ሕዝቡ ተሰብስቦ የውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም ትርጉም ያዳምጣል። ከቅዳ ሴው በኋላ በሰርክ ለትምህርተ ወንጌልና ምህላ ይሰበሰባል። ትምህርት ያዳምጣል፣ ለትምህ ርተ ወንጌል ልዩ ፍቅር ያለው ሕዝብ ነው።

የወጣቱም እንቅስቃሴ ልዩ ነው በሰንበት ት/ቤት ውስጥ ይማማራሉ፣ ቤተ ክርስቲያ ናቸውን ባላቸው ሁሉ ያገለግላሉ፣ በስብከተ ወንጌል ይሳተፋሉ፣ ይዘምራሉ፣ ከዚህም በተ ጨማሪ አረጋውያንንና ነዳያንን ይንከባከባሉ። ባጠቃላይ አገልግሎት ለመስጠት ሲፋጠኑ በጣም ደስ ያሰኛል።

ሌሎቻችንም በየደረጃችን ለአገልግሎት እንድንሰለፍ፣ መናፍቃንን እንድንከላከል እና ቤተ ክርስቲያናችንን እንድናገለግል የሚጠ በቅብን መሆኑን መገንዘብ አለብን።

መ/ር አምሳሉ ተፈራ

የስብከተ ወንጌል መምሪያ ዋና ጸሐፊ

www.ethiopianorthodox.org

# እስትጉቡእ

(እስትጉቡእ - ጥርቅም፣ የተቀመመ፣ የተሰባሰበ ማስት ነው)

## የእመቤታችን ተአምር በሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አ ሜን

ስመ ክርስትናዬ ኃይለ ጊዮርጊስ ይባላል የመጣሁት ከኮልፌ አካባቢ ነው። እመቤቴ ቅድስት ማርያም ኪዳነ ምሕረት ያደረገችልኝን ታምር ይህ ነው። ለረጅም ጊዜያት ሲያሰቃየኝ የነበረው ራስ ምታት በሽታ ነበረብኝ። ሐኪም ቤት ስሄድ የነርቭ በሽታ ነው ብለውኝ ከአንድ ወር በኋላ ተመለስህ ና ብለውኝ ቀጠሮውን ጠብቄ ሐምሌ ፴ ቀን መድኃኒቱን ሰጡኝ። ለአሥራ አምስት ቀን ያህል ሳታቋርጥ ውሰድ አሉኝ። ይህን ነገር እንደ ነገሩኝ ለምወደው መንፈሳዊ ጓደኛዬ ስነግረው አይሆንም መድኃኒቱ ሊያድንህ አይችልም፤ ከነገው ቀን ጀምረህ ኪዳነ ምሕረት ፀበል ሳታቋርጥ ጠጣ ንስሐ ግባና፣ ጹም፣ ጸልይ፣ ስገድ፣ ትፈውስሃለች ብሎ ነገረኝ። መከረኝ። እኔም አመንትቼ መጨረሻ ባለኝ ሐሳብ ተስማምቼ አምኜ ሳላቋርጥ ጠበልዋን ጠጣሁ እርሷም ይቅርባይ ናትና ማረችኝ በጣም ድኛለሁ። አሁንም ጤንነቴን ታጸናልኝ ዘንድ ምእመናን ሁሉ በጸሎት አስቡኝ።

## የእስልምና ተከታዮች ወደ ክርስትና ተመለሱ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፤

፩. የመጀመሪያው ስሜ መሐመድ ሐጂ አቡና የዛሬው ስሜ ኃይለሚካኤል፤

፪. የመጀመሪያው ስሜ መዲና ሐጂ አቡና የዛሬው ስሜ እኅተ ማርያም፤

፫. የመጀመሪያው ስሜ ዘሀራ ሐጂ አቡና የዛሬው ስሜ ወለተ መድህን፤

በእግዚአብሔር ቸርነት በእመቤታችን አማላጅነት ከጭለማ ወደ ብርሃን ከሞት ወደ ሕይወት ከክህደት ወደ እምነት ተመልሰን ከክርስቶስ ቤተሰቦች ተቀላቅለን በስላሴ ስም ተጠምቀን በሕይወት መንገድ ላይ እንገኛለን። እስከ ዛሬ በ፩ ሺህ ፰፻ አቢያተ ክርስቲያናት ተዘዋውረን ምስክርነትን ሠጥተናል። የተነሣነው ከባሌ ክፍለ ሀገር ነው።

ስለዚህ ክርስቲያኖች በእምነታችን እንድንፀናና የጠፉት ቤተሰቦቻችን (ወገኖቻችን) ሁሉ ወደ እውነት መንገድ ወደ ተዋህዶ እምነት እግዚአብሔር እንዲመልሳቸው በጸሎታችሁ አስቡን።

የምንገኘው ገዳም ነው። ዝቋላ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ

## የቅዱስ ገብርኤል ተአምር በቁልቢ

ይድረስ ለመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል

ይድረስ ለመላኩ ቅዱስ ገብርኤል ከዚህ በፊት የጠየቅንህን ሁሉ ፈጽመህልናል። አንተን የሰጠን አምላክ ይክበር ይመስገን። አሁንም የልቡናችንን ፍላጐት ሁሉ አማልደህ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈጽምልን። አሜን።

ኃ/ማርያም እና ፍቅርተ ማርያ

## ቊልቢው ቅዱስ ገብርኤል ተስየ ሴት ልጅ ወለድኩ ከሞትም አዳነችኝ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ እግዚአብሔር በሰላም ሰብስቦ እድሜውን ሰጥቶን ለዚህ ያደረሰን አምላክ ይመስገን።

እኔ ይህን ደብዳቤ የምጽፈው ቸሩ እግዚአብሔር ለሰጠኝ ነገር ሁሉ ተመስገን እያልኩኝ ስዘምር በእግዚአብሔር ደስ እያለኝ ነው።

እህቶቼ ወንድሞቼ እግዚአብሔርን ወዳጅ የሆናችሁ ሁሉ እግዚአብሔር ለእኔ ያደረገልኝን ውለታ መክፈል ባልችልም መመስከር አለብኝ።

ለቊልቢ ገብርኤል እደጅ መጥቼ በ፲፱፻፺ ዓ.ም ማለት ነው ስለት ተስዬ ነበር ያኔ ስሳል ቅሪት ነበርኩኝ። በመጀመሪያ ወልጄ ሙቶ ብኛል። እና ለምርመራ ሐኪም ቤት ስሄድ በምርመራ አሁንም ብትወልጂ አያድግም፤ ለወደፊቱ ግን መድኃኒት ይደረግልሻል ተብዬ በጣም አዘንኩ። ቊልቢ ገብርኤል መጥቼ አለቀስኩ ነገርኩት ወንድም ይሁን ሴት የምወልደውን ልጅ ባለሁበት ቦታ ለገብርኤል ክርስትና እሰጣለሁ ብዬ ተሣልኩ ይኸው በዚያው በ፲፱፻፺ ዓ.ም በነሐሴ ወር ሴት ልጅ ወለድኩ። ባለሁበት ቦታ በናዝሬት ገብርኤል ክርስትና ለቅዱስ ገብርኤል ሰጥቼ ልጄም ይኸው እግዚአብሔር በፈቀደ በነሐሴ ወር ፫ ዓመት ይሆናታል። በቅዱስ ገብርኤል አማላጅነት እግዚአብሔር ልቅሶዬን ሰምቶ የምስመው ልጅ ሰጥቶ አሳድጎልኛል። ለወደ ፊትም እግዚአብሔር ተስፋዬ ነው። እግዚአብሔር ይመስገን አሁን ደግሞ ቅዱስ ገብርኤል ልጄን ይዤ መጥቼ ደጁን እንድረግጥ የእሱ ፈቃድ ይሁን።

እህታችሁ ከናዝሬት

ስሜ እግዚአብሔር ያውቀዋል።

## ስእለቴን አቅርቤአለሁ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ

የኪዳነ ምሕረት ተአምር ዘርዝሬ ባልዘልቀውም በ፲፱፻፺፱ ዓ.ም አጋማሽ ላይ በራስ ቅል ውስጥ በተፈጠረው እጢ አማካኝነት ዐይኔ ከመታወሩም አልፎ ሐኪሞች ለሕይወቴ ቴስፋ ባልቆረጡኝ ወቅት ለኪዳነ ምሕረት ነገርኳት።

፩. በሽታው ወዲያው እንዲታወቅ ረዳችኝ፤

፪. የምታከምበትን ከፍተኛ ገንዘብ ረዳችኝ።

፫. ደቡብ አፍሪካ ሄጄ እጢው ወጥቶ ምንም ዐይኔስውር ቢያደርገኝም ለሕይወቴ ረዳችኝ። ስለዚህ በዛሬ ዕለት ለክብርዋ የሚሆን ስእለቴን አቅርቤአለሁ። ልመናዋ፣ ፍቅርዋ እና ምህረትዋ ልትእኔ እንደሂን ሁሉ ለሁላችሁም ይሁን አሜን።

ዓለማየሁ አጉናፍር

## የቅዱስ ዑራኤል ተአምር

## ቅዱስ ዑራኤል ሆደ በሽተኛዋን በሻማ እሳቱ ፈወሰ



[illegible]

[illegible] ቀን ጀምሬ ለ፫ ቀናት እስከ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ድረስ ከጥቶኩ በኋላ ሐምሌ ፳፩ ቀን ታናሽ እኅቴ ለማርያም በተሳለችው መሠረት ከማርያም ስትመጣ ወላጅ አባቴ ከቅዱስ ዑራኤል የመጣ ሻማ ስለሆነ ሆዴን ትሸበት ብሎ ልኮልኝ ስለ ነበር ሆዴ እስከ ሐምሌ ፳፩ ቀን ማታ ፫ ሰዓት ድረስ በግምት የ፰ ወር እርጉዝ ያክል ነበር። ከዚያም በሻማው ሆዴን አሸቼው ፰ ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ፪ ሰዎች ባሉበት እብጠቱ የት እንደ ገባ ሳይታወቅ በአስደናቂ ፍጥነትና ሁኔታ ሆዴና ጀርባዬ የተጣበቀ መሰለ እኔም ሆንኩ አብረውኝ የነበሩት ሰዎች በጣም ደነገጥን። ቀደም ብዬም ዑራኤል በ፳፪/፲፩/፲፱፻፺፫ ለማስቀደስ አስቤ ስለ ነበር በአራት ወር ሰውነቴ አልቆ በጀርባዬ ብቻ የምተኛና መቆም፤ መቀመጥና መተኛት የማልችል እንዲሁም ለ፪ ወራት ምግብ ሳልቀምስ ቆይቼ ከሌሊቱ ፲፡፴ ብቻዬን ዑራኤል ሳስቀድስ በመስቀል ታሸቼና ፀበል ተረጭቼ ያንን ሁሉ ግፊያ ችዬው የፓትርያርኩን መስቀል ተሳልሜ ወደ ቤቴ ተመለስኩ። ግን ሐኪሙም ሆነ ሁሉም ሰው መድኃኒቱ መቋረጥ እንደሌለበት በጥብቅ ስላስጠነቀቁኝና ጭንቀት ስለያዘኝ መድኃኒቱ እንደሚጐዳኝ እየታወቀኝ መድኃኒቱን ለመቀጠል ብሞክርም ከዚያ ቀን ጀምሮ የምወስደው መድኃኒት ተመልሶ የሚወጣ ሲሆን የምበላው ምግብ ግን አይወጣም። ከዚያም በ፳፭/፲፩/፺፫ ሐኪሙ ዘንድ ቀርቤ ሲያዩኝና ሁኔታውን ስነግራቸው ከአሁን በፊት ያላጋጠማቸው ታሪክ በመሆኑ በጣም ተገረሙ። ሆኖም በሽታው ባልታወቀ ተአምር የጠፋ ቢመስላቸውም ሙሉ ምርመራ ሳላደርግ መድኃኒቱን ማቋረጥ በጣም አደገኛ ሊሆን እንደሚችልና ሕክምናውም ... ቢሆን ከእግዚአብሔር ጥበብ ውጪ እንዳልሆነ ቢያስረዱኝም መድኃኒቱ በጣም እየጐዳኝና በሙሉ እየወጣ ስለታመምኩኝ ይህንኑ ለሐኪሙ ስነግራቸው መድኃኒቱ ተመልሶ እንዳይወጣ የሚረዳ መድኃኒት አዘዙልኝ ምግብ ከመብላቴ ፴ ደቂቃ በፊት ወስጄው ከዚያም ከምግብ በኋላ መድኃኒቱን ብወስድ እንደማይወጣ ቢነግሩኝም መጀመሪያ ከ፴ ደቂቃ በፊት የዋጥኩት መድኃኒትና በኋላ የምወስዳቸው መድኃኒቶች ሲወጡ የምበላው ምግብ ግን አይወጣም ነበር።

ከዚያም በ፳፯/፲፩/፺፫ በ፫ ሰዓት ሙሉ ምርመራ ተደርጐልኝ ከምርመራው ክፍል እንደወጣሁ ከአፍንጫዬ ከመሀል ምላሴና ከውስጥ ጉንጩ ላይ ደም ይወጣ ነበር!! እንዲሁም ፊቴ ላይ አንገቴ ላይ ሆዴ ላይና እግሮቼ ላይ የደም ነጠብጣብና የበለዘ ምልክት ወጣብኝ ሐኪሙም በውጤቱ መሠረት ባልታወቀ ተአምር በሽታው ከሰውነቴ እንደወጣና መድኃኒቱንም ወዲያው እንዳቆም አዘዘኝ። ነገር ግን ባልታወቀ ምክንያትና ፍጥነት ከ፲ ቀን በፊት ንጹሕ የነበረው ጉበቴ በጣም እንደ ተጐዳና ዓይኔም ቢጫ መሆኑን ተመለከተ። ምክንያቱንም ለማወቅ መዛሪያው ወደሚገኝበት ቤተ ዛታ ክሊኒክ ብላከም ወደ ቤት ተመልሼ በሻማው ዓይኔን ሳሸው ወዲያው ነጭ ሆነ። የጉበቴ ምርመራ ውጤትም ንጹሕ ሆነ።

ከ፳፰/፲፩/፲፱፻፺፫ ጠዋት ሽንት ከሸናሁ በኋላ ፀበል ጠጣሁ ቋርሴን በልቼ ሽንቴን ስሸና ጥቁር ደምና የመድኃኒት ሽታ የነበረው ሲሆን ለአራት ቀናት በጠቅላላው ፫ ሊትር የሚሆን ደም ሸናሁ። ምንም እንኳን ለቤተሰቦቼ በዕቃ አስቀምጬ ሳሳያቸው በጣም ቢጨነቁም፤ እኔ ግን የፀበሉ ኃይል መሆኑ ስለገባኝ ለሐኪም አልተናገርኩም። በ፪/፲፪/፲፱፻፺፫ ከ፭ተኛው ቀን በኋላ ግን ነጭ ሽንት ሆነ።

በ፪/፲፪/፲፱፻፺፫ ለሐኪሙ ውጤቱን አቅርቤ ለ፬ ቀናት የሸናሁትን ሽንትና ሰውነቴ ላይ የወጣውን ነጠብጣብ ሳሳያቸው ከበሽታው ጋር ግንኙነት እንደሌለውና ይህም ሰውነታችን ውስጥ ያለው ደም ፈሶ እንዳያልቅ የሚቆጣጠረው ነገር ስላነሰ ሊሆን እንደሚችል በማመን ደሜን ለኩኝ ደሜ ግን ሙሉ ነበር። ከዚያም በጣም ተገርመው ከአሁን በፊት እንዲህ ዓይነት ነገር አጋጥሟቸው እንደማያውቅና ሁኔታውም ልዩ ተአምር ስለሆነባቸው ለተጨማሪ ምርመራ ሌላ ቦታ ተልኬ በውጤቱ መሠረት ከበሽታዬ ሙሉ በሙሉ ልፈወስ ችያለሁ። ✣



www.ethiopianorthodox.org